# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

እሁድ | 83ኛ ዓመት ቁጥር 013 መስከረም 13 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# በዓባይ ውሃ ፍትሐዊ አጠቃቀም መርህን ማስፈን ብቸኛው አማራጭ ነው

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- በዓባይ ውሃ አጠቃቀም ፍትሐዊ እና ምክንያታዊ አጠቃቀም መርህን ማስፈን ብቸኛው አማራጭ መሆኑን የኢትዮጵያ ወገን ተደራዳሪዎች ልዑካን መሪ አምባሳደር ስለሺ በቀለ ገለጹ፡፡

የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብን በተመለከተ የኢትዮጵያ፣ ግብጽ እና ሱዳን የሦስትዮሽ ሁለተኛ ዙር ውይይት ትናንት መስከረም 12 ቀን 2016 ዓ.ም በአዲስ አበባ ተጀምሯል፡፡

ሁለተኛው የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ የውሃ ሙሌት እና አለቃቀቅ ደንቦች እና መመሪያዎች የሦስትዮሽ ድርድር መክፈቻ ላይ የኢትዮጵያ ወገን ተደራዳሪዎች ልዑካን መሪ አምባሳደር ስለሺ በቀለ (ዶ/ር) እንዳሉት፤ ይህ ውይይት እየተካሄደ

በዓባይ ውሃ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ፡- በአዮብ ተፈሪ

## «አረንጓዴ ዐሻራ የምርታማነታችንና የዕድገታችን ሞተር ነው»

- አቶ ደስታ ሌዳሞ
የሲዳማ ክልል ርዕሰ መስተዳድር

ጌትነት ምህረቴ

አዲስ አበባ፡- የአረንጓዴ ዐሻራ የአፈር መሸርሸርን በመከላከል፣ ፍራፍሬዎችን በማልማት፣ ንብ በማነብና እንስሳትን በማድለብ የምርታማነታችንና የዕድገታችን

“አረንጓዴ ዐሻራ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## «የመከላከያ ሠራዊት ሥነ ልቦና ግንባታ ዋና ዳይሬክቶሬት የሠራዊታችን የግንባታ ማዕከል ሆኖ እየሠራ ነው»

-ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ
የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም

መስከረም ሰይፉ



አዲስ አበባ፡- የመከላከያ ሠራዊት ሥነ ልቦና ግንባታ ዋና ዳይሬክቶሬት የሠራዊታችን የግንባታ ማዕከል ሆኖ እየሠራ ነው ሲሉ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ ገለጹ፡፡ ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ የመከላከያ ሠራዊት ሥነ ልቦና ግንባታ ዋና ዳይሬክቶሬትን የሥራ እንቅስቃሴ ትናንት በስፍራው ተገኝተው ጎብኝተዋል።

ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ከጉብኝቱ በኋላ የመከላከያ ሠራዊቱ የሥነ ልቦና ግንባታ ዋና ዳይሬክቶሬት መከላከያ ሠራዊቱ በሞራል እና በሥነ ልቦና የተገነባ መሆን እንዲችል በሚዲያው ዘርፍ፣ በኪነጥበባት ሥራዎች፣ በግንባታ ጽሑፍ እና በስፖርቱ ዘርፍ በርካታ ውጤታማ ሥራዎችን ሠርቷል ብለዋል።

የመከላከያ ኪነ ጥበባት ሥራዎች ለሀገራችን የዘመናዊ ሙዚቃ

“የመከላከያ ሠራዊት... ወደ ገጽ 4 ዞሯል















## በዓሉ ሲከበር ለጽንፈኞች አጀንዳ በር መክፈት አይገባም

ገጽ 4









ወይዘሮ ፍሬህይወት ገብረመድህን

## የመስቀል ደመራ እና ኢሬቻ በዓላት የመዲናዋን የቱሪዝም ፍሰት ይበልጥ የሚያነቃቁ ናቸው

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ የመስቀል ደመራ እና ኢሬቻ በዓላት ሲከበሩ የመዲናዋን የቱሪዝም ፍሰት ይበልጥ የሚያነቃቁ ተግባራት እንደሚከናወኑ የአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነ ጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ ገለጸ።

የአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነ ጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ የቱሪዝም ልማት እና ፕሮሞሽን ዳይሬክተር ወይዘሮ ፍሬህይወት ገብረመድህን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ የተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) በማይዳሰሱ ቅርሶች ከተመዘገቡት መካከል የመስቀል ደመራ እና ኢሬቻ በዓላት ይገኙበታል። እነዚህ በዓላት በአዲስ አበባ ከተማ በአደባባይ ከሚከበሩ በመሆኑ የመዲናዋን የቱሪዝም ፍሰት ይበልጥ የሚያነቃቁ ናቸው። ይህን ታሳቢ ያደረጉ የመዲናዋን የቱሪዝም መዳረሻዎችን የማስተዋወቅ ሥራ በትኩረት እየተሠራ ነው።

በዓላቱ የቱሪስት መስህብ እንዲሆኑ ለማድረግ እየተሠራ እንደሚገኝ አመልክተው፤ መዲናዋን ተመራጭ የቱሪስት መዳረሻ እንድትሆን ለማድረግ እና የቱሪዝም ፍሰቱን ለማነቃቃት አዳዲስ የቱሪዝም መዳረሻዎችና የበዓላቱን ሃይማኖታዊና ባህላዊ እሴቶች በስፋት የማስተዋወቅ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ተናግረዋል።

የመስቀል በዓል በአደባባይ የሚከበር፣ በዩኔስኮ የተመዘገበ፤ ሃይማኖታዊ ትውፊት ያለው እና በተለያዩ ትእይንቶች የሚከበር በዓል ነው ያሉት ፍሬህይወት፣ በዓሉ ሃይማኖታዊ፣ ታሪካዊ እና ባህላዊ እሴቱን ጠብቆ እንዲከበር ቢሮው ከሚመለከታቸው አጋር አካላት ጋር በቅንጅት እየሠራ ነው ብለዋል።

በሀገሪቱ ብሎም በመዲናዋ ባለፉት ዓመታት በኮቪድ እና ሀገራዊ የጸጥታ ሁኔታ ምክንያት የቱሪዝም ሴክተሩ መቀዛቀዝ አሳይቶ እንደነበር አውስተው፤ ይህንን ሴክተር ሊያነቃቃ በሚችል መልኩ የቱሪዝም መዳረሻዎችና በዓላቱን የማስተዋወቅ ሥራ እየተሠራ እንደሆነ ፍሬህይወት ተናግረዋል።

ለዚህም ቢሮው ከመስከረም 16 ከሚከበረው የደመራ ቀን ጀምሮ የራሱን ቦታ ወስዶ ባህሉንና መዲናዋ የሚገኙ የቱሪዝም መስህብ መዳረሻዎችን የማስተዋወቅ ሥራዎች ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ መሆኑን ገልጸዋል። ይህም ዘንድሮ የታደሙ የውጭ ቱሪስቶች በየዓመቱ እንዲታደሙ ለማድረግ የሚያስችል መሆኑን አመልክተዋል።

ሌላው በመዲናዋ የሚከበረው በዓል ኢሬቻ መሆኑን ጠቁመው፤ የኢሬቻ በዓል ከተለያዩ ክልሎችና እህት ከተሞች የሚመጡ የኅብረተሰብ ክፍሎች የሚሳተፉበት እንዲሁም ከውጭ ሀገራት የሚመጡ ቱሪስቶች የሚገኙበት በዓል ስለሆነ ሕዝቦች ባህልና እሴታቸውን የሚያስተዋውቁበትና ማኅበራዊ ትስስር የሚፈጥሩበት መሆኑን ተናግረዋል። ይህም የከተማዋን ኢኮኖሚ በማነቃቃት ጉልህ ፋይዳ መኖሩን ገልጸዋል።

ቢሮው የተለያዩ ድረ ገጾችን በመጠቀም በዓላቱንና የቱሪዝም መዳረሻዎችን የገጽታ ግንባታ ሥራ መሥራቱን አንስተው፣ ኅብረተሰቡ ስለቱሪዝም ያለውን ግንዛቤ ለማጎልበትም የንቅናቄ ሥራዎች በማከናወን የቱሪዝም ዘርፉን ለማነቃቃት ሥራ መሥራቱን ጠቅሰዋል።

የቱሪስቶችን የቆይታ ጊዜን ለማራዘም ያሉትን የቱሪስት መዳረሻዎች በማስፋት እና የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ማለትም ከሆቴሎችና ከአስጎብኚ ድርጅቶች ጋር በጋራ እየተሠራ መሆኑን አስታውቀዋል፤

ከተማዋ ከቱሪዝም ዘርፉ ከፍተኛ ተጠቃሚ እንድትሆን ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት በሙሉ የበኩላቸውን ድርሻ እንዲጫወቱም ጥሪ አቅርበዋል።

# «ያሆዴ» የተጣላን የሚያስታርቅ፣ የተራራቀን የሚያቀራርብ የአብሮነት በዓል ነው

**ታደሰ ብናልፈው**



ሆሳዕና፡- የሀድያ ብሔር የዘመን መለወጫ «ያሆዴ» በዓል የተጣላን የሚያስታርቅ፣ የተራራቀን የሚያቀራርብ የአብሮነት በዓል ነው ሲሉ የባህልና ስፖርት ሚኒስትር አቶ ቀጀላ መርዳሳ ገለጹ።

የሀድያ ብሔር የአዲስ ዓመት የዘመን መለወጫ «ያሆዴ» በዓል በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መዲና ሆሳዕና ከተማ በትናትናው ዕለት ተከብሮ ውሏል።

በበዓሉ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የባህልና ስፖርት ሚኒስትር አቶ ቀጀላ መርዳሳ፤ ያሆዴ በዓል የተጣላን የሚያስታርቅ፣ የተራራቀን የሚያቀራርብና አብሮነትን በማጠናከር ለሀገር ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ እድገት ከፍተኛ ሚና የሚያበረክት ነው።

በሀድያ ብሔረሰብና በሌሎች የሀገራችን ማኅበረሰቦች ያሉትን የተለያዩ ባህሎችን በማሳደግ ለኢኮኖሚና ፖለቲካዊ እድገት እንዲውሉ ለማድረግ እየሠራን ነው ብለዋል።

የያሆዴ የዘመን መለወጫ በዓል ከማንኛውም ሃይማኖት አስተሳሰብ ነፃ የሆነና የተለያየ ሃይማኖት ያላቸው ማኅበረሰቦች በአንድነት የሚያከብሩት የፍቅር፣ የሰላም፣ የይቅርታና የአብሮነት መገለጫ ባህላዊ በዓል መሆኑን ገልጸዋል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በሀገሪቱ የሚገኙ የተለያዩ ባህሎችን የማሳደግ ሥራ በመሥራት ከትውልድ ትውልድ እንዲተላለፉና ለኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንዲውሉ የማድረግ ሥራ እየሠራ እንደሚገኝም ጠቁመዋል።

የሀድያ አባቶችና እናቶች የራሳቸውን ባህል፣ ቋንቋ፣ ፍልስፍና የቀን መቁጠሪያ በመፍጠርና እንዳይጠፉ ጠብቀው ማቆየታቸውን አውስተው፤ ያሆዴን የመሰለ የማኅበረሰቡን አንድነት የሚያጠናክር ትልቅ በዓል ለትውልድ ማስተላለፍ እንደሚገባ ተናግረዋል።

እሴቱን፣ ባህሉን፣ ቋንቋውን ያላከበረ ማኅበረሰብ መብቱ የተጓደለ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፣ የሀድያ ማኅበረሰብ ባህሉንና ቋንቋውን ጠብቆ ለትውልድ የማስተላለፍ ሚናውን እየተጫወተ ይገኛል ብለዋል።

የማኅበረሰቡን ባህል፣ ኢኮኖሚ፣ ፖለቲካና አብሮነቱን የሚያጠናክረውን የያሆዴን የዘመን መለወጫ በዓል ሻይሸራረፍና ሳይበረዝ ለትውልድ ለማስተላለፍና በዩኔስኮ ለማስመዝገብ በትኩረት እንደሚሠሩ አመልክተዋል።

የሀድያ ዞን ዋና አስተዳደር አቶ አብረሃም መጫ የዘመን መለወጫ በዓሉን አስመልክተው ባስተላለፉት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት፤ የሀድያ ብሔር ዘመን መለወጫ ያሆዴ የሀገርን ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እድገት ለማምጣት ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ የሚገኝ ባህላዊ ክብረ በዓል ነው ብለዋል።

የያሆዴ የዘመን መለወጫ በዓል ለሀድያ ብሔረሰብ የዘመን መለወጫና ቅድሚያ የሚሰጠው ባህል ነው ሲሉ ገልፀዋል።

የያሆዴ ባህላዊ በዓል የማኅበረሰቡን አንድነት የሚያፀና ከመሆን ባለፈ የፆታ እኩልነትን የሚያስተምርና ፍትሕዊነትን የሚያሰፍን፣ የእርቅ ሥነ ሥርዓትም ያለው ነው ሲሉ አብራርተዋል።

የሀድያ ብሔር በ13ኛውና በ14ኛው ክፍለ ዘመን የራሱ የሆነ የእስላሚክ ሱልጣኔት ያለው ትልቅ ማኅበረሰብ ነው ያሉት ኃላፊው፤ አሁንም የህገ ሥርዓቱን፣ ባህሉንና ቋንቋውን ጠብቆ ከሌሎች ማኅበረሰቦች ጋር በፍቅርና በአንድነት የሚኖር የሰላም ተምሳሌት ሕዝብ መሆኑን ተናግረዋል።

የያሆዴ በዓል የተጣላ የሚታረቅበት፣ የተራራቀ የሚገናኝበት፣ ጨለማ ዘመን አልፎ ብርሃን የሚታይበት የሰላምና የብልፅግና በዓል እንደሆነ አቶ አብርሃም ገልጸዋል።

በዓሉ ለሀገርም የተለያዩ ጠቀሜታዎችን የሚያስገኝ በመሆኑ በዩኔስኮ ለማስመዝገብ እየተሠራ መሆኑን ጠቁመው፣ በዓሉን እሴቱን ጠብቆ ሳይሸራረፍ ለትውልድ እንዲተላለፍም የተለያዩ ተግባራት እየተከናወኑ እንደሚገኙ ነው የገለጹት፡፡

# የጊፋታ በዓልን

## በዩኔስኮ የዓለም ቅርስነት ለማስመዝገብ በሂደት ላይ ነው

**አመለወርቅ ከበደ**



አዲስ አበባ፡- የወላይታ ብሔር የዘመን መለወጫ የሆነውን የጊፋታን በዓል በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) የዓለም ቅርስነት ለማስመዝገብ እየተሠራ እንደሚገኝ የወላይታ ዞን አስተዳደር አስታወቀ፡፡

የወላይታ ዞን ዋና አስተዳዳሪ አቶ ሳሙኤል ፎላ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የጊፋታን በዓል በዩኔስኮ በዓለም አቀፍ የማይዳሰስ ቅርስነት ለማስመዝገብ የተለያዩ የዝግጅት ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛል፡፡

ለዩኔስኮ ምዝገባ እንዲረዳ ከኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር፣ ከኢትዮጵያ የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን እንዲሁም ከወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመሆን በጊፋታ በዓል ላይ ጥናት መደረጉን አመልክተዋል።

የጊፋታ በዓል ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማኅበራዊ ፋይዳው በጥናቱ አማካኝነት በመለየት በባለሙያዎች እንዲገመገም መደረጉን ጠቁመዋል።

አቶ ሳሙኤለ እንደተናገሩት፤ የባህልና ስፖርት ሚኒስቴርና የሚመለከታቸው የቅርስ ተቋማት ጊፋታ በዩኔስኮ እንዲመዘገብ አስፈላጊውን የዝግጅት ሥራ እያከናወኑ ይገኛሉ፡፡

ጊፋታ ለኅብረ ብሔራዊነት፣ ለሀገር አንድነትና ውበት ሚናው የጎላ ነው ያሉት አስተዳዳሪው ፤ የጊፋታ በዓል አከባበር የተለያዩ ቁሳዊና መንፈሳዊ ሥርዓቶች የሚከናወን በመሆኑ የኅብረብሔራዊነት መገለጫ ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በዓሉ የአብሮነትና ይቅርታ በዓል በመሆኑ ማኅበረሰቡ በመደጋገፍ በአደይ አበባ ደምቆ ከማክበሩም በተጨማሪ፤ የተጣሉና ደም የተቃቡ ሰዎች ሁሉ ይቅር የሚባባሉበት በዓል በመሆኑ በዩኔስኮ መመዝገቡ ይበልጥ በዓለም እንዲታወቅ ይረዳል ብለዋል።

የጊፋታ በዓል ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን ያነሱት ዋና አስተዳዳሪው፤ ለጊፋታ በዓል ወንዶች ዓመቱን በሙሉ ለበሬ መግዣ የሚሆን ገንዘብ የሚቆጥቡ ሲሆን፤ ሴቶች ደግሞ ለበዓሉ የሚሆኑ ምግቦችን በማዘጋጀት በደመቀ ሁኔታ እንደሚያከብሩት አስረድተዋል።

በዓሉን በዩኔስኮ ለማስመዝገብ ከሚደረገው ጥረት በተጨማሪ ከበዓሉ ጋር ተያይዞ ማኅበረሰቡ የሚገለገልባቸውን ቁሳቁሶች በቀጣይ በሙዚየም መልክ አዘጋጅቶ በማስቀመጥ ለጎብኚዎች ክፍት ይደረጋል ብለዋል፡፡

በዚህም ከዓለም አቀፋዊ እንቅስቃሴዎች ጋር ተያይዞ የሚመጡትን የበዓል መበረዞች ለመግታት የዞኑ መንግሥት በትኩረት እየሠራ ይገኛል ሲሉ አስረድተዋል።

አቶ ሳሙኤል እንደገለጹት፤ የጊፋታ በዓል በዞኑ በሚገኙት 23 ወረዳዎች እየተከበረ ይገኛል። በተጨማሪም በወላይታ ሶዶ ስታዲየም በድምቀት እየተከበረ ነው፡፡

በዓሉን ለማክበር በርካታ ዝግጅቶች መደረጋቸውን አስታውሰው፤ በወላይታ በሚከናወነው ሥነ ሥርዓት ከ200 ሺህ በላይ ታዳሚዎች ይገኛሉ ተብሎ ይጠበቃል ብለዋል፡፡

በመጨረሻም ዋና አስተዳዳሪው መላ ኢትዮጵያውያን በዓሉን ሲያከብሩ የተቸገሩትን በመርዳትና በዘላቂነት የሚረዱበትንና አብሮነትን በሚያጎለብቱበት መልኩ መንገድ ሊሆን ይገባል ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል ፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ስለሌላው መኖርን የሕይወት መርሕ ልናደርገው ይገባል!

ቀናት ሳምንታትን፤ ሳምንታት ወርን ፤ ወራት አመትን እየወለዱ በተንሰላሰለ የጊዜ ሂደት ውስጥ ትውልድ ተፈጥሮ በትውልድ ይተካል። ትውልዶችም ዘመናቸውን በሚዋጅ ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ መስተጋብሮቻቸው የየራሳቸውን ጥሩም መጥፎም የታሪክ ትርክቶችን ፈጥረው ያልፋሉ። በዚህም በቀጣይ ትውልዶች የሚወቀሱበት ወይም የሚወደሱበት እውነታ ይፈጠራል።

ይህንን ሰብአዊ መስተጋብር ታሳቢ በማድረግም በየትኛውም ዘመን የኖሩ ትውልዶች የመጪ ትውልዶችን ብሩህ ነገዎች ታሳቢ ያደረጉ ተግባራትን ሲፈጽሙ፤ በዚህም የትውልዶችን ቀጣይነት ብቻ ሳይሆን ከትናንት ዛሬ፤ ከዛሬ ደግሞ ነገ የተሻለ ኑሮ የሚኖሩበትን በጎ ኅሊና ፈጥረው፣ ለዚህም በቁርጠኝነት ሲንቀሳቀሱ ማየት የተለመደ ነው።

ይህ ከቤተሰብ የሚጀመረው ትውልዶችን በበጎ ኅሊና ለራሳቸው፤ ለቤተሰባቸው እና ለሀገራቸው እንዲጠቅሙ አድርጎ የማብቃት፤ ሰውነታቸውን በተሟሉ ሰብዓዊ እሴቶች ሙሉ የማድረግ ኃላፊነት በእኛም ሀገር ዘመናት ያስቆጠረ ትልቁ ማኅበራዊ እሴታችን ነው፤ የትውልዶችን የመንፈስ ፣ አዕምሮ እና ሥነ ልቦና ስብዕና በመቅረጽ ሂደትም አልፋና ኦሜጋ ተደርጎ የሚወሰድ ነው።

ከዚህ የተነሳም እንደ ሀገር በመጣንባቸው የረጅም ዘመናት ታሪክ ውስጥ፤ እንደ ሕዝብ ተቻችሎና ተከባብሮ መኖር ችለናል፤ ይህ ታሪካዊ እውነታ እንደ ሀገር የምንኮራበት ትልቁ የታሪካችን ትርክት ከመሆን አልፎም በዓለም አቀፍ ደረጃ ደምቀን የምንታይበትና የምንሰማበት መልካችን እና ቋንቋችን መሆን ችሏል። በዘመናት መካከል መጥተው ያለፉ እና ያሉ ትውልዶችም የማንነት ግንባታ ጡብ ሆኗል።

የአሁኑም ትውልድ ቢሆን በብዙ ተግዳሮቶች /ፈተናዎች ውስጥ፤ ብዙ ያልተገቡ ዋጋዎችን ከፍሎ ለማለፍ የተገደደ ቢሆንም፤ አብዛኛው ማንነቱ የተገነባው የራሱንና የጎረቤቱን፤ የማኅበረሰቡንና የሀገሩን፤ ከዚያም አልፎ የመጪዎቹን ትውልዶች ነገዎች ብሩህ ማድረግ በሚያስችሉ መንፈሳዊ፣ አዕምሯዊ እና ሥነ ልቦና እሴቶች ነው።

«ጠላትህን እንደራስህ ውደድ» ከሚለው የክርስትና መንፈሳዊ አስተምሮ የሚገራው ማንነቱ ፤ «ለጎረቤቱ መልካም ሥራ ያልሠራ እንደ አመነ አይቆጠርም» በሚለው የእስልምና ትልቅ እሴት የሚቀዳው መንፈሳዊ ልምምዱ ፤ በበጎ ኅሊና ላይ የተገነባው ማኅበራዊ መስተጋብሩ፤ በየዘመኑ ፈተና ሆነው ከፊቱ የቆሙ የራስ ወዳድነት ዘመን አመጣሽ አስተምህሮዎች እና የፖለቲካ እሳቤዎች ሊፈጥሩ ይችሉ የነበረውን ሀገራዊ ጥፋት መሻገር እንዲችል አቅም ሆነውታል።

ስለ ሀገሩ እና ነፃነቱ ፍጹም ቀናኢ፤ ሁሌም ይህንን ታሳቢ ያደረገ የማንነት ዝግጅት እንዲኖረው ረድተውታል። እንደ አንድ ትልቅ ማኅበረሰብ/ ሕዝብ ከራሱ አልፎ በዓለም አቀፍ ደረጃ ስለ ነፃነት የማንቂያ ደውልና የመንፈስ ጽናት እንዲሆን አስችለውታል። በዓለም አቀፍ አደባባዮች ቀና ብሎ የሚራመድበትን የሥነ ልቦና ከፍታ አላብሰውታል ።

በትውልዶች ቅብብል ውስጥ ባለ የማንነት ግንባታ እያለፈ ያለው ይህ ትውልድም ፤ እንደ ትውልድ ያለበትን ኃላፊነት ለመወጣት፤ ከሁሉም በላይ የቀደሙት አባቶቹና አያቶቹ እሱን አምጠው የወለዱበትን በጎ ኅሊና እና ኅሊናው የተገነባበትን እሴቶች በአግባቡ ሊያጤናቸው፤ ሊረዳቸው፤ የራሱ ሊያደርጋቸው፤ ለመጪዎቹ ትውልዶች ዘመኑን በሚዋጅ መንገድ ሊያጎለብት፤ ሊያሳድጋቸው ይገባል።

አሁን እያጋጠመው ያለውን ተግዳሮት አሸንፎ ፤ ዓይኑን ከፍቶ ያያቸውን ብሩህ ነገዎች የራሱ ማድረግ የሚችለው፤እንደ ማኅበረሰብ ብዙ ፈተናዎችን በጽናት ተሻግረን ዛሬ ላይ እንድንደርስ ያስቻሉንን ፤ ከራስ ወዳድነት ይልቅ ስለሌላው መኖርን መርሕ አድርገው ጸንተው ለቆሙ እሴቶቻችን ተገቢውን ከበሬታ መስጠት ሲችል ፤ በነሱ የመታመን የማንነት ስሪቱን የአደባባይ መገለጫው ሲያደርገው ነው!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ሠላማዊ መንገድ አማራጭ የሌለው ምርጫችን ነው

**ሰው መሆን**

በአዲሱ ዓመት ወደ ሠላም፣ እድገትና የተሟላ ማንነት ሊወስደን የሚችል አዲስና የተሻለ አስተሳሰብ መያዝ እንዳለብን ይታመናል። ይህንን ለማሳካት «ጊዜ ብቻ ሳይሆን መቀየር ያለበት እኛው እራሳችን ጭምር ነን» የሚል እሳቤ ያላቸው ብዙኃን ናቸው።

ምክንያቱ ደግሞ ዓመቱ ተቀይሮ አስተሳሰባችን ቀድሞ የነበረበት (የጥላቻ፣ የዘር፣ የግጭት) እሳቤ ውስጥ የተዘፈቀ ከሆነ ጊዜ መቀየሩ ብቻ ዕድሜን ከመቁጠር ውጪ የሠላም፣ የፍቅር የአንድነት እሳቤን ስለማይሰጠን ነው። ከዓመቱ ጋር ወደ ፍፁም የሠላምና የአንድነት ልዕልና የምንሻገር ከሆነ ግን እውነትም «ከጊዜው ጋር እኩል ተቀይረናል» ለማለት ያስደፍረናል።

ከላይ ያነሳነውን ተጠየቅ ተንተርሰን እኛ (ኢትዮጵያውያን) የመረጥነውን መንገድ ለመፈተሽ ብንሞክር ምላሻችን በጊዜ ሂደት የሚታወቅ ቢሆንም፤ ከእስካሁኑ ግን «ጊዜው ብቻውን እንጂ እኛም ከጊዜው ጋር» አለመቀየራችንን ለመታዘብ የሚቸግር አይመስለኝም። ለዚህም መልካም ምኞቶችን እየተመኘን በሁከትና በብጥብጥ ያሳለፍናቸው አመታትን መቁጠር በቂ ነው።

ልዩነቶቻችንን ቁጭ ብሎ በመነጋገር አጥብቦ በሠላም ከመመላለስ፤ ዛሬም ልዩነቶችን በኃይል ለመፍታት የሚደረጉ ያልተገቡ ጥረቶች ብዙ ዋጋ እያስከፈሉን ነው። ይህ ዓይነቱ አስተሳሰብ ሰፊውን ማኅበረሰብ የሚወክል ባይሆንም ወደ እሱ ለማጋባት የሚደረጉ ጥረቶች አደገኝነት በራሱ የሀገራዊ ስጋት ምንጭ መሆኑ አይካድም።

«ማኅበረሰብን አንቂ ነን፤ የፖለቲካ ሊሂቃን ነን፤ ተፅእኖ ፈጣሪ ነን» ወዘተ የሚሉ ግለሰቦች ዘመኑን በማይዋጅ በዚህ አስተሳሰብ ታጅለው በየአደባባዩ ሲንገዋለሉና ሲጮሁ መስማት የተለመደ ነው። እውነታው በአሮጌ አቁማዳ አዲስ ወይን ከመከተት ተለይቶ የሚታይ አይደለም።

«አዲስ ዓመት ብለን» ልዩነታችንን የምናቻችልበት አዲስ እሳቤና የተሻለ አማራጭ ለመያዝ ቁርጠኝነቱ ከሌለን ነገም በትናንቱ ችግራችን ውስጥ መቆየታችን የማይቀር ነው። አዲሱንም አመት አሮጌ ማድረጋችን የማይቀር ነው።

ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ የአዲስ ዓመት መልዕክት ባስተላለፉበት ወቅት «ችግሮቻችንን በጊዜያዊ ጥገና ሳይሆን ከመሠረቱ ለመፍታት የምንንቀሳቀስበት ዘመን እናድርገው፡፡ በሠላም ግንባታ፣ በውይይትና ምክክር፣ በጋራ ጉዳይ ሀገራዊ መግባባት ላይ በመድረስ፣ ጥላቻ፣ መናናቅ፣ መገፋት፣ ጥቃትን በጽኑ በመታገል መብቶችን በማክበር፣ በማስከበር ሁላችንም ድርሻ አለን፡፡ የዓመቱ ዋና ትኩረታችን ይሁን፡፡ አዲስ ዓመት አዲስ እይታን፣ የአስተሳሰብ እድሳትን፣ የተሻለ እንድንሠራ ቃል መግባትን ይጋብዛልና እንጠቀምበት» ማለታቸው ይታወሳል።

መልዕክቱ ከሁሉም በላይ እንደ ሀገር ከፍ ባለ ቁርጠኝነት ስር ነቀል ለውጥ በማምጣት ወደኋላ እየጎተተን ከሚገኝ ችግር መውጣት እንደሚጠበቅብን የሚያመላክት ነው። ዓመቱ ሲቀየር እኛ በአዲስ እሳቤ ለመቀየር በመቸገራችን ሰቅዞ ከያዘን የልዩነት አዙሪት መውጣት አለመቻላችንን የሚጠቁም ነው።

ለችግሮቻችን ሰላማዊ መንገድ አማራጭ የሌለው መፍትሔ መሆኑን ይነግረናል። ሥልጣኔን፣ እድገትና አብሮነት በዚህ መሰል ዘመናዊ አስተሳሰብ የሚገኝ እንጂ ለዓመታት በቆየንበት የጥላቻ፣ የመገፋፋትና ልዩነትን የማጉላት መንገድ እንደማይመጣ በግልፅ የሚያስረዳ ሆኖ እናገኘዋለን።

ላለፉት አምስት ዓመታት ኢትዮጵያውያን ጫፍና ጫፍ በረገጡ እሳቤዎች ተወጥረው ቆይተዋል። እነዚህ ፅንፍ የያዙ መሳሳቦች ማኅበረሰባችን ሰላማዊ ሕይወቱን እንዳይመራ፣ የተረጋጋ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት እንዳይፈጠር አድርገዋል። ከመነጋገር ጠብ-መንጃን ምርጫ ማድረግ ዛሬም እንደ ሀገር ያልተገባ ዋጋ እንድንከፍል እያደረገን ነው።

ከዚህ በዘመናት መካከል ብዙ ዋጋ ካስከፈለንና ዛሬም እያስከፈለን ካለው አሮጌ ጊዜ ያለፈበት የፖለቲካ ባህል፤ ወጥተን ችግሮቻችንን በውይይትና በመነጋገር መፍታት ወደምንችልበት ያደገ የፖለቲካ ባህል መጓዝ አለብን። ለዚህም ሃሳብን በኃይል ገዥ ለማድረግ የሚንቀሳቀሱ ቡድኖች አደብ መግዛት ይኖርባቸዋል። ይህ የአሮጌው ዘመን እሳቤ ማብቂያ ሊበጅለት ይገባል።

ዛሬም ለውይይትና ለድርድር፤ ለሃሳብ ልዕልና በራቸውን ክፍት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ይህ መሆን ሲችል ብቻ ነው ከዘመኑና ቀን ቆጥሮ ከሚቀየረው አዲስ ዓመት ጋር እኛም መቀየራችንን እርግጠኝ መሆን የምንችለው። ለመልካም ምኞታችን ባለ ጉዳዮች የምንሆነው።

በርግጥ ምሁራን፣ የፖለቲካ ሰዎች፣ የማኅበረሰብ አንቂዎች፣ ጦር የሰበቁ አካላት ሁሉም የሚያነሱት የልዩነት ጥያቄዎች ሊኖራቸው ይችላል። የማያግባቡ ጫፍና ጫፍ የረገጡ ርዕሰ ጉዳዮችና አጀንዳዎችም አይጠፉም። ይህ እንደ እኛ ባለ ብዝሃነት መገለጫው ለሆነ ማኅበረሰብ አዲስ ሊሆን አይችልም። የሚጠበቅ ነው።

ዋናው ቁምነገር መሆን የሚገባው ግን፤ የትኛውንም ዓይነት ልዩነት በሰላማዊ መንገድ በውይይት፤ የሃሳብ የበላይነት መሠረት ባደረገ መንገድ ለመፍታት እራስን ሁሌም ዝግጁ ማድረግ ነው። ይህንንም በኢትዮጵያዊነት ማዕቀፍ፤ ሉዓላዊነትን በማይጥስ አግባብ ለመከወን ለሚያስችል መርህ ለመተግበር ቁርጠኛ መሆን ነው።

ለዚህ ደግሞ አሁን ላይ ብዙ ሂደቶችን አልፎ ወደ ሥራ ለመግባት እየተንደረደረ ያለው ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን ትልቅ አቅም ነው። መንግሥት የሀገሪቱ ያደሩ ሆኑ ከነሱ የተዋለዱ አሁነኛ ችግሮቻችን በሠላማዊ መንገድ በውይይት እንዲፈቱ የሚያስችል አቅጣጫ አስቀምጧል። ለተፈጻሚነቱም ገለልተኛ ተቋም መሥርቷል (ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን)።

በርግጥ ለሀገሪቱ ችግሮች ዘላቂ መፍትሔ ለማምጣት በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ተሰባስቦ መነጋገር ወሳኝ ነው። ሁሉንም የማኅበረሰብ ክፍሎች ያካተተ የውይይት መድረክ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፤ በመድረኩ ሁሉም ልዩነቶች በአግባቡ ሊታዩ እና ሊመረመሩ ይገባል። ተጨባጭ ስለመሆናቸውም ማስተማመኛ ማግኘት ያስፈልጋል።

ለዘመናት የቆዩ ቁርሾዎችን ፈር ለማስያዝ፣ የፖለቲካ ልዩነቶችን በውይይት እና በንግግር ለመፍታት፣ የልማት፣ የወሰን እና ለሌሎች ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት አዲሱን ዓመት በአዲስ እሳቤና ቀና መንፈስ ልንቀበለው ይገባል። የሰው ልጅን ሰብዓዊ ክብር ከሚያዋርደው ጦርነትና ግጭት ከቂምና ቁርሾ ባለፈ የምናተርፈው ምንም እንደሌለ በአግባቡ ማጤን ይገባናል።

በድህነትና በልማት እጦት ችግር ውስጥ የሚገኝን ማኅበረሰብ ወደ ግጭትና ጦርነት ገፋፍቶ «ከድጡ ወደ ማጡ» ከመውሰድ ይልቅ ልዩነቶችን እና ሃሳቦቻችንን በንግግር የመፍታት ልምድ ማዳበር ይኖርብናል። እነዚህ ልዩነቶች ደግሞ ከሕዝብ ሠላም ከሀገር አንድነት በታች መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል።

ቀደም ሲል እንዳነሳሁን የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ሀገራዊ ችግሮችን በውይይት ለመፍታት ኃላፊነት ወስዶ እየሠራ ነው ፤ ይህንን ጥረት በማገዝ የሀገርን ሰላም ማጽናት ደግሞ የሁሉም ዜጋ ኃላፊነት ነው። በተለይ «በአዲስ ዓመት አዲስ እሳቤ» መያዝ ካለብንና ትናንት ከነበርንበት ያረጀ አመለካከት ለመውጣት ከወሰንን የሠላምን ቀና መንገድ ልንመርጥ ይገባል።

ሀገር አሸናፊ እንድትሆን ቅሬታን የፈጠሩ ጉዳዮችን ወደ ውይይት መድረኩ መጥተው መፍትሔ እንዲያገኙ የጋራ ጥረት ይፈልጋል። ከሁሉም በላይ ግን በመካከላችን የተፈጠሩ አጥሮች ሉዓላዊ ከሆነችው ኢትዮጵያ እንደማይበልጡ መተማመን ላይ መድረስ ይኖርብናል።

በዚህ መንገድ የሃሳብ ልዕልናን ብቻ መሠረት በማድረግ፣ መነጋገርን እና መደማመጥ ብቻ በማስቀደም፤ ለሁሉም ኢትዮጵያውያን መፍትሔ የሚሆኑ ሠላማዊ አማራጮችን ማግኘት እንችላለን። ለዚህ ነው በራችንን ለሠላሙ መንገድ ብቻ መክፈት የሚኖርብን። ሠላም!

ዜና

# የስደተኞችን ደህንነት ለማስጠበቅ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- የስደተኞች መብትና ደህንነት እንዲጠበቅ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የየድርሻቸውን ኃላፊነት ሊወጡ እንደሚገባ የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማኅበራት ኮንፌዴሬሽን ገለጸ፡፡ የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማኅበራት ኮንፌዴሬሽንና የሶማሊያ ሠራተኛ ማኅበራት ኮንፌዴሬሽን በጋራ ለመሥራት ተፈራርመዋል፡፡

የኮንፌዴሬሽኑ ፕሬዚዳንት አቶ ካሣሁን ፎሎ ፌዴሬሽኑ ከሶማሊያ አቻው ጋር በጋራ ለመሥራት የሚያስችል ስምምነት በተፈራረሙበት ወቅት እንዳሉት፤ ስደተኞች እንደ ማንኛውም ዜጋ ክብራቸውና ደህንነታቸው ሊጠበቅላቸው ይገባል፡፡ ለዚህ ደግሞ መንግሥትን ጨምሮ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ኃላፊነታቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ቀደም ሲል ከሊባኖስና ከኩዌት የሠራተኛ ማኅበራት ጋር ተመሳሳይ ስምምነት መደረጉን አስታውሰው፤ በቀጣይነትም ከደቡብ ሱዳን ሠራተኛ ማኅበር ጋር ተመሳሳይ ስምምነት ለማድረግ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች መጠናቀቃቸውን ገልጸዋል፡፡

ስምምነቱን በሌሎችም ሀገራት የማስፋት ፍላጎት መኖሩን ጠቅሰው፤ በአንዳንድ ሀገራት የሠራተኛ ማኅበር አለመኖርና ማኅበር ቢኖርም የዓለም አቀፉ ሠራተኛ




ማኅበር አባል አለመሆናቸው ተግዳሮት እንደሆነ አመልክተዋል፡፡

የሶማሊያ ሠራተኛ ማኅበራት ኮንፌዴሬሽን ዋና ፀሐፊ ኦማር ፋሩክ ኦስማን በበኩላቸው፤ ስደተኞች የተሻለ ኑሮ ፍለጋ ከአንድ ሀገር ወደ ሌላ ሀገር በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ሕልፈተ ሕይወትን ጨምሮ ለተለያዩ ችግሮች ይጋለጣሉ፡፡

የኢትዮጵያና የሶማሊያ ሠራተኛ ማኅበራት ስምምነት የሁለቱ ሀገራት ዜጎችንና ሌሎችንም ስደተኞች ደህንነት በማስጠበቅ በኩል ጉልህ ሚና ይኖረዋል ብለዋል፡፡

ስደተኞች ለሀገራት ኢኮኖሚና ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ የማይተካ አስተዋጽኦ እንዳላቸው ጠቅሰው፤ በሚኖሩባቸው ሀገራት ሰብዓዊ ክብራቸውን በሚመጥን ክብርና ደህንነት እንዲንቀሳቀሱ ተገቢው የሕግ ከለላና ጥበቃ ሊደረግላቸው እንደሚገባ ጠቅሰዋል፡፡

በዓለም አቀፉ የሠራተኞች ድርጅት (አይኤልኦ) የአፍሪካ ቀንድ አስተባባሪ አሌክሲዮ ሙሲንዶ እንዳሉት ደግሞ፤ የኢትዮጵያ እና ሶማሊያ ሠራተኛ ማኅበራት ፌዴሬሽን ስምምነት በስደተኛ ሠራተኞች ላይ የሚደርስን መገለልና ጥቃት የሚቀርፍና የሠራተኛን ደህንነት የሚያስጠብቅ ነው።

የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ዜጎች ወደ መካከለኛው ምሥራቅ እና ወደ ሌሎችም ሀገራት በሚጓዙበት ወቅት የተለያዩ እንግልቶችን እያስተናገዱ መሆኑን ጠቅሰው፤ ከኢትዮጵያ እና ሶማሊያ በተጨማሪ ሌሎችም ሀገራት በጋራ እንዲሠሩ ግፊት እያደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

በኢትዮጵያ ከ250 ሺህ በላይ ሶማሊያውያን ስደተኞች፣ በሶማሊያ ደግሞ ከ35 ሺ በላይ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች እንዳሉ የተገለጸ ሲሆን፤ በዓለም አቀፉ የሠራተኞች ድርጅት አስተባባሪነት የተፈረመው የሁለቱ ሀገራት ሠራተኛ ማኅበራት ስምምነት በሠራተኞች ደህንነት ዙሪያ ትብብር፣ ጥበቃ እና ሌሎች ሥራዎችን በጋራ ለመሥራት እንደሚያስችል ተጠቁሟል፡፡

# በዓሉ ሲከበር ለጽንፈኞች አጀንዳ በር መክፈት አይገባም

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- የመስቀል ደመራ በዓልን ሲከበር ለጽንፈኞች አጀንዳ በር መክፈት እንደማይገባ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰላምና ፀጥታ ቢሮ ገለጸ፡፡

በአዲስ አበባ የሃይማኖት ተቋማት ጉባዔና የአዲስ አበባ ከተማ የሰላምና ፀጥታ ቢሮ አዘጋጅነት ትናንት የ2016 ዓ.ም የመስቀል ደመራ በዓል አከባበርን በተመለከተ ውይይት ተካሂዷል።

በውይይቱ ወቅት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰላምና ፀጥታ ቢሮ ኃላፊ ሊዲያ ግርማ፤ በበዓሉ ላይ ለሕግ አስከባሪ አካላት ተገዥ የማይሆኑና የሚፈልጉትን አጀንዳ ለመፈጸም ለሚጥሩ ጽንፈኞች በር መክፈት አይገባም ብለዋል።

በዓሉን ስናከብር ሃይማኖታዊ ትውፊቱን በጠበቀና የሕዝቦችን አንድነት፣ መተባበርንና ወንድማማችነት በሚገልጽ መልኩ መሆን አለበት ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

እንደ ኃላፊዋ ገለጻ፤ በዓሉን በሰላም በማክበር ዜጎች በሰላም ወጥተው የሚገቡበትን ሁኔታ ለመፍጠር ከጸጥታ አካላት ጋር በትብብር መሥራት ያስፈልጋል።

አሁን የገጠመንን ችግር ልንፈታ የምንችለው በጋራ ነው፤ የሃይማኖት ተቋማት ይበልጥ ስለሰላም መስበክና ጥፋተኞችን መገሰጽ ይኖርባቸዋል ብለዋል።



**ሊዲያ ግርማ፤**

የሃይማኖት ተቋማት የፖለቲካ አጀንዳ ማራመጃ መሆን እንደሌለባቸውና በየእምነት ተቋማት ተሰግስገው የፖለቲካ ዓላማቸውን ለማሳካት የሚጥሩትን ለሕግ አሳልፎ መስጠት እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡

የአዲስ አበባ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ዋና ጸሐፊ መጋቢ ታምራት አበጋዝ በበኩላቸው እንደገለፁት፤ የመስቀል ደመራ በዓል ሃይማኖታዊ እሴቱን በጠበቀና ሰላማዊ በሆነ መንገድ እንዲከበር ኅብረተሰቡ የበኩሉን ድርሻ ሊወጣ ይገባል።

በዓሉ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ከሚከበሩ የአደባባይ በዓላት አንዱ ነው፤ በዓሉ በዩኔስኮ የተመዘገበ በመሆኑ የኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን የዓለም ቅርስ በመሆኑ በተረጋጋ መንፈስ በማክበር ለሀገር የሚተርፍ ተግባር ማከናወን እንደሚገባ ዋና ጸሐፊው ጠቁመዋል።

አንዳንድ አካላት የአደባባይ በዓላትን በመጠቀም እኩይ ተግባራትን ለማከናወን ጥረት እንደሚያደርጉ የጠቆሙት ዋና ጸሐፊው፤ ሕዝቡ ትዕግስት በተሞላበት ስሜት በዓሉን በደማቅ ሁኔታ ማክበር እንዳለበት አስገንዝበዋል።

ምዕመናኑ በዓሉ እንዴት መከበር እንደአለበት በብፁዕ አባቶች የተላለፈውን መልዕክት ተቀብሎ ተግባራዊ ማድረግ እንዳለበት ያነሱት መጋቢ ታምራት፤ የሃይማኖቱ ተከታዮች በዓሉን ሲያከብሩ አብሮነትን በሚያጎለብት መልኩ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

የውይይቱ ተሳታፊዎች በበኩላቸው ክብረ-በዓሉ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የመረጃ ክፍተት እንዳይኖርና መንግሥት ጥብቅ ቁጥጥር እንዲያደርግ ጥያቄ አቅርበዋል፡፡

በውይይቱ ላይ የተለያዩ አድባራትና ገዳማት አስተዳዳሪዎች፣ በየደረጃው ያሉ የሃይማኖት አባቶችና የከተማ አስተዳደሩ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ተሳትፈዋል፡፡

# «አረንጓዴ ዐሻራ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ሞተር ነው ሲሉ የሲዳማ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ደስታ ሌዳሞ ተናገሩ፡፡ ርዕሰ መስተዳድር አቶ ደስታ አረንጓዴ ዐሻራን በማስመልከት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የአረንጓዴ ዐሻራ እንደ ሀገርም ሆነ እንደ ክልል ፈርጀ ብዙ ጥቅም ያስገኛል፡፡ የአፈር መሸርሸርን በመከላከል፣ ፍራፍሬዎችን በማልማት፣ ማር በማነብና እንስሳትን በማድለብ የምርታማነታችንና የዕድገታችን ሞተር መሆኑ እሙን ነው፡፡

በአረንጓዴ ዐሻራ ሁሉም የሀገሪቱና የክልሉ አካባቢዎች አረንጓዴ ሲለብሱ ምርታማነት እያደገ ይሄዳል፣ ዜጎች ንብ በማነብና እንስሳትን በማድለብ ተጨማሪ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡ ዜጎች ፍራፍሬዎችን በየአካባቢያቸው በተመጣጣኝ ዋጋ የሚያገኙበትን ሁኔታ ይፈጥራል ያሉት አቶ ደስታ፤ በጥቅሉ ሲታይ የአረንጓዴ ዐሻራ ሥራዎቻችን ኢኮኖሚ ፋይዳቸው ፈርጀ ብዙ ነው ብለዋል፡፡

በሲዳማ ክልል የአረንጓዴ ዐሻራ መተግበር ከጀመረ አንስቶ እስካሁን ድረስ ከአንድ ቢሊዮን በላይ ችግኞች መተከላቸውን ገልጸው፤ እነዚህ ችግኞች የክልሉን የተራቆቱ አካባቢዎች በደን ከመሸፈን ባሻገር ኢኮኖሚያዊ ጥቅምም እያስገኙ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ በክልሉ በክረምት ወቅት ከ300 ሚሊዮን በላይ ችግኞች መተከላቸውን አውስተው፤ በችግኝ ተከላ ወቅት ኅብረተሰቡ ያሳየው ተሳትፎ ለዕቅዱ መሳካት ከፍተኛ ሚና መጫወቱን ነው የተናገሩት፡፡ በቀጣይ ወራትም እነዚህ የተተከሉ ችግኞችን በመንከባከብ ረገድም ኅብረተሰቡ የሚጠበቅበትን ሚና እንዲወጣ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

በመጪው ዓመትም ከ300 ሚሊዮን በላይ ችግኞችን ለመትከል ከወዲሁ ዝግጅት ጀምረናል ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ ለዚህም ከወዲሁ ለመጪው ክረምት የችግኝ ዝግጅት እያደረግን ነው፡፡ የሲዳማ ክልል አብዛኛው አካባቢ በደን የተሸፈነ፣ በእንሰት፣ ቡናና አቮካዶ በብዛት የሚገኙበት በመሆኑ እነዚህን በመንከባከብና በመጠበቅ ላይ ትኩረት ተደርጎ እንደሚሠራ አስገንዝበዋል፡፡

በክልሉ የተተከሉትን ችግኞች ከመንከባከብ ጎን ለጎንም እያንዳንዱ ሰው ባለው ክፍት ቦታና በጓሮው ውስጥ በገበያ ላይ ከፍተኛ ተፈላጊነት ያላቸውን የፍራፍሬና ሌሎች ችግኞችን በመትከል ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነቱን ለማሳደግ ይሠራል ሲሉ አቶ ደስታ ጠቁመዋል፡፡ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አነሳሽነት በየዓመቱ በክረምት ወቅት እየተካሄደ የሚገኘው የአረንጓዴ ዐሻራ የችግኝ ተከላ መርሐ ግብሮች የሀገሪቱን የአረንጓዴ እጽዋት ሽፋንን እንዳሳደገ፣ የአየር ንብረት ለውጥ እየተከላከለ እና የሰዎች ሕይወት ላይ ለውጥ እያመጣ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ።

# «የመከላከያ ሠራዊት ሥነ ልቦና ግንባታ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

እድገት ከክቡር ዘበኛ ጀምሮ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረከተ እና አንጋፋ ሀገር ወዳድ ሙዚቀኞችን ያፈራ መሆኑን የገለፁት ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ፤ የሠራዊቱን ሞራል ከፍ በማድረግ ሥራዎቹን በሁሉም አካባቢዎች አዝናኝ እና አስተማሪ በሆነ አግባብ በማቅረብ የሠራዊታችን የግንባታ ማዕከል ሆኖ እየሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

የሚዲያ ክፍሉ ዳይሬክቶሬት እንዲሁም የግንባታ ሠነዶች ዝግጅት እና ሥልጠና ሥራዎች አስፈላጊ ጽሑፍ በማዘጋጀት በየትኛውም ቦታ በመገኘት የሠራዊቱን ሁለንተናዊ የግዳጅ አፈፃፀም፣ ከኅብረተሰቡ ጋር ያለውን መልካም ዝምድና፣ ለሀገር ሠላም እና ልማት እያበረከተ ያለውን አስተዋፅኦ እንዲሁም ሌሎች ሥራዎችን በመዘገብ ውጤታማ ሥራ መሥራቱን እና በቀጣይም መሟላት የሚገባውን በማሟላት ከዚህ በላይ መሥራት እንዳለበት ጠቁመዋል።

መቻል የመከላከያ ስፖርት ክለብም አንጋፋ እና ብርቅዬ ስፖርተኞችን ለሀገር ያበረከት ሀገራቸውን ወክለው በዓለም አደባባይ ሠንደቅ ዓላማችንን ከፍ ያደረጉ ምርጥ ስፖርተኞችን ያፈራ እና ለሀገራችን የስፖርት ዕድገት አሁንም ድረስ ከፍተኛአስተዋፅኦ እያበረከተ የሚገኝ መሆኑን ተናግረዋል።

የመከላከያ ሥነ ልቦና ዋና ዳይሬክቶሬት ሠፉፊ ለሠራዊቱ ወሳኝ እና አስፈላጊ ሥራዎች መሥራቱን ገልፀው በቀጣይም ክፍሉን ይበልጥ ለማሳደግ አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ እንደሚያደርጉ ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ አረጋግጠዋል።

የመከላከያ ሠራዊት የሥነልቦና ግንባታ ዋና ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ሜጀር ጀኔራል እንዳልካቸው ወልደኪዳን በበኩላቸው የዳይሬክቶሬቱ ዋነኛ ዓላማ የሠራዊቱን ሥነ ልቦናዊ ዝግጅት ማረጋገጥ መሆኑን ገልጸዋል።

በዳይሬክቶሬቱ ውስጥ ሲማሩ የቆዩ በአየር ኃይልና በኤይር ፎርስ ክፍለጦር ለአራት ወራት ሲሰለጥኑ የቆዩ የክብር ዘቦች አባላት በትናንትናው ዕለት ተመርቀዋል፡፡

በተያያዘ ዜናም በሠላም ማስከበር ማዕከል የዓለም አቀፍ ሰላም ማስከበር ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ለመጀመሪያ ጊዜ በሁለተኛ ዲግሪ ያሰለጠናቸውን ከፍተኛ ወታደራዊ መኮንኖች ትናንት አስመርቋል፡፡

በምርቃት ሥነ-ሥርዓቱ ላይ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ወታደራዊ አማካሪ እና የተኩስ አመራር ኃላፊ ሌተናል ጀኔራል አለምሸት ደግፌ፣ የሰላም ማስከበር ማዕከል ኃላፊ ሜጀር ጀኔራል አዳምነህ መንግስቴ፣ የዓለም አቀፍ ሰላም ማስከበር ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት አዛዥ ኮሎኔል ደመቀ መንግሥቱ፣ በኢትዮጵያ የጃፓን አምባሳደር ኢቶ ታካኮ፣ ወታደራዊ መኮንኖችና ሌሎችም እንግዶች ተገኝተዋል።

ትናንት ከተመረቁ ወታደራዊ መኮንኖች መካከል ከኢትዮጵያ በተጨማሪ የሦስት ጎረቤት ሀገራት ከፍተኛ የጦር መኮንኖችም ይገኙበታል።

ተመራቂዎቹ የስታፍ መኮንንነት፣ የወታደራዊ ታዛቢነት፣ በግጭት ወቅት ሲቪሎችን መከላከል፣ የሲቪል ሚሊተሪ ትስስር፣ የሚሽን ሚዲያ፣ የሎጅስቲክስ የትምህርት ዓይነቶችን ጨምሮ ሌሎች የሰላም እና ግጭት አፈታት ትምህርቶችን መከታተላቸው ተገልጿል።

ከፍተኛ መኮንኖቹ ትምህርቱን ለሁለት ዓመታት የተከታተሉ ሲሆን ከተመራቂዎች ውስጥ የኬንያ የደቡብ ሱዳን እና የኡጋንዳ ዜጎች ይገኛሉ፡፡

የመከላከያ ሠላም ማስከበር ማዕከል የዓለም አቀፍ ሠላም ማስከበር ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በማስተርስ ደረጃ ከፍተኛ መኮንኖችን ሲያስመርቅ ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲሆን ከዚህ ቀደም በቅድመ ስምሪት አጫጭር ሥልጠናዎችን ሲሰጥ መቆየቱ ይታወቃል፡፡

ማዕከሉ በሠላም እና ግጭት አፈታት በማስተርስ ዲግሪ ሥልጠናውን የሰጠው የተባበሩት መንግሥታት የልማት ድርጅት (ዩ.ኤን.ዲ.ፒ) ባደረገው የቴክኒክ ድጋፍ እና የጃፓን መንግሥት ባደረገው የገንዘብ ድጋፍ መሆኑን አሳውቋል፡፡

# በዓባይ ውሃ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ያለው እ.ኤ.አ በ2015 በተደረሰው የመርሆዎች መግለጫ መሠረት በስኬት ከተከናወነው አራተኛው ዙር የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ሙሌት በኋላ ነው። በዓባይ ውሃ አጠቃቀም ፍትሐዊ እና ምክንያታዊ አጠቃቀም መርህን ማስፈን ብቸኛው አማራጭ ነው ብለዋል፡፡ በዚህ ዙር ውይይት ሀገራቱ በጉዳዮች ዙሪያ መግባባት ላይ ለመድረስ ያላሰለሰ ጥረት እንደሚያደርጉ ያላቸውን እምነት ገልጸዋል።

አያይዘውም በመርሆዎች መግለጫው በተቀመጠው መሠረት በዓባይ ውሃ አጠቃቀም ፍትሐዊ እና ምክንያታዊ አጠቃቀም መርህን ማስፈን ብቸኛው አማራጭ መሆኑን ገልጸዋል። በተጨማሪም ሒደቱ በስኬት እንዲጠናቀቅ ኢትዮጵያ እንደ ከዚህ ቀደሙ ሁሉ በቁርጠኝነት የበኩሏን ሚና እንደምትጫወት አረጋግጠዋል። የግብጽ የውሃ እና መስኖ ሚኒስትር ፕ/ር ሐኒ ሴዊላም እና የሱዳን ተጠባባቂ የውሃ ሚኒስትር ዳውልበይት አብድልረህማን ማንሱር ባሽር በመክፈቻ ንግግሮቻቸው በድርድሩ ሒደት ከስምምነት ላይ ለመድረስ ያላቸውን ፅኑ ተስፋ ገልጸዋል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## ትውልድና ዘመን ተሻጋሪ አርዓያነት ፤

ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ በአዲስ አበባ ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል የተገነባው የመታሰቢያ ሐውልት ባለፈው ማክሰኞ መመረቁን በብዙኃን መገናኛዎች በስፋት ተዘግቦ ስመለከት “መኀልይ መኀልዩ ዘብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ስላሴ...”አልሁና ይህን ዘካሪ መጣጥፍ ከአንድምታና ከተለያዩ ምንጮች አጠናቀርሁ ። ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ በኢትዮጵያ የሥነ-ጽሑፍ ታሪክ ፈር ቀዳጅ ከሆኑት መካከል አንዱ ሲሆኑ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በመሆንም ሀገራቸውን አገልግለዋል ። በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት በተለያዩ የፖለቲካ ኃላፊነቶች በትጋት እና በቁርጠኝነት ያገለገሉት ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ የልዩ ፍርድ ቤት ዳኛም ነበሩ ። ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ በሊግ ኦፍ ኔሽን የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ልዑክ አባል እንደነበሩም የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መረጃ አመልክቷል ። ከ21 በላይ መጽሐፍትንም ደርሰዋል ።

ዶ/ር ታደለ ገድሌ ጸጋየ፤”ደራሲው ዲፕሎማቱ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴና በጥረት የተገኘ ታላቅነታቸው ፤”ባስነበቡን መጣጥፍ ፤ በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ታሪክ ታላቅና ግዙፍ አስተዋጽኦ ያላቸው ደራሲ ፤ ታሪክ አዋቂ ፤ ዲፕሎማት ፤ በቤተ ክህነት ትምህርትና በቋንቋ የተካኑ ፤ ባለቅኔ ፤ ገጣሚ ፤ የዘመናቸውን ዕውቀት የቀሰሙ ምሁር ፤ በአኗኗራቸው በምሳሌነት የሚታዩና ሠርተው የማይደክሙ ኢትዮጵያዊ ናቸው ይሉናል ። እኒህ ሊቅ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ይባላሉ ፡፡

ከአባታቸው ከአቶ ወልደ ሥላሴና ከእናታቸው ወይዘሮ ወለተ ማርያም ዜና የተወለዱት ግንቦት 1 ቀን 1871 ዓ ም በቀድሞ አጠራሩ በመርሐ ቤቴ አውራጃ በታች ቤት ወረዳ ረመሽት ቀበሌ ደን አቦ ገዳም በተባለ ሥፍራ ሲሆን ያረፉት ደግሞ መስከረም 9 ቀን 1931 ዓም እንግሊዝ አገር ባዝ በተባለው ቦታ በስደት ላይ እያሉ ነው ። ብላቴን ጌታ ኅሩይ ለቤተ ሰቦቻቸው የመጀመሪያ ልጅ ሲሆኑ አባትና እናታቸው ከእርሳቸው ቀጥሎ በተከታታይ ሁለት ሴት ልጆችን ወልደዋል ።ሲወለዱ የወጣላቸው ስም ገብረ መስቀል የሚል ነው ።ምናልባትም የክርስትና ስማቸው ሊሆን ይችላል።ይህም የመስቀል ባሪያ አገልጋይ ፤ ጽሙድ እንደማለት ነው፡፡

ከቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ የተወለዱበትን የደን አቦ ገዳም ቤተ ክርስቲያን ያሠሩትና የበላይ ጠባቂ ሆነው ያስተዳድሩት የነበሩት የዳግማዊ ምኒልክ የቀድሞ ሁለተኛ ሚስታቸው ወይዘሮ ባፈና ነበሩ።በዚህ ረገድ ወይዘሮ ባፈና የብላቴን ጌታ ኅሩይን አባት አቶ ገብረ ሥላሴን የገዳሙ አስተዳዳሪና የቤተ ርስት ሹም አድርገው አስቀምጠዋቸው ነበር።አቶ ገብረ ሥላሴም ሸዋ ውስጥ በመርሐ ቤቴ አገሪት በተባለች ቦታ መንዝ ውስጥ ቢያድጉም ቤተ ሰቦቻቸው ከወሎ አማራ ሳይንት የመጡ ናቸው።እናም አባታቸው እናታቸውን ያገቡት የ40 ዓመት ጎልማሳ እያሉ ሲሆን ወይዘሮ አመተ ማርያም ዜና በመንዝ ጠል በተባለው ቦታ የማደሬ ቤተሰብ ተወላጅ ናቸው።ከሸዋው ንጉሥ ከሣህለ ሥላሴ እናት ከወይዘሮ ዘነበወርቅ ጋርም ወይዘሮ አመተ ማርያም ይዛመዳሉ፡፡

ከዕለታት አንድ ቀን አቶ ወልደ ሥላሴ የገዳሙን ካህናትና ዲያቆናት ግብር ለማብላት ዝግጅት ባደረጉ ጊዜ የገዳሙ አለቃ ለጊዜው በቦታው ላይ ባለመገኘታቸው ካህናቱ በረሃብ ይንገላታሉ።ይህንን ያስተዋሉት የቤተ ርስቱ ሹም አቶ ወልደ ሥላሴ የገዳሙ አለቃ የድርሻቸው ምግብ ተቀምጦላቸው አገልጋይ ካህናቱ እንዲመገቡ ያደርጋሉ።በመሃል የደብሩ አለቃ ድግስ እየተበላና እየተጠጣ ከች ይላሉ።በዚህ ጊዜ በቁጣ ንግግር «በቃ የገዳሙ ባህል ፈረሰ።እንዴት እኔ ሳልመጣ ሌሎቻችሁ ማእድ ትቆርሳላችሁ? ይህንን የሚያደርግ መቼም ወልደ ሥላሴ እንጂ ሌላ አይደለም።ወይዘሮ ባፈና ያልተማረ ጨዋ ሾመው ይኸው ይጫወትብናል » በማለት ከተናገሩ በኋላ ወደ ካህናቱ ዞረው «እንዴትስ በሌለሁበት ግብር ትበላላችሁ?» በማለት ይገስጹዋቸዋል፡፡

አቶ ወልደ ሥላሴም ጠቡንና ክርክሩን ያበረድሁ መስሏቸው «ካህናቱ በደጅ ቆመው በፀሐይ ሙቀት ስለተጉላሉ እርስዎም እንደደረሱበት ገብተው ግብር እንዲቀመጡ ያደረግሁ እኔ ነኝ።የእርስዎም ፋንታ በክብር ተቀምጦዋል።እና እባክዎን ይቀመጡና ይጋበዙልን » በማለት በትሕትና ይለምኗቸዋል።የደብሩ አለቃ ግና ባለመረጋጋት ነገሩን አክርረው «ካልተማረ መሐይም ምን ይጠበቃል? ቆይ ለወይዘሮ ባፈና ነግሬ ከሹመትህ ባላሽርህ እኔ ሰው አይደለሁም» ብለው የተቀመጠላቸውን ምግብ መኮምኮምና ጠላቸውንም መጎንጨት ይጀምራሉ።አቶ ወልደ ሥላሴም በደብሩ አለቃ ንግግር ተበሳጭተው ነበርና «መቼም እኔ ከእንግዲህ ተምሬ አልደርስም።ልጄ እንደኔ እንዳይሰደብ እርሱን ማስተማር አለብኝ » በማለት ወሰኑ ፡፡

በዚህ ዓይነት ልጃቸው ገብረ መስቀል የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ለመማር እንዲችሉ በሰባት ዓመታቸው አባታቸው መርሐ ቤቴ ሥላሴ ወስደው ከነስንቃቸው ጭምር ለመምህራኑ አስረከበዋቸዋል። የመጀመሪያው መምህራቸውም ደብተራ ሥነ ጊዮርጊስ ይባላሉ።በሁለት ዓመት ውስጥ በግእዝ ለማንበብና ዳዊት ለመድገም ችለዋል።ከችሎታቸው የተነሣም ኅሩይ ለአባታቸው ጠቃሚ ልጅ ሆነው ታዩ።በዚህም ልጃቸው በበለጠ እንዲማር ከፍተኛ ፍላጎት ስለአደረባቸው ኅሩይ 10 ዓመት ሲሆናቸው በዘመኑ ታላቅ ወደነበረው ስሬ መድኃኔዓለም መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ወስደው አስገቡዋቸው።በዚህ ዓይነት የቤተ ክህነቱን ልዩ ልዩ ከፍተኛ ትምህርት ሲማሩ ቆይተው በዜማ ትምህርት እስከመምህርነት ደረጃ አጠናቀቁ።የመጻፍንም ልምድ ከተለያዩ ዕፀዋትና ጥላሸት ቀለም በጥብጠው ከሚገለብጡት ከብራና መጻሕፍት ቀለማት ለማወቅ ችለዋል፡፡

በዚህ ዓይነት አባትና ልጅ አብረው ለሁለት ዓመታት ከቆዩ በኋላ ወልደ ሥላሴ ወደ ታላቁ ገዳም ደብረ ሊባኖስ ሄደው በምንኩስና መኖር ጀመሩ።በኋላ በ53 ዓመታቸው እንደገና ወደ ልጃቸው ዘንድ ተመለሱ።ወላጅ እናታቸው ልጃቸውን ኅሩይን አንድ ጊዜ እስከሚማሩበት ቦታ ድረስ ሄደው ቢጠይቋቸውም በኋላ ሊያገኙዋቸው አልቻሉም፤ ጠፉባቸው።የአባ ወልደ ሥላሴም ጤና እየታወከ በመሄዱ እንደገና ወደ ደብረ ሊባኖስ ወርደው ጸበል ሲጠመቁ ከቆዩ በኋላ ልክ ኅሩይ 13 ዓመት ሲሞላቸው ዐረፉና እዚያው ደብረ ሊባኖስ ተቀበሩ።ኅሩይ የአባታቸውን መቃብር ለማየት ወደ ደብረ ሊባኖስ በሄዱበት ሰዓት የአባታቸውን የንስሐ አባት አግኝተው ያባታቸውን ኑዛዜ ነገሩዋቸው።ይኸውም ለኅሩይ በዚህ ዓለም ላይ ያለው ሀብት ትምህርት ስለሆነ ጠንክሮ ይማር፤ የማወርሰው ሀብትና ንብረት ስለሌለኝ ወደ ትውልድ ሀገራችን እንዳይመለስ የሚል ነው።ከአባታቸው በተቀበሉት ኑዛዜ መሠረትም ኅሩይ የቤተ ክህነቱን ልዩ ልዩ የትምህርት ዓይነት አጠናቅቀው በዜማ ትምህርት እስከ መምህርነት ደረጃ ደርሰዋል።ከዚህ ደረጃ ላይ የደረሱትም ብዙ ችግሮችን በመቋቋም ነው፡፡

ወደ አዲስ አበባ እንጦጦ ራጉኤል ደብር መጥተው የመጻሕፍትን ትርጓሜ በዘመኑ ከነበሩ ሊቃውንት ዘንድ በመማር አጠናቀቁ። በእንጦጦ የነበሩ አንድ ሊቅ መምህራቸው ስማቸውን በጠየቋቸው ጊዜ ገብረ መስቀል መሆኑን ተናግረዋል።ሊቁም «ጎንደር በነበርሁ ጊዜ አስተማሪየ ስለወደዱኝ ኅሩይ እያሉ ይጠሩኝ ነበር።ወደ አዲስ አበባ ስመለስ ግን በቀድሞ ስሜ እየተጠራሁ ነኝ።ስለዚህ አንተ የቀለም ቀንድ ስለሆንህና በምግባርህም የተወደድህ በመሆንህ ኅሩይ የተባለውን ስሜን ትጠራበት ዘንድ ሸልሜሃለሁ» ይሏቸዋል፡፡በ1901 የራጉኤል የደብር አለቃና የዳግማዊ ዓፄ ምኒልክ የጽሕፈት ሚኒስትር ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ወልደ አረጋይ ስለ ኅሩይ ዝና ከደብሩ ሊቃውንት ስለሰሙ ኅሩይን በጣም አቀረ ቧቸው ። ኅሩይንና ጓደኞቻቸውን ፤ በምሁርነታቸውና በብሩህነታቸው ፤ በትጋታቸው ፤ በታማኝነታቸውና በመልካም ሥነ ምግባራቸው ፈጽሞ ወደዷቸው፤ አከበሯቸውም፡፡

ከዳግማዊ ምኒልክ ፊት አቅርበውም አሸለ ሟቸው። ዳግማዊ ምኒልክም የኅሩይን ልጅነት አይተው« እንዲያው ለቁጥር ማሙያ ከሊቃውንቱ ጋር አቅርበህ አሸለምከው እንጂ ገና ልጅ ነው። ምን ሊያውቅ ይችላል ? ቢሏቸው ጸሐፊ ትእዛዝም ‘ጃንሆይ እድሜው ነው እንጂ እውቀቱ ትልቅና ዘሊቅ ነው ’ ብለው በመመስከር ንጉሡ ነገሥቱን አሳመኗቸው።ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ኅሩይ በቤተ ክህነቱና በቤተ መንግሥቱ እየታወቁና እየገነኑ ስለመጡ ተወዳጅነታቸው በሁሉም ሰው ዘንድ ታወቀ፡፡

ብላቴን ጌታ ኅሩይ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን የታወቁ ፖለቲከኛና በቤተክህነቱም ከፍተኛ ምሁር የነበሩ ሰው ናቸው።ኅሩይ በጥንታዊና ዘመናዊ ትምህርት የተቀረጹ ሰው ነበሩ።ለዘመናዊ ትምህርትም ከአላቸው ጉጉት የተነሣ በኋላ ላይ አዲስ አበባ ስዊድን ሚሽን ትምህርት ቤት ገብተው የውጭ አገር ቋንቋ ማለት እንግሊዝኛ መማራቸው ስለውጭ ሀገራት የነበራቸውን አስተሳሰባቸውን በበለጠ አሳድጎላቸዋል። በተጨማሪም ከዶክተር ቻርለስ ማርቲን ወይም ከሐኪም ወርቅነህ ጋር ግንኙነት መመሥረታቸው ስለውጭ ሀገር ያላቸውን ዕውቀት ከፍ አድርጎላቸዋል።ከእንግሊዝኛ በተጨማሪ በዐረብኛም የተለያዩ የትምህርት ዓይነቶችን ለመማር ጥረት አድርገዋል፡፡

ነገር ግን በወቅቱ ኅሩይ እስላም ሆነ የሚለውን አሉባልታ ስለሰሙ የዐረብኛ ትምህርታቸውን ለማቆም ተገድደዋል።ቀጥለው ከፈረንሳይ የከብት ሕክምና ባለሙያዎች ፈረንሳይኛን ለመማር ችለዋል።በተለይ የኅሩይን ዕውቀት በበለጠ ያሳደገላቸው በተደጋጋሚ ወደ ውጭ ሀገራት ሲያደርጉት የነበረው ጉዞ ነው ለማለት ይቻላል።ለአብነትም እኤአ በ1911 ከደጃዝማች በኋላ ልዑል ራስ ካሣ ኃይሉ ጋር በእንግሊዙ ንጉሥ በጆርጅ 5ኛ በዓለ ንግሥ ላይ ለመገኘት መቻላቸውና በተደጋጋሚም ከኢትዮጵያ መንግሥት ልዑካን ጋር እንግሊዝ ሀገር ደርሰው መመለሳቸው ፤ እኤአ በ1949 በመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ዘአሊያንስ ተብለው ይታወቁ የነበሩት የቃልኪዳን (የኅብረት ኃይሎች) ስለአሸነፉ አሜሪካንን እንኳዋን ደስ አለሽ ለማለት ወደዚያው መጓዛቸው ፤ እኤአ በ1920 እና በ1923 ወደ ኢየሩሳሌም ማቅናታቸው ፤ እንደገና እኤአ በ1924 እና 1931 ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጋር ወደ አውሮፓና ወደ ቻይና ደርሰው ለመመለስ በመቻላቸው፤ ለጥቂት ጊዜያትም በጃፓን የኢትዮጵያ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር ሆነው መሥራታቸው ስለውጭ ሀገራት እድገትና ሥልጣኔ ይበልጥ ለማወቅ አስችሏቸዋል፡፡

እኤአ በ1914/15 የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር እንዲሆኑ በር የከፈተላቸው ራሳቸው የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ብለው ስም በአወጡለት መሥሪያ ቤት ዋና ጸሐፊና ኃላፊም ሆነው መሥራታቸው ነው ።እኤአ ከ1916 ጀምሮ የዲሬክተር ጀኔራልነት ማዕረግ አግኝተው አገልግለዋል። እኤአ ከ1920-21 ድረስ ደግሞ የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ምክትል ከንቲባ ሆነው ሠርተዋል።ቀጥሎ በዋና ኃላፊነትና በብላቴን ጌታ ማዕረግ የልዩ ፍርድ ቤት ዳኛ በመሆን አገልግለዋል።ልዩ ፍርድ ቤቱ ይመለከትና ይመረምር የነበረው ርእሰ ጉዳይ የሀገር ውስጥና የውጭ አገር ዜጎችን ክስ ነው።«ብላቴን ጌታ» የሚለው ስመ ማዕረግ ኅሩይ ከሚለው ስማቸው ጋር ተወራራሽነት አለው። ብላቴን ጌታ ኅሩይ እኤአ በ1927 በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዲሬክተር ጀኔራል ሆነው ተሾመዋል፡፡

ብላቴን ጌታ ኅሩይ በትዳር ሕይወታቸውም መልካም አርዓያ ስለነበሩ ከባለቤታቸው ወይዘሮ ሐመረ እሸቴ ስድስት ልጆን ወልደዋል።በርካታ የልጅ ልጆችንም አፍርተዋል።ቤተሰባቸውንም በእግዚአብሔር ሕግ መሠረት በፍቅር ይመሩና ያስተዳድሩ ነበር።ሞልቪየር እንደጻፈው ብላቴን ጌታ ኅሩይ በዚያች በድህነታቸው ዘመን ለማግባት የፈለጉት የጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴን ልጅ ነበር።ግን አልፈቀዱላቸውም።ለዚህም ነው ወደ ትውልድ ሀገራቸው ሔደውና ቆንጆይቱን ወይዘሮ ሐመረን አፈላልገው ያገቡት።በድርሰት ረገድ ከ21 በላይ የተደነቁ መጻሕፍትን ደርሰዋል።ሥራዎቻቸው ሁሉ ትሕትናን፤ ትክክለኛነትን፤ ምግባረ ሠናይነትንና ሞራልን ከፍ አድርገው የሚያሳዩ ናቸው፡፡

ብላቴን ጌታ ኅሩይ ከጻፏዋቸው መጻሕፍት ውስጥ ኢትዮጵያና መተማ የዓፄ ዮሐንስ ታሪክ ባጭሩ(1910 ዓ .ም)፤ ወዳጄ ልቤ 1955 ዓ. ም ፤ዳግማዊ ቴዎድሮስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ 1955 ዓ ም፤ የልዕልት ወይዘሮ መነን መንገድ በኢሩሳሌምና በምስር 1915ዓ .ም፤ መጽሐፈ ቅኔ 1918 ዓ .ም፤ ዋዜማ 1926 ዓ .ም፤ በኢትዮጵያ የሚገኙ በግእዝና በአማርኛ ቋንቋ የተጻፉ የመጻሕፍት ካታሎግ 1920፤ የኢትዮጵያ ታሪክ ከንግሥት ሳባ እስከ ታላቁ የዓድዋ ድል 1999 ዓ.ም፤ ድርሳኖች 1983፤ ማኅደረ ብርሃን ሀገረ ጃፓን 1924፤ዓ.ም፤ የብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ታሪክ 1871-1931 ዓ.ም በባሕሩ ዘውዴ የሚሉት ይጠቀሳሉ።ከሥራዎቻቸው ውስጥ አብዛኛቹ በታሪክ፤ በግለ ታሪክ ‹መዝገበ ቃላት፤ በጉዞ ማስታወሻዎችና በልቦለድ ላይ ያተኮሩ ናቸው።የሥነ ጽሑፍ ሥራዎቻቸውም ዓለምአቀፋዊ ዝናን አትርፈ ውላቸዋል፡፡


**ሻሎም ! አሜን ።**

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

# ባስራዕዩ - በሻካራማው መንገድ

**መልካምሥራ አፈወርቅ**



### የተክለኃይማኖት ትዝታዎች

መሀል አዲስ አበባ ሰፈረ - ተክለኃይማኖት። የበርካቶች መገኛ የብዙኃን መኖሪያ። ይህ አካባቢ ሁሉም በአቅሙ ሰርቶ ፣ ለፍቶ ያድርበታል። ዕድሜ ጠገቡ ሰፈር ተሳስበው ፣ ተዋደው የሚኖሩበት ዋርካ ነው ። በዚህ ስፍራ ብዘዎች በላባቸው ወዝ፣ በጉልበታቸው ድካም ይኖራሉ።

እዮብ ተወልደመድህን በዚህ ሰፈር አፈር ፈጭተው ፣ ውሃ ተራጭተው ካደጉ የአካባቢው ፍሬዎች አንዱ ነው። ተክለኃይማኖት ለእዮብ የልጅነት ታሪኩ ብቻ አይደለም ። ከወጣትነት ዕድ ሜው ተሻግሮ ጎልማሳነቱን በፍቅር ኖሮበታል። ሥራ ይዞ ገንዘብ ቆጥሮበታል። ልጅ ወልዶ ስሞበታል።

እዮብ በሰፈሩ ኑሮን ለማሸነፍ፣ አልሆነው የለም። ራሱን ለመቻል ፣ ከማማው ከፍታ ወጥ ቷል ። መልሶ ደግሞ ከዝቅታው ታይቷል ። ሁሌም ወድቆ ለመነሳት ሲሞክር ተንገዳግዶ አይቀርም። ሕይወትን ከሀሁ ፣ መጀመር ከዳዴ መቀጠል ያውቅበታል። ለእሱ ደስታ ከመከራ ብርቁ አይደለም። በለስላሳና ሻካራ የሕይወት ጎዳናዎች ደጋግሞ ተመላልሷል።

ተክለኃይማኖት ለእዮብ የዝምታው መደበቂያ ነበር። ልጅነቱን በብቸኝነት ገፍቶበታል። ብሶቱን ከራሱ አውግቶበታል። ሰፈሩ ለእሱ፣ እሱም ለሰፈሩ ልዩ መገለጫዎች ናቸው። በዚህ ሥፍራ ተወዶ ተከብሯል፣ አግኝቶ አጥቷል ፣ ወድቆ ተነስቷል። እዮብ ስለሰፈሩ ለማውራት ቃላት የለውም። ተክለኃይማኖት ለእሱ ታሪኩ ነው። ሕይወትን ያነበበበት፣ ኑሮን ያየበት፣ የልብ መስታወት።

በዚህ ሰፈር ቀኝ እጅ የሆነላቸው በርካቶች ስሙን በበጎ ሲያነሱት ውለዋል።ዕንባ የታበሰላቸው፣ ጎዶሎ የሞላላቸው ፣ መርቀው፣ አመስግነው አይጠግቡትም። ዓላማው ከዓላማቸው ያልገጠመ ጥቂቶች ደግሞ ስሜቱን ሊነጥቁ ፣ ተስፋውን ሊያ መክኑ ሞክረዋል ። እሱ ግን ከዕቅዱ ሸሽቶ፣ ከሃሳቡ ተናጥቦ አያውቅም ። ሁሌም ዓላማው የሰፋ፣ መንገዱ የራቀ ነው። ህልሙን ያሳካል ፣ ጅምሩን ይጨርሳል።

### ልጅነትን ወደኋላ ...

ለጥንዶቹ የመጀመሪያ ወንድ ልጅ የሆነው እዮብ የልጅነቱ የመጀመሪያ ዓመታት በፍቅር የተሞሉ ነበሩ። በእነዚህ ጊዜያት ከወላጆቹ ፍቅር እንክብካቤን አላጣም። እሱም እንደ እኩዮቹ በቤተሰብ እቅፍ ውሎ አደረ። ይህ እውነታ ግን ብዙ አልዘለቀም። የአባቱ በሥራ ምክንያት ከቤት መራቅ ታሪኩን ሊቀይረው ግድ አለ።

እዮብ አባቱን ተከትሎ ወደ ምዕራብ ሐረርጌ አሰበ ተፈሪ አመራ። የዛኔ አስራ አንደኛ ዓመት ዕድሜውን መጀመሩ ነበር። አጋጣሚው ከእናቱና ከታናናሽ ወንድሞቹ የለየው ብላቴና ውሎ አድሮ የሰው ሀገር እንግድነትን ተላመደ። የአባቱ የሥራ ባህሪ ከቤት የሚያውል አልሆነም ። ማለዳ ወጥተው ምሽት የሚገቡበት ጊዜ ይበረክታል።

የአባቱ እንደ ልብ ከቤት አለመገኘት እያደር የእዮብን ብቸኝነት አባሰው። ትኩረት በሚያሻው ዕድሜ ፍቅር ማጣቱ ትንሹን ልጅ ምርጫ አሳጣው። እያደር አካባቢውን ይመስል ያዘ። ቤት እየጠበቀ ከሱቅ ሥራ መዋል ግዴታው ሆነ።ትምህርት ቢጀምርም በቂ ዕውቀት አልጨበጠም።የት ነህ? የት ዋልክ ? የሚል ፈቃጅ ከጎኑ አጣ። ናፍቆት በአንጀቱ እየተላወሰ፣ የወላጅ ፍቅር በዓይኑ እየዞረ ግዴታውን ተቀበለ።

ያለ ታዛቢና ተቆጪ የሚያድርባቸው ጊዜያት በረከቱ።በትልቁ ቤት ብቻውን ውሎ ማደር ፣ ሰንብቶ መክረም ልምዱ ሆነ። የራሱ አዛዥ አለቃ ለመሆን በሩ ሰፋለት። «ሁሉ በእጁ ሁሉ በደጁ» የሆነው ታዳጊ ያለአንዳች ከልካይ ሰፊውን ሜዳ ናኘበት፣ ቦረቀበት።

ቀናት አልፈው ቀናት ተተኩ።የእዮብ ባህሪ መለወጥ፣ መቀየር ጀመረ። ከሱቅ መዋሉ ከገንዘብ አስተዋወቀው ። ጣፋጭ መብላት መጣጣት አዘወተረ።ልጅነቱ እሳትን ከውሃ አላስለየውም። የሚጠቅም የሚጎዳውን ሳይመርጥ ባሻው መንገድ ተራመደ። «ተው ፣ እረፍ ፣ አደብ ግዛ» የሚል ተቆጪ አጣ። የእሱ ጊዜ «ልጅነቴ ማርና ወተቴ» የሚባልለት አልሆነም። ይህ ዕድሜ ለእዮብ ማንነት የማይፈዝ ማህተም አሳርፎ እንደዋዛ አለፈ።

### አፍላነት

ወቅቱ በመላው ሀገሪቱ አዲስ የለውጥ እሳት የተቀጣጠለበት ነበር ።ወርሀ ግንቦት 1983 ዓ.ም። ይህ እውነታ እዮብን ከአሰበ ተፈሪ ወደ አዲስአበባ እንዲመለስ አስገደደው። ባደገበት በኖረበት አካባቢ ሁኔታዎች ተቀየሩ። ለውጡን ተከትሎ የመጣው እንቅስቃሴ እዮብን ከክፉ ዓይኖች ጣለው። ሰበብ ፈልገው የሚያሳድዱት፣ የሚከተሉት በረከቱ። ይህ እውነታ በነፃነት ላደገው ልጅ ፈተና ሆነ።

ያን ጊዜ ሰዎች ሲሮጡ «ሌባ፣ቀማኛ፣» ተብለው የሚገደሉበት፣ አንዳንዶች በየሰበቡ ኃይላቸውን የሚያሳዩበት ነበር። እንዲህ አይነቱ ሀቅ ለፈጣኑ እዮብ ፈተና ሆነ። «እናውቀዋለን» ባሉ የቅርብ ዘመዶቹ ተሳደደ።ጉልበታሙ ኃይለኛው ወጣት በቀላሉ እጅ አልሰጠም።ቀን እስኪያልፍ ቀን ጠበቀ። ክፉ ጊዜውን ሸሽግ ፣ ድበቅ ብሎ አሳለፈ ።ያም ሆኖ ነገሮችን አልረሳም። የበደሉትን አልዘነጋም።

ውሎ አድሮ ነገሮች ተረጋጉ። እዮብ ከቤተሰቡ ውሎ እንዳደረ ትምህርት ቤት የመግባት ዕድል ገጠመው። እንደ እኩዮቹ ደብተር ይዞ፣ ሰአት ጠብቆ ትምህርት ቤት ተመላለሰ። ይህ ጊዜ ብዙ ላየው ትንሹ እዮብ የተመቸ አልሆነም። ቀድሞ የጨበጠው ዕውቀት የለም ። በትምህርት ከእኩዮቹ እኩል መራመድ አልቻለም። እንደተማሪ ክፍል አለመግባቱ ደግሞ ስንፍናውን አጋለጠ።

እዮብ ሰባተኛና ስምንተኛ ክፍል ደጋግሞ ወደቀ። እንዲያም ሆኖ በሚማርበት የፈለገ ዮርዳኖስ ትምህርት ቤት ባህሪውን ለመለወጥ ትንሽ ጭላንጭል አላጣም። ቆም ብሎ የሚያስብበት አፍታ ቢያገኝ ስለማንነቱ ይጨነቅ ፣ ያስብ ያዘ ።

ከዚህ በኋላ የነበሩት ጊዜያት ለእዮብ ማስተዋልን ጨመሩለት።ለትምህርቱ ልዩ ትኩረት ሰጠ።ትናንት እንደዋዛ የባከኑትን ጊዜያት በጥናት ተካቸው። ጎበዝ ተማሪ ሆነ። ጊዜው ደርሶ ዳግም ስምንተኛ ክፍልን ተፈተነ። ነባር ታሪኩ መልኩን ለወጠ ፣ በጥሩ ውጤት ማለፉን አወቀ። በአዲሱ ዓመት የዘጠነኛ ክፍል ትምህርቱ መልካም ሆነለት።

አሁን እዮብ ዕድሜ እየጨመረ ፣ ወጣትነቱ እያበበ ነው።ይህ ጊዜ ለእሱ የጎረምሳነት ኃይል ብቻ አልሆነም። በእናቱ ቤት ላቅ ያለ የኑሮ ችግር ስለመኖሩ እያስተዋለ ነው። ቀድሞ የነበረው የቤተሰብ መለያየት በልጆች ሕይወት ጫና አሳድሯል።ይህን አሳምሮ የሚያውቀው እዮብ ስለ ሁሉም አስትንፋስ አጥብቆ እያሰበ ነው።

እዮብ ጎበዝ ከሚባሉት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች አንዱ ሆኗል።ለትምህርቱ የሰጠው ትኩረት ውጤት ደርቦለት ዕውቅናን ችሮታል። ውሎ አድሮ ግን ይህ ጥንካሬው ዕንቅፋት አላጣውም። እሱ በኑሮ ደረጃ ከእኩዮቹ አቻ አልሆነም። ችግር አብዝቶ የሚጎበኘው የእናቱ ጓዳ ፍላጎቱን በወግ አልሞላም።

### ትምህርት - በባዶ ሆድ

አሁን እዮብ ምግብ ከሚበላበት የማይቀ ምስበት ጊዜ በርክቷል። በባዶ ሆድ ትምህርት ይሉትን መቀበል እየከበደው ነው።ይህ ችግር የእሱ ብቻ አይደለም። ከቤት ያሉት እናቱና ወንድሞቹም ይጋሩታል። እህል ባልሻረ አፉ ውሎ ሲገባ ኩርማን እንጀራ አይቆየውም። ከባዱ የሕይወት ምዕራፍ እየፈተነው ፣ መንገዳገድ ይዟል። አሁን በውጉ ለመኖር አንዱን ጥሎ ፣ አንዱን ሊመርጥ ግድ ነው።

እዮብ ፀንቶ ከቆየበት ዓላማ ሊፋታ ጊዜው ደረሰ። ውስጡ ቢያዝንም ምርጫ የለውም።የዘጠኛ ክፍል ትምህርቱን አቋርጦ የቀን ሥራ ፈላለገ ።1988 ዓ.ም። ይህ ወቅት እንደ እዮብ ላሉ አፍላ ወጣቶች ቀላል አልነበረም።ሁሉም ጉዳይ በሰው፣ በዘመድ ነው።ማንም ባሻው ዘው ብሎ ሥራ አይገባም። ለእሱ ሥራው ካልተሳካለት የቤቱ ችግር ይበረ ታል፣ ርሀቡ ይጠናል።

ለሥራ ፈላጊው ወጣት ቀን አልጎደለም።በአንዲት ሴት መልካምነት ከአንድ የእንጨት መሰንጠቂያ ድርጅት እንጀራው ተገኘለት። ቦታው ለቤቱ የቀረበ ነው።ተጨማሪ ወጪ የለውም። ማልዶ ከቤት ሲወጣ ብዙ አይሻም። አንዲት ጉርሻ ከእናቱ ምርቃት ጋር በቂው ነው ። የእዮብ ልብ በደስታ ሞላ።ችግር የፈታውን ቤተሰብ ሊታደግ ነውና ለፈጣሪ ምስጋና ተንበረከከ ።

### ሥራና ሥራ ...

እነሆ እዮብና ሥራ በፊት ለፊት ተገናኙ።አሁን ከዚህ ውሎ የተሻገረ ሌላ ዓላማ የለውም። በዕለተ ሀሙስ የመጀመሪያውን ቀን በሥራ አሳለፈ። ከአንድ ቀን በኋላ አስር ብር ተከፈለው።የእዮብ ደስታ ልዩ ነበር።አስር ብሩን ለእሱ ትርጉሙ ይለያል። የተሰጠውን ሳያጎድል ለእናቱ አስረከበ። የዛን ቀን መላው ቤተሰብ ምሳና ራቱን በልቶ ማደሩን አይዘነጋም።።

ከዚህ በኋላ የእዮብ ታታሪነት በሥራው ይገለጥ ያዘ። ጉልበቱን ሳይሰስት ይሰራል። ከተሰጠው ድርሻ አልፎ ይገኛል። ለሻይ ቡና የሚያጠፋው ምንም ሳንቲም የለም። አራት ሰአት ላይ ሠራተኛው ብስኩት በሻይ ሲበላ እሱ አይሞክረውም። ልጅነቱን በሚያስታውሰው እጅግ በሚወደው ብስኩት ይጨ ክናል።

አንዳንዴ ውስጡ አብዝቶ ይጠይቀዋል።እሱ ግን እንዳይለምድበት ሲሰጋ እንዳልሰማ ይተወዋል። አብረውት የሚሰሩ ባልደረቦች በየቀኑ ዳቦ ገዝተው ሻይ አስቀድተው እንዲበላ ይጋብዙታል። የእዮብ ምላሽ ግን ሁሌም አንድ ነው ።ለጠየቁት ሁሉ «ያመኛ» ነኝ ሲል ይመልሳል። ከሚሰጠው ገንዘብ አንዳች ሳንቲም አያጣፋም።እንደወጣት ብዙ ቢያምረውም የቤቱን ችግር ያስቀድማል።

እዮብ የሳምንት ክፍያው አርባ ብር ሲገባ የእናቱን ጎዶሎ ያለአንዳች መሳቀቅ ይሞላ ያዘ። ይህኔ ቤተሰቡ በልቶ ማደሩ ሰላም ሰጠው። ለቤት ሰጥቶ የምትተርፈውን አስር ብር በኪሱ ይዞ ከሌሎች ላለማነስ ጣረ። ባልንጀሮቹ ሲጋብዙት እሱም የአቅሙን ያደርግ ጀመር።

በሻይ ለስላሳ የተጀመረ ግብዣ ውሎ አድሮ ደረጃው አደገ። ቀስ እያለ ከድራፍት ፣ ከቢራው መንደር ዘለቀ። አንዳንዴ አረፍ ባለ ጊዜ ያለፈበትን ውጣውረድ ያስበዋል። በልጅነቱ የከፈለው ዋጋ ፣ የደረሰበት እንክርትና በደል ውል ይልበታል። ትናንትናው ለእሱ የክፉ አሻራ ትዝታ ነው።ዛሬን ባይወድቅም ባሳለፈው ታሪክ ውስጡ ደምቷል፣ ዓይኑ አንብቷል።

### በደል የወለደው ቂም

እዮብ ሁሌም በልጅነት ዕድሜው ክፉ የሠሩትን ያስባል። አዲስ አበባ ለመመለስ ምክንያት የሆነው አጋጣሚ ወለል ብሎ ይታየዋል።እሱ የሆነበትን በደል አይረሳም።ይህን ሲያስታውስ የሰዎቹ ምስል በአካል ይቀርበዋል።ድርጊታቸው ፣ ማሳደዳቸው፣ ስም ማጥፋታቸው ትውስ ይለዋል።

ይህ ትዝታ ያለፈውን እየመዘዘ ፣ የክፉ ታሪኮቹን ስዕል የሚያጎላ ነው። እንዲህ በተሰማው ጊዜ ውስጡ የሚሞላው ቁጭት ብቻ ይሆናል።እነሱን በተራው ሊያገኛቸው ፣ ሊበቀላቸው ይሻል።የልጅነት ደስታውን ነጥቀው ፣ ፈገግታውን ያፈዘዙበት፣ ሩጫውን የገቱበት ክፉዎች ድርጊት እንደጥላ ተከትሎታል።

እዮብ አሁንም ኃይለኝነቱ ከእሱ ነው።የአፍላነት ወኔው ይበልጥ ግሏል።ራሱን ቢችልም ይህ ብቻ አልበቃውም። ከወቅቱ ሰዎች መቅረብ መጠጋትን ፈልጓል። ይህን የማድረግ ፍላጎቱ ደግሞ የእሱ ሚስጥር ብቻ ነው። አጋጣሚው ይጠቅመዋል። አሁን የዛኔ የጎዱትን፣ መልሶ መጉዳት፣ ያስለቀሱትን ዳግም ማስለቀስ ዕቅዱ ሆኗል። የሆዱን በሆዱ ይዞ፣ ወዳሰበው ተራመደ።ለዓላማው የፈለጋቸውን አላጣቸውም። መንገዱ አልጋ በአልጋ ሆኖ ተቃናለት።

የቀረባቸው የተክለኃይማኖት አውራጃ አመራሮች አልራቁትም። ቅልጥፍናውን ወደዱት።በፊታቸው ግርማ ሞገስ ሆነለት።በወቅቱ ካድሬዎች ወጣቶችን መያዝ ማደራጀት ይሻሉ።እዮብ ለዓላማቸው የተመቸ፣ የተቃኘ ሆነላቸው። እንደታሰበው የአካባቢውን ወጣቶች አሰባስቦ አደራጀ።የፈጣኑና ቀልጣፋው ልጅ ታዛዥነት የብዘዎቹን ልብ ገዛ። የትንሹ ልጅ ውስጠት በሀሴት ተሞላ።

የዘመኑ ሥርዓት በራሱ ዕቅድ የሚመራ ነው። ጊዜውን ተጠቅሞ ወደቀጣዩ ያልፋል። ለራሱ ዓላማ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## ባለራዕዩ - በሻካራማው...

ከእነሱ መዝለቅ የፈለገው እዮብ ይህ የገባው ቆይቶ ነበር። ወደ የቀበሌው ያመራው አዲሱ ድልድል ዕውን በሆነ ጊዜ ከልብ ደነገጠ፣ አምርሮም አለቀሰ። ያሰበውን ሳያሳካ ከቦታው መነጠሉን ቢያውቅ ተስፋ ቆረጠ ።

የሥራ ድልድሉ በወጣቶቹ ፍላጎት ተመስርቶ ተለየ።የእዮብ ሃሳብ ከሌሎች የራቀ ሆኖ ምርጫው ውትድርና ሆነ።ይህን የሰሙ ሁሉ ሳቅ ቀደማቸው።እዮብ ቁመትና እድሜው ለውትድርና የሚመጥን አይደለም ።ለስሜቱ የተጠነቀቁ ‹‹ይቅርብህ›› ሲሉ መከሩት።

**ይቅር ለእግዜር ...**

አሁን ያዘጋጀው የበቀል ልምጭ ላይዘረጋ ታጥፏል።እንዳሰበው ከከፍታው ተቀምጦ ጠላቶቹን አልተበቀለም።በእሱ ሳይሆን በአጋጣሚዎች መንገድ መዳዙ አቅጣጫውን አስለውጧል።ከጎኑ የነበሩ መልካም ሰዎች በጎነት አልራቀውም።ሲመክሩት ‹‹እህ...›› ብሎ ሰማቸው። በማታው ክፍለጊዜ ያቋረጠውን ትምህርት እንዲቀጥል ሲያበረቱት ሃሳቡን ተቀብሎ ጠንክሮ ተማረ።

አሁን እዮብ በዕድሜ በስሎ በአእምሮው ዳብሯል።ይህ ለውጥ ያለፈውን እያስጣለ በመልካም መንገድ እያራመደው ነው ።ትናንት አብሮት የቆየው የበቀል መንፈስ አሁን ከእሱ የለም።በውስጡ በጎነት ነግሷል።በመሥራት መለወጥ፣ በመተው መርሳት እንዳለ ገብቶታል። ያለፈበት መንገድ ብዙ እንዳሳየው አላጣውም።ለራሱ ዓላማ ከቀረባቸው ሁሉ ክፉ ደጉን ተምሯል።ትናንት ዛሬ ሆኖ እንደማይቀጥል እየገባው ነው።በጊዜ የማይለወጥ፣ የማይቀየር እንደማይኖር አውቋል።

እዮብ ከለውጡ ሰዎች ጋር በነበረው ጊዜ ግምገማ ይሉትን ተምሯል።ይህ አጋጣሚ ደግሞ ሀቀኝነቱን ያስመሰከረ ነበር ። እሱ ጥፋት ያየባቸውን ፈጽሞ አያልፍም፣ ለጥቅም የተገዙትን፣ በሥልጣን የተመኩትን በማስረጃ እየለየ ለክስ ያቀርባል። ይህ ማንነቱ በብዙዎች ዘንድ አላሰወደደውም። ጥርስ አስገብቶ አስነክሶታል። የእድሜው አፍላነት ከሀቅ ተዳምሮ ከበርካቶች ተላትሟል። የወቅቱ ፖለቲካ ባይገባውም ለያዘው ዓላማ የጸና ፣ በእጅጉ የበረታ ነበር።

እዮብ የወጣቶች ሊቀመንበር በሆነ ጊዜ ከብዙዎች ሞግቷል። እውነትን በእውነት ማውጣት ልምዱ ነውና ካልመሰሉት ጋር አይራመድም፡። ውሎ አድሮ የፖለቲካ ጉዳይ ቢሰለቸው ሁሉን ትቶ ወደራሱ ተመለሰ ።ይህ ጊዜ ከሜጋ ማተሚያ ጋር አገናኘው። በእጅ ሙያው ብዙዎች ይፈልጉታል።ይህን ህንፃ ጨምሮ የቀድሞውን ባህር ትራንስፖርት ድርጅት ሙሉ አልሙኒየም ያለበሰው እሱ ነበር።

እዮብ ራሱን ለሥራ ሰጥቶ በበረታ ጊዜ ጤንነት አልሰማ ይለው ጀመር። ዓይኑን ያመዋል፣ ውስጡን ይጨንቀዋል።ደጋግሞ መድኃኒት እየወሰደ ከራሱ ታገለ።በጊዜው የኢትዮ- አርትራ ጦርነት ነበር።ሥራውን የሰጡት ሰው ኤርትራዊ ናቸው።እሳቸው ችግሩን አልተረዱም፡፤ የሚታይበትን ለውጥ ከራሳቸው አያይዘው ስጋት ገብቷቸዋል።ንብረታቸው እንዳይ ወረስ፣ እንዳይባክን እየፈሩ ነው።

ይህ እውነት የገባው እዮብ ከህመሙ እየታገለ ለታማኝነቱ ይጥራል።የተፈራው አልቀረም። ግለሰቡ ወደ ሀገራቸው ተሸኝተው ሥራውን ልጆቹ ተረከቡ።ከዚህ በኋላም እዮብ ትጋቱ አልቀረም።በህመም እየተሰቃየ አብሯቸው ዘለቀ።ቆይቶ ነገሮች ከአቅም በላይ ሆኑ።ህመሙ በረታ፣ስቃዩ ጨመረ።አጋጣሚው ምክንያት ሆኖ ከሥራው ተፋታ።

**ራስን መቻል ...**

የእረፍት ቆይታው ወደቀበሌ አመላልሶ ከሊቀመንበርነት አገናኘው። ይህ አጋጣሚ ከብዙዎች አውሎ ወደሙያው መለሰው። ለመጀመሪያ ጊዜ ድንቅ የእጅ ሥራውን አስመስክሮ አንድ ሺ ሁለት መቶ ብር ተከፈለው። ይህ ገንዘብ ለእሱ እጅግ ከፍተኛ የሚባል ነበር።እዮብ አሁንም እናቱን አልረሳም። የሚያገኘውን ይዞ ለቤት ያስረክባል። እንዲህ አይነት ክፍያዎች ሲደጋገሙ እናቱ እንጀራ ጋግረው መሸጥ ጀመሩ።የእሱ ጥረት ተቃንቶም በግቢው ውስጥ የራሱን የእንጨት ሥራ ለመክፈት ተዘጋጀ።

ጎን ለጎን የቀበሌ ሊቀመንበርነቱን አልተወም።ችግር ላለባቸው ምላሽ እየሰጠ፣ በጎደለው ሁሉ እየሞላ ጥቂት ተጓዘ። ይህ አይነቱ ይሁንታ ለብዙዎቹ አላመቸም። ግምገማው ወቀሳው ተደጋገመ።‹‹ሂስህን ዋጥ፣ አልውጥም›› ከሌላው ጎራ አላስማማውም።ለብዙዎቹ የጎን ውጋት፣ የቅርብ ስጋት ሆነ።

**የሱስ ፈተና**

ራስን መቻል ሂደት በእንጨት ሥራ ተጀመረ።እጀ መልካሙ ባለሙያ የሚፈልጉት ደንበኞች በረከቱ። እዮብ አንዳንዴ ቁጭ ሲል ጫት ይቅማል። ይህ እውነታ ከልጅነቱ የተከተለው ነው። የገንዘብ አቅሙ ሲጨምር ፣ አጠናከረው። ጫቱ በቀላሉ የማይተወው ሱስ ሆነበት።

እዮብ አሁንም ቤተሰቦቹን አልተወም።ታናናሾቹን በራሱ ገቢ ያሳድራል። ሁሉም ተምረው ራሳቸውን እስኪችሉ መጠበቅን ግዴታው አድርጓል።ያሰበው ተሳክቶ ከግቡ ሲደርስ ወደራሱ ተመለሰ።ከዚህ በኋላ ቤተሰብ ውስጥ ሆኖ መቀጠል አያሻውም። እናቱን በቅርብ እየደጎመ ከቤተሰቡ ተነጠለ።የራሱን ቤት ተከራይቶም የሸቀጥ ሱቅ ከፈተ።

ይህ አጋጣሚ ለጫት፣ ለሀሺሽ ሱስ አመቸው። ምርኮኛ ሆኖ እጁን ሰጠ። እዛው ውሎ አደረ።ብቻነቱ ነጻነትን ሰጠው። እሱን ያሉ ከእሱ ቢመስሉ ተከታዮቹ በረከቱ። አርአያነቱ በጎ እንዳልሆነ ቢገባውም ‹‹ይቅርባችሁ›› አላለም። በሥራው ቢገንም ተግባሩ ላይ ሰነፈ።

የእጆቹን ሥራ የሚሹ ባለበት ይፈልጉታል።ባገኙት ጊዜም እንዳያመልጣቸው ቤታቸው እስከ ማሳደር ይደርሳሉ። እዮብ አይጀምረው እንጂ ሥራውን ከያዘው እጅን በአፍ የሚያስጭን ድንቅ ውጤት አጠናቆ ያስረክባል። እሱ ስለነገ አይጨነቅም። የዕለቱን ካገኘ በቂው ነው።አሁን የሱስ ደረጃው ከፍ ብሏል።ይህ እውነታ ክብሩን አስጥሎ ችሎታውን ፈትኖታል።

1995 ዓ.ም ።እዮብ የሕይወት መንገዱን የሳተበት፣ ጤናው የተቃወሰበት ፈታኝ ዓመት። በዚህ ወቅት ብዙ ሰርቶ ብዙ በትኗል፣ ብዙ ደክሞ ብዙ ባክኗል።አንድ ቀን ግን ይህ ታሪክ ‹‹ነበር›› ሊባል ጊዜው ሆነ።እሱን ፈልጎ ካለበት የመጣ አንድ ወዳጁ ከነበረበት አውጥቶ ከአንድ ሥራ አገናኘው።ቦታውን ለቆ ሲርቅ እሱን ብለው የከበቡት የጫት ጓዶቹ ተለዩት።

**ግራ ጎን ፍለጋ...**

እነሆ እዮብ ከተሻለው መንገድ እየቆመ ነው። ከቆየበት ሥራ ከፍ ብሎ የኢንዱስትሪውን መንደር ተቀላቅሏል።ይህ አጋጣሚ ለብቻው አልመጣም።የእዮብ ዓይኖች ከአንዲት ቆንጆ አርፈው ልቡ በፍቅር ተረቷል።ከዛሬ ነገ ልጅቷን፣ ውበቷን አሳልፉ ለሰጠችው ጉብል ፍጹም ታማኝ ሆኗል።እዮብ ራሱን ሊገዛ ሞከረ።አላቃተውም።ማንነቱን ከሱስ አቅቦ ለክብሯ ተጠነቀቀ።ከእሷ ሲሆን ጥንካሬው ተከተለው።ውሎው ተቀየረ።ልምዱን ተጠቅሞ የኢንዱስትሪ መንደሩን አደራጀ። በጥረቱ ስኬታማ ሆነ።

በነበረው የቀበሌ ቤት ከቆንጆይቱ ጋር አብሮነትን ቀጠለ።ወላጆቿ አላሳፈሩትም።ሽምግልናውን ተቀብለው ሚስቱ እንድትሆን መርቀው ሰጡት።ጎጆው ተቀለሰ፣ አዲስ ሕይወት ተጀመረ።አሁን እዮብ የራሱ ብቻ አይደለም።ለሚስቱ ይጨነቃል፣ ላደራጀው ማህበር ያስባል።

ለፈጠረው አዲስ ሥራ የጠየቀው ብድር ሲሳካ በራሱ ወጪ ዕቃ ገዝቶ ሙያውን አጋራ። ውጤቱ መልካም ሆነለት። ማህበሩ አትራፊ መሆን ሲይዝ አፈንጋጮቹ በዙ፣ ሽኩቻ፣ ንትርክ ተጀመረ። ልፋት ድካሙ መና ቀረ፣ ዓይኑ እያየ ማህበሩ እንደዋዛ ፈረሰ።እዮብ ይህ በሆነ አፍታ ጤናው ተቃወሰ፣ ጨጓራው ደም አነባ፣ የረጋ ደም ከአፉ ተፋ። እርር፣ ድብን አለ። ኀዘን ብስጭት ቢጎዳው ከሆስፒታል አልጋ ተገኘ።

እዮብ ስለሚስቱ አብዝቶ ተጨነቀ።በእሱ ምክንያት ከንቱ መቅረቷ ያስቆጨው ጀመር።ድንገት የሰማው የምስራች ግን ለውስጡ ፈውስ ሆነ።ባለቤቱ ነፍሰጡር ነበረች። ወዲያው ሱስ ይሉትን እርግፍ አድርጎ ሊተወው ወሰነ።ተሳካለት።የመጀመሪያ ልጁን አቅፎ እንደሳመ መካከለኛ ባለሀብት ሆኖ ተመዘገበ።

**የእዮብ ኩላሊቶች...**

ሩጫው ቀጥሏል።አሁን እዮብ የትናንቱ አይደለም። ታሪኩ ተቀይሮ መልካም አባወራ ሆኗል።ሰፈሩ በልማት ሲፈርሰ ኮንዶሚኒየም አግኝቷል።እሱ ግን ጤና ይሉት የለውም።የደም ግፊት ይዞታል።የራስ ምታት ፣ የልብ ህመም፣ ያሰቃየዋል። በህክምና ክትትል መድኃኒቶችን እየወሰደ ነው። 2006 ዓ.ም ደግሞ ካለፉት ዓመታት የከበደ ሆነበት።

አንድ ቀን ምርመራ ላይ ያገኘው ሀኪም በአስቸኳይ ወደ ሌላ ሆስፒታል ጻፈለት። ሳይውል ሳያድር መሄድ ነበረበት።ዕለቱን ያገኘው ሌላ ሀኪምም ውስጡ እያዘነ ሁለቱም ኩላሊቶቹ መድከማቸውን ነገረው። ስለ ንቅለ ተከላ፣ ዲያሌሲስና ህክምናው ዘረዘረለት። በወቅቱ ያስፈልገው የነበረው ገንዘብ 400 ሺ ብር ነበር። እዮብ ይህን ገንዘብ በእጁ አለ። ግን ለሚስቱ ሊተው ወሰነ ። የተባለውን ትቶ በማስተገሻ መድኃኒት ቢቆይም ህመሙ ብሶ አሰቃየው። ያገኛቸው ሀኪሞች ሁሉ ስለ ዲያሌሲስ ይነግሩታል። የእሱ ልብ ግን ይህን ሊያደርግ አልፈቀደም።ከከፋ ህመሙ ጋር ሲታገል ጊዜያት ተቆጠሩ። እዮብ መሞቱ ላይቀር ቤተሰቡን መበተን አይፈልግም።ሚስጥሩንና ገንዘቡን ለሚስቱ ሸሽጎ ማስቀመጥን ይሻል።

ህመሙ ያሰቃየው ይዟል።አልቻለም።እንደምንም ተመክሮ ህክምናውን ጀመረ።በድንገት ባለቤቱ አወቀችበት። ለወራት ውስጡ ቢቃወስም በጥንካሬ አገገመ። አሁንም ብዙ ያስባል።እንደሱ ዲያሌሲስ የሚያ ደርጉ ምስኪኖች ያሳዝኑታል። አብዛኞቹ ኑሯቸው ከእጅ ወደአፍ ነው። በህመሙ ብዙ ነገራቸውን አጥተዋል።

አምርሮ እያዘነ ርምጃውን አፋጠነ።ፊርማ አሰባስቦ ድምጽ ሆናቸው።ውጣውረዱ ፍሬ ያዘለት።ፈቃድ አወጣ፣ ከሚመለከታቸው ቀርቦ የአደባባይ ሰልፍን አስፈቀደ።ተሳካለት።መስከረም 2008 ዓ.ም በፖሊስ ማርሽ ታጅቦ ፣ በበርካቶች ተደግፎ ‹‹ሞት በኩላሊት ይብቃ›› ማህበርን አወጀ።

እዮብ አቅም የሌላቸውን ለማገዝ በሚቀመጡ ሳጥኖች፣ በየባዛሩ በሚደረጉ ዝግጅቶች፣ ገንዘብ እየለቀመ ለህልውናቸው ታገለ።መጽሄቶች ታተሙ፣ በሚዲያዎች ሰፊ ትኩረት ተቸረው። በዚህ ብቻ አልበቃውም። ብዘዎች እንደሚሉለት ከለውጡ በፊት በከተማዋ ማዕድ ማጋራትን የጀመረው እሱ ነበር። በአረንጓዴ ዐሻራ መረሀ ግብሩም አባላቱ ‹‹እየሞትንም ቢሆን እንደግፍሃለን›› በሚል መርህ ችግኞችን በመትከል ተሳትፈዋል። ከደጋፊዎቻቸው ለመከላከያ ሠራዊቱም ደም እንዲለገስ አድርገዋል።

እዮብ እስኪሞት ቃል ለገባለት ዓላማው ጽኑ ሆኖ እንደቆመ ነው።ማህበሩ አቅም ሲያንሰው ስለ ሌሎች መኖር ሲል ኮንዶሚኒየሙን ሸጧል። ይህን ማድረጉ ፈጽሞ አያስቆጨውም። ከህመም እየታገለ፣ መሮጥ መባከን ልማዱ ነው። ይህ እውነታ ግን ውሎ አድሮ ዋጋ ያስከፍለው ያዘ።

የጉዳት መጠኑ አጥንቱን አሳሳው።አካሉ ክፉኛ ተጎዳ።የእሱን መድኃኒቶች ለሌሎች በማሳለፉ ጠንካራ አግሮቹ ዛሉ ፣ አንድ ዱላ ይዞ መውተርተር ጀመረ።አልተሻለውም።እንደምንም በሁለት ክራንች መጓዙን ቀጠለ።በጀርባ መተኛት ብርቅ ሆነበት።በእጅጉ ታመመ፣ ተሰቃየ።እንዲያም ሆኖ መኪና መንዳቱን አላቆመም።

የአንድ ቀኑ ክስተት ግን ነገሮችን እንዳልነበር ለወጣቸው።እዮብ ክራንቹን ተመርኩዞ ወደ መጸዳጃ እየወጣ ነበር ። በድንገት ሸርተት ብሎ ከመሬቱ አረፈ።አፋፍሰው ከሆስፒታል ቢያደርሱት ብረት እንዲገባለት ሆነ። ይህ ብቻውን አልጠቀመም።ከወገቡ በታች መላወስ ተስኖት ‹‹ፓራላይዝድ›› ሆነ።እዮብ እንዲህ መከሰቱ አሳዝኖታል።አሁንም ግን ለሌላ ዓላማ አልሰነፈም።ማህበሩ ላይ ‹‹ሰላም፣ ጤና›› የሚል ቃል አክሎ ትውልድ በሚቀይር ስያሜ አሳደገው።

እዮብ አካሉ በዊልቸር ላይ ከዋለ በኋላም አልቦዘነም። ድጋፍ ለሚያሻቸው ሁሉ አበክሮ ታግሏል።ኃላፊነቱን በብቃት ተወጥቷል።እዮብ ስለወደፊቱ ታላቅ ዓላማን ሰንቋል። ወደፊት የማህበሩን ምክርቤት መስርቶ ለሌሎች ማስረከብ ፍላጎቱ ነው።

የሁለት ሴቶች ልጆች አባት የሆነው እዮብ ዛሬም ጠንካራ ሚስቱ ከጎኑ ናት።ኑሮን ለማሸነፍ በሾፌርነት ሙያ ቤተሰቧን እያሳደረች ነው።ቤተሰቡ ዛሬ የግል ቤት የለውም።በቤት ኪራይ ችግር መፈተኑን ይዟል።እሱ በልጅነቱ ያሳለፈው ውጣውረድና የተራመደበት የስህተት መንገዶች በልጆቹ እንዲደገም አይፈልግም። አሁንም ቢሆን ስለሰው በጎ የመሆን ሰብዕናው አይለወጥም።ዲያሌሲሱን እየወሰደ በመልካምነቱ መስመር መጓዙን ይቀጥላል።

**‹‹ባለራዕይ አይቆምም››**

‹‹ባለራዕይ አይቆምም›› የእዮብን የሕይወት ጉዞ የሚዳስስ ግለ ታሪክ ነው።ይህ መጽሀፍ የተጻፈው በጠንካራው፣ በልበ ሙሉው የኩላሊት ህመምተኛ እዮብ ተክለመድህን ነው።ገጾቹ ሲገለጡ እዮብ ከልጅነት እስከ ጉልምስና ዕድሜው የተራመደባቸውን ሻካራማ መንገዶች ያሳያሉ። እዮብ ዛሬ አካሉ ቢጎዳም ጥንካሬ አልራቀውም። መልካምነቱ ከእሱ ነው። ስለሰዎች ይኖራል።ስለመኖር ይታገላል። ሕይወትም ትቀጥላለች።



ኢኮኖሚ

# ባህልና ቱሪዝም

## አዲስ ዘመን አብሳሪው “ጊፋታ” የወላይታ ብሔረሰብ ሌላኛው እሴት

**ዳግም ከበደ**



ዛሬ መስከረም 13 ቀን በድምቀት የሚከበረው የወላይታ ህዝብ ባህላዊ እሴት የሆነው የጊፋታ በዓል የመላው ኢትዮጵያውያንም ኩራትና ሀብት ምንጭ ነው። ማስረጃዎች እንደሚጠቁሙትም፤ “ጊፋታ” የአዲስ ዓመት በዓል ሥነ ሥርዓት ነው። የዘመን መለወጫ ክብረ በዓሉን መላው ኢትዮጵያውያንም በወላይታ ዞን እና በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች በሚከበረው በዚህ በዓል በድምቀት እንደሚሳተፉ የወላይታ ዞን የባህልና ቱሪዝም መምሪያ ኃላፊው አቶ ተሾመ ሀብቴ ነግረውናል።

የ2016 ዓ.ም የወላይታ ዘመን መለወጫ የጊፋታ በዓል ከወትሮ በላቀ ደረጃ እየተከበረ እንደሚገኝ የዞኑ አስተዳደር አሳውቋል። የዝግጅት ክፍላችን ያነጋገራቸው የመምሪያ ኃላፊው አቶ ተሾመ ሀብቴ በዓሉን በደማቅ ሁኔታ ለማክበር የሚያስችል የንቅናቄ መድረክ ከማዘጋጀት አንስቶ በየደረጃው ልዩ ልዩ ዝግጅቶች መደረጋቸውን ነው የሚገልጹት።

“ጊፋታ በወላይታ ህዝብ ዘንድ ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው ታላቅ የዘመን መለወጫ በዓል ነው” ያሉት ኃላፊው፤ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የመጣና የብሔሩ ማንነት መገለጫ የሆነውን ይህ በዓል ዘንድሮ በተለየ መልኩ እየተከበረ እንደሆነ ያመለክታሉ።

የወላይታ ዞን የመንግሥት ዋና ተጠሪ አቶ አሳምነው አይዛ በበኩላቸው ፤ የብሔሩ ታሪክ አዋቂ ሽማግሌዎችን መረጃዎች ጠቅሰው፣ ጊፋታ በብሔሩ ትልቅ ስፍራ ያለው ከማይዳሰሱ ቅርሶች ውስጥ የሚጠቀስ ታላቅ በዓል መሆኑን ነው የተናገሩት።

“ጊፋታ ማለት ‘ታላቅ ወይም መጀመሪያ’ እንደ ማለት ሲሆን በሌላ በኩል ጊፋታ ማለት መሻገር ማለት ነው” የሚሉት የዞኑ የመንግሥት ተጠሪ፤ በወላይታ የዘመን አቆጣጠር ጊፋታ የዓመቱ የመጀመሪያ ወር ስያሜ ነው። ይህም ከአሮጌ ወደ አዲስ፣ ከጨለማ ወደ ብርሃን መሻገር የሚለውን ይገልጻል ሲሉም ያብራራሉ። ጊፋታ በወላይታ ህዝብ ዘንድ ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው ታላቅ የዘመን መለወጫ በዓል መሆኑንም አመልክተው፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የመጣ የብሔሩ ማንነት መገለጫ መሆኑን ይናገራሉ።

የዝግጅት ክፍላችንም ዛሬ የሚከበረውን በዓል አስመልክቶ “የጊፋታን ታሪካዊ ዳራዎች፣ ባህላዊና የሥነ ፈለግ እውቀቶች አጠቃላይ ሥርዓቱ ምን እንደሚመስል” ለመዳሰስ ወድዷል። በዚህም የዘመን አቆጣጠሩን፣ ህብረተሰቡ በዓሉን ለማክበር የሚያደርገውን ዝግጅትና ከበዓሉ ጋር የተያያዙ የብሄረሰቡን እሴቶች እንዳስሳለን።

### የዘመን አቆጣጠር

ይህንን ደማቅ “የወላይታ ብሔር የዘመን መለወጫ “የጊፋታ” በዓልን ሥርዓት፣ ምንነት እና አጠቃላይ ባህላዊ ሥነ ሥርዓቶችን አስመልክቶ የባህል የታሪክና ቅርስ ተመራማሪው አቶ አዳነ እንደሚገልጹት፤ የወላይታ ብሔር የራሱ የሆነ የዘመን መቁጠሪያ (calendar) አለው። በወላይታ ባህላዊ የዘመን አቆጣጠር መሠረት ጊፋታ የዓመቱ የመጀመሪያ ወር ስያሜ ነው። የዘመን መለወጫ በዓል ስናወሳ የዘመን አቆጣጠርን ነጥለን ማየት አንችልም፤ ምክንያቱም እያንዳንዱ የዘመን መለወጫ በዓል መነሻው የዘመን አቆጣጠር ነውና። የዓለም ህዝብ የጊዜ አቆጣጠር ሥርዓት የፀሐይ (solar) ፣ የጨረቃ (lunar) ወይም ሁለቱን አንድ ላይ የጨረቃና የፀሐይ (luni-solar) ኡደትን ተከትሎ እንደሆነ ይታወቃል።

“በዚህ ዙሪያ በተደረጉ ጥናቶች እንደተረጋገጠው የወላይታ የዘመን አቆጣጠር የግማሽ ጨረቃና የግማሽ ፀሐይ ኡደትን የተከተለ (Lunisolar) ነው” የሚሉት ተመራማሪው፤ ወላይታዎች ቀን (Gallassa) ብለው ሲጠሩ ፀሐይ ስትጠልቅ ወይም ሲመሽ ደግሞ ቃማ (Qammaa) ብለው ይጠራሉ። ቀንና ሌሊትን አንድ ላይ አንድ ቀን (Issi wontta) እንደሚባል ይገልፃሉ።

አቶ አዳነ እንደሚሉት፤ ወላይታዎች ሳምንታትን የሚቆጥሩት በአካባቢው የሚውለውን ትልቁን ገበያ መነሻ በማድረግ ነው። በዚህም ከአንዱ የገበያ ቀን እስከሚቀጥለው የገበያ ቀን ያለውን ጊዜ እንደ አንድ ሳምንት እንደሚቆጥሩት ያስረዳሉ። ይህም (Naa”u Giyaa) ወይም ሁለት ገበያ ማለት እንደሆነ ይናገራሉ።

ይህንን ጥበብ በምሳሌ ሲያስቀምጡት፤ በአንድ አካባቢ የሚውል ትልቁ ገበያ ቅዳሜ ከሆነ እስከሚቀጥለው ቅዳሜ ድረስ ያለውን ጊዜ የመጀመሪያውን ቅዳሜ አንድ ብሎ ቀጥሎ በሳምንቱ የሚመጣውን ቅዳሜ ሁለት በማለት ሁለት ገበያ (Naa”u Giyaa) በማለት እንደሚጠሩት ያስረዳሉ። በዚህም መሠረት አምስት ገበያ (Ichchashu Giyaa) አንድ ሙሉ የጨረቃ ኡደት አንድ ወር (Issi Aginaa) መሆኑን ይናገራሉ። ጨረቃዋ ለመጀመሪያ ጊዜ የታየችበትን ቀን (Aginiyaa xeeraasu) በማለት አንድ ብሎ መቁጠር እንደሚጀምሩ ነው የሚገልፁት።

“በማህበረሰቡ ዘንድ ጨረቃ አዲስ ከመታየቷ በፊት ባሉት ሁለት ቀናት ውሃ ውስጥ ትውላለች የሚል እምነት አለ” የሚሉት የባህልና ታሪክ ተመራማሪው አቶ አዳነ፤ እነዚህ ቀናት ጤሮ ጨገና (xeero ceggennaa) በመባል እንደሚታወቁ ይናገራሉ። ይህም ህብረተሰቡ የጨረቃን መውጣት በመጠባበቅ ወደ ሥራ ለመግባት ዝግጅት የሚያደረግበት ወቅት መሆኑን ያስረዳሉ።

### የአባወራዎች ተግባር

“የጊፋታ በዓል ዝግጅት የሚጀምረው በቁጠባ ‘Qoraphphuwaa’ነው” የሚሉት የታሪክ የባህልና ቅርስ ተመራማሪው አቶ አዳነ፤ በጊፋታ ዕለት አባት ልጁን አስከትሎ በሬ ወደሚታረድበት ቤት በመሄድ ያደለቡትን በሬ በጋራ በማረድ በመደብ በመደብ እንደሚከፋፍሉ ይገልፃሉ። በዚህ ሁኔታ ከሁሉም የሥጋ ብልቶች ትንሽ ትንሽ ቆርጠው በባለተራው ቤት በተዘጋጀው ማባያ ማለትም ቆጮ፣ቂጣ፣ዳጣ በርበሬ ጋር ከቅርጫው አባላት (Amuwaa) ጋር ስለሚቋደሱ ይህም አንድነትን፣ፍቅር ማብሰሪያ ተደርጎ ይወሰዳል። ከዚያም የየራሳቸውን ድርሻ ሥጋ ከመውሰዳቸው በፊት ለመጪው ዓመት በሬ መግዣ አሁን በታረደው በሬ ቆዳ ላይ ቁጠባ ይጀምራሉ።

ይህም ሥርዓት የጊፋታ በዓል ከተሸኘ በኋላ በየሳምንቱ እንደሚቀጥል የሚናገሩት ተመራማሪው፤ በመጨረሻም ዓመቱ ሲጠናቀቅ ተሰብስበው በሬ ከገዙ በኋላ የሚተርፈውን ገንዘብ ለቤት ውስጥ ወጪ እንደሚጠቀሙት ያስረዳሉ። ተጨማሪ የአባወራዎችን ተግባር መኖሩን የሚገልፁት አቶ አዳነ፣ ሥርዓቱን እንደሚከተለው በዝርዝር ያቀርቡታል።

የተለያዩ የሰብል ዓይነቶችን በዘር ወቅት መዝራት፣ መሰብሰብና ለጊፋታ ለይቶ ማስቀመጥ፣ በዓሉ ሲቃረብ ለልጆች አዳዲስ ልብሶችን መግዛት፣ ለማጣፈጫና ለቅመማ ቅመም መግዣ የሚሆን ገንዘብ ለእናቶች መስጠት እና ለጊፋታ የሚታረድ በሬ መግዛት የአባወራ ተግባራት ናቸው። ለእርድ ቀን ከሁለት ወር በላይ የሚሆን ጊዜ ሲቀረው በሬ በመግዛት እስከ እርድ ቀን ድረስ ለሚንከባከብ ተረኛ (Ariyawaa) ይሰጣል። ለበሬው ምቹ ቦታ ቀድሞ በዚህ ቤት እንዲዘጋጅ ይደረጋል።

የጊፋታ በሬ እንደሙሽራ ስለሚታይ ሰው እንዳያየው የተለየ ጋጣ ተዘጋጅቶ ሁሉም ቀዳዳዎች ከምግብ መስጫ ጠባብ በር ውጪ በደረቅ የኮባ ቅጠል (Qonashiyaa) ሙሉ በሙሉ ይሸፈናል። የአሙዋ አባላትም ስኳር ድንች፣ የበቆሎ አገዳ፣ በቆሎ እና የመሳሰሉትን በልጆቻቸው እያሸከሙ ወይም በአህያ እየጫኑ በየተራ በማምጣት ይቀልባሉ። ቀጥሎም በየ 15 ቀኑ ተሰብስበው በሬውን ወደ ውጪ በማውጣት ያለበትን ደረጃ በማየት በጣም እየወፈረ ከሆነ ተንከባካቢውን እያሞገሱ አስተያየት ይሰጣሉ፤ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ የጊፋታ በሬ ይቀለባል።

ሌላው በአባቶችና በወንድ ልጆቻቸው የሚከናወን የአካባቢ ጽዳትና የቤት እድሳት ሥራ ነው። ይህም በወላይታ ብሔር አዲስ ዓመት የመታደስ ምልክት ስለሆነ ሰዎች የቤታቸውን የሳር ክዳን በአዲስ ሳር መቀየር፣ በቤት ውስጥ ያረጁትን ነገሮች ከውጪ ደግሞ በቤቱ ዙሪያና በአካባቢው የሚገኙ ቆሻሻዎችን በማጽዳት በዓሉን እንደሚቀበሉት አቶ አዳነ ይናገራሉ።

### የእማወራዎች ተግባር

“እማወራዎች ለጊፋታ በዓል ከሚያደርጓቸው ዝግጅቶች የመጀመሪያው ቁጠባ (qoraphphuwaa) ነው፤ ይህም የቅቤ እቁብ መጀመር ነው” የሚሉት ተመራማሪው፤ በዚህም መሠረት ዓመቱን በሙሉ የቆጠቡትን በጊፋታ ሰሞን ሁለተኛ ሳምንት ገበያ (Bobbooda) አጥቢያ በቅቤ ዕቁብ ሰብሳቢያዋ ቤት የቅቤ ቡና ከጠጡ በኋላ የየድርሻቸውን ተከፋፍለው እንደሚወስዱ ይናገራሉ። ጊፋታ ካለፈ በኋላም ለቀጣይ ዓመት በየሳምንቱ ቁጠባውን እንደሚቀጥል ይገልፃሉ።

እናቶች ከሰኔ ወር መጨረሻ አካባቢ ጀምሮ ለተለያዩ ባህላዊ ምግቦች ማለትም “ቆጮ፣ ሙቹዋና ባጪራ” በመባል ለሚታወቁ ባህላዊ ምግቦች የሚሆኑ የደረሱ እንሰቶችን ከጓደኞቻቸውና ከሴት ልጆቻቸው ጋር ሆነው በመፋቅ ዝግጅት እንደሚያደርጉ የሚናገሩት የባህል ተመራማሪው፤ ከዚህም በተጨማሪ ዳጣ በርበሬ፣ የተለያዩ መጠጦች ማለትም ቦርዴ፣ ጠላ፣ ጠጅ፣ ቃሪቦ እና ወተት በትልቅ እንስራ እንደሚዘጋጅ ያብራራሉ። በተጨማሪ “ጋዚያ” በመባል ለሚታወቀው ባህላዊ ጨዋታ የሚሆን ሎሚ ገዝተው በቀዝቃዛ ቦታ ያስቀምጣሉ፤ የተለያዩ መዋቢያ ጌጣጌጦችን እንደሚገዙ፤ ለምግብነት የሚውሉ የተለያዩ የእህል ዓይነቶችን ገዝተው እንደሚያጠራቅሙ ይናገራሉ።

“የዳጣ በርበሬ በጊፋታ የቤተሰብ የሥራ ክፍፍል በጣም የጠበቀ በመሆኑ ሁሉም የራሱን ሥራ ያለማንም አዛዥ ወቅቱ ሲደርስ ያከናውናል” የሚሉት ተመራማሪው፤ ወጣት ወንዶች የጉሊያ እንጨት ከመቁረጥና ከማቆም ጀምሮ ለከብቶች ሳር በማጨድና በመከመር፣ እንጨት በመፍለጥ ለበዓሉ ጊዜ ከማስቀመጥ በተጨማሪ ከዘር እና ከአጨዳ ወቅት ጀምሮ ሁሉንም የጊፋታ ዝግጅት ሥራዎችን ከአባቶቻቸው ጎን በመሆን እንደሚከውኑ ይገልፃሉ። ልጃገረዶች እንሶስላ ከመሞቅ ፣ የጋዚያ ጨዋታ ከመጫወት ከመሳሰሉ በግል ከሚፈፅሟቸው ተግባራት በተጨማሪ በሁሉም ሥራዎች እናታቸውን እንደሚደግፉ ያስረዳሉ።

የባህል፣ የታሪክና ቅርስ ተመራማሪው የጊፋታ ክብረ በዓል ተጨማሪ እሴቶች እንዳሉት ጠቁመው፣ ከእነዚያ ውስጥ እዳ መክፈል፣ የቤት እድሳትና የአካባቢ ፅዳት፣ የመንፃት ሥርዓት እንዳገኙበት ይናገራሉ። እነዚህን እሴቶች ከዚህ እንደሚከተለው በዝርዝር ያብራሯቸዋል።

### ዕዳ መክፈል

ከጊፋታ በዓል ቅድመ ዝግጅቶች አንዱ ያደረ ዕዳ መክፈል ነው። በወላይታ ብሔር ሰዎች ከዕዳ ጋር አዲሱን ዓመት አይቀበሉም። ምክንያቱም የግለሰብም ሆነ የመንግሥት ዕዳ ተሸክመው አዲሱን ዓመት የሚቀበሉ ከሆነ ዓመቱን በሙሉ በረከት አይኖረውም ተብሎ ይታመናል። በሌላ በኩል ደግሞ እዳውን ለመክፈል ዳተኛ የሆነ ሰው በማህበረሰቡ ከፍተኛ ነቀፌታ ይደርስበታል። ስለሆነም አንድ ገንዘብ ወይም እህል ያስፈለገው ሰው ከሌላ ሰው ሲበደር አበዳሪው ይህ ዕዳ እጅግ ቢዘገይ እስከ ጊፋታ በዓል ድረስ እንደሚመለስ በጣም እርግጠኛ ሆኖ የሚያበድረው በመሆኑ በብሔሩ ከጊፋታ በፊት ዕዳን አሟጦ መክፈል ነባር ባህል ነው።

### የቤት እድሳትና የአካባቢ ጽዳት

የጊፋታ በዓሉ እየተቃረበ ሲመጣ ማህበረሰቡ አዲሱን ዓመት አዲስ ቤት በመሥራት ወይም አሮጌውን ቤት በማደስ መቀበል ነባር ባህል ነው። በመሆኑም ነባሩን አሮጌ ቤት ፈርሶ አዲስ የሚሠራ ከሆነ በደቦ ወይም በማህበር ያከናውናሉ። ነገር ግን የቤት ዕድሳት ብቻ ከሆነ አባወራው ከቅርብ ጓደኞቹ ወይም ለአቅመ አዳም ከደረሱ ልጆቹ ጋር ያከናውናሉ። በአሮጌው ዓመት ማብቂያ ቤታቸውን፣ ጓሯቸውንና አካባቢያቸውን በማጽዳት በዓሉን በተሟላ ንጽህና ይቀበላሉ።

### የመንፃት ሥርዓት

በወላይታ ነባር ባህል የዘመን መለወጫ በዓሉ እንደነገ ሊከበር ማለትም (በ2016 ዓ.ም በ12 ቀን ቅዳሜ ለእሁድ አጥቢያ) እኩለ ሌሊት ላይ አዲሱን ዓመት ከመቀበላቸው በፊት ሁሉም የማህበረሰቡ አባላት ከአሮጌው ዓመት እድፍና ቆሻሻ ጋር አዲሱን ዓመት አንቀበልም” በሚል እምነት ውሃ አሙቀው ገላቸውን ይታጠባሉ። ምክንያቱም ወላይታዎች ሁልጊዜ አዲሱን ዓመት የሚቀበሉት በሽታ፣ ረሃብ፣ ድርቅ የሌለበት መልካም ዝናብ የሚጥልበት፣ መልካም ነፋስ የሚነፍስበት፣ የጥጋብ ዓመት እንዲሆን ከአለፈው ዓመት ኃጥያት መንጻት አለብን ብለው ስለሚያምኑ ነው። ለህዝቡ አዲስ ዓመት ሁል ጊዜ አዲስ ተስፋ ይዞ ስለሚመጣ ንፁህ ሆነን መቀበል አለብን የሚል የፀና እምነት አለ።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ሳምንቱን በታሪክ

# ዲፕሎማትና የታሪክ ምሁሩ ኅሩይ

**ዋስልኝ አየለ**

ስለኢትዮጵያ ቀደምት ታሪኮች ሲጠቀስ የእኚህን ምሁር ስም መጥቀስ የተለመደ ነው።በብዙ የታሪክ ድርሳናት ውስጥ የእርሳቸው መጻሕፍት ምንጭ ተደርገው ይጠቀሳሉ።‹‹ከንግሥት ሳባ እስከ ዓድዋ›› ከሚለው መጽሐፋቸው ጀምሮ የኢትዮጵያን የጥንት፣ የመካከለኛው ዘመን እና ዘመናዊ ታሪኮችን አስተዋውቀዋል።‹‹ወዳጄ ልቤ›› በሚለው መጽሐፋቸው በብዙዎች ዘንድ ይታወቃሉ።

በዛሬው ሳምንቱን በታሪክ ዓምዳችን ከ85 ዓመታት በፊት መስከረም 9 ቀን 1931 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩትን ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴን እናስታውሳለን።ከዚያ በፊት ግን እንደተለመደው በዚህ ሳምንት የተከናወኑ ሌሎች ዓለም አቀፍ እና የሀገር ውስጥ የታሪክ ክስተቶችን እናስታውስ።

መስከረም 7 ቀን 1888 ዓ.ም የዓድዋ ጦርነት የክተት ዘመቻ አዋጅ ታወጀ።ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ አጤ ምኒልክ የውጫሌን ውል እንደማይቀበሉና ሁሉም ኢትዮጵያውያን ሀገራቸውን ከወራሪ ጠላት እንዲከላከሉ የሚያሳስብ ታሪካዊ አዋጅ ተናገሩ። መስከረም 7 ቀን 1888 ዓ.ም የታወጀው አዋጅ የሚከተለው ነበር።

‹‹እግዚአብሔር በቸርነቱ እስካሁን ጠላት አጥፍቶ ሀገር አስፍቶ አኖረኝ፤ እኔም እስካሁን በእግዚአብሔር ቸርነት ገዛሁ፤ እንግዲህ ብሞትም ሞት የሁሉ ነውና ስለኔ ሞት አላዝንም፤ ደግሞ እግዚአብሔር አሳፍሮኝ አያውቅም፤ ወደፊትም ያሳፍረኛል ብዬ አልጠራጠርም።አሁን ግን ሀገር የሚያጠፋ፣ ሃይማኖት የሚያስለውጥ ጠላት እግዚአብሔር የወሰነልንን ባህር አልፎ መጥቷል፤ እኔም ያገሬን ከብት ማለቅና የሰውን መድከም ዐይቼ እስካሁን ዝም ብለው ደግሞ እያለፈ እንደፍልፈል መሬት ይቆፍር ጀመር።አሁን ግን በእግዚአብሔር ረዳትነት አገሬን አሳልፌ አልሰጠውም፤ ያገሬ ሰው ካሁን ቀደም የበደልኩህ አይመስለኝም፤ አንተም እስካሁን አላስቀየምከኝም።ጉልበት ያለህ በጉልበትህ እርዳኝ! ጉልበት የሌለህ ለልጅህ፣ ለሚስትህና ለሃይማኖትህ ስትል በኀዘን እርዳኝ! ወስልተህ የቀረህ ግን ኋላ ትጣላኛለህ! አልተውህም! ማርያምን ለዚህ አማላጅ የለኝም! ዘመቻዬም በጥቅምት ነውና የሸዋ ሰው እስከ ጥቅምት እኩሌታ ድረስ ወረይሉ ከተህ ላግኝህ!››

መስከረም 7 ቀን 1971 ዓ.ም የግብጽ ፕሬዝደንት አንዋር ሳዳት እና የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ሜናኼም ቤጊን በአሜሪካው ፕሬዝደንት ጂሚ ካርተር ሽምጋይነት፤ ከ12 ቀናት የምሥጢር ድርድር በኋላ፤ ‹‹የካምፕ ዴቪድ ስምምነት››ን ተፈራረሙ።‹‹የካምፕ ዴቪድ ስምምነት›› የመካከለኛው ምስራቅ ፖለቲካን የለወጠ ክስተት ነበር።የአረቡ ዓለም መሪ ተደርጋ ትቆጠር የነበረችው ግብጽ ስምምነቱን መፈረሟ በከሃዲነት አስፈርጇት ለ10 ዓመታት ከአረብ ሊግ አባልነት ታገደች።ከዚህ በተጨማሪም ስምምነቱ፣ የስምምነቱ ፈራሚ የሆኑት ፕሬዝደንት አንዋር ሳዳት እንዲገደሉ ምክንያት ሆነ።

አሁን በዝርዝር ወደምናየው የብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴ ታሪክ እንመለስ።

ገና በሕፃንነታቸው ያሳዩት የትምህርት ፍላ ጎት፤ የነበራቸው የአዕምሮ ብሩህነት ሊቃውንት መምህ ሮቻቸውን አስደንቆ ከመምህሮቻቸው የተሰጡትን ስማቸውን እንዲሸልሟቸው ያስደረጉ የቀለም ቀንድ ናቸው።በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ከነበሩት የወቅቱ የኢትዮጵያ ዘርፈ ብዙ ምሁራን መካከል በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱ እንደሆኑ በተደጋጋሚ ተመስክሮላቸዋል።ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴ።

ኅሩይ የተወለደው በ1871 ዓ.ም ሸዋ፣ መርሐ ቤቴ አውራጃ፣ በታች ቤት ወረዳ፣ ረመሸት ቀበሌ፣ ደን አቦ ገዳም በተባለ ሥፍራ ነው።ወላጆቹ ያወጡለት ስም ገብረመስቀል ነበር።ገብረ መስቀል እንጦጦ ራጉኤል ደብር መጥቶ የመጻሕፍትን ትርጓሜ ከደብሩ



ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴ

ሊቃውንት በሚማርበት ወቅት ወልደጊዮርጊስ የተባሉት መምህሩ ‹‹ጎንደር በነበርኩ ጊዜ መምህሬ ስለሚወዱኝ ‹ኅሩይ› እያሉ ይጠሩኝ ነበር። ወደ አዲስ አበባ ከመጣሁ በኋላ ግን በዚህ ስም እየተጠራሁኝ አይደለም። አንተ የቀለም ቀንድ ስለሆንክና በምግባርህም የተወደድክ ስለሆንክ ‹ኅሩይ› የተባለውን ስሜን ትጠራበት ዘንድ ሸልሜሃለሁ›› አሉት፤ እርሱም ስሙን በደስታ ተቀበለ።

አባቱ ትምህርት ባለመማራቸው ምክንያት ስድብ ደርሶባቸው ያውቅ ነበርና በእርሳቸው የደረሰው በልጃቸው ላይ እንዳይደርስ ሲሉ ኅሩይን ከልጅነቱ ጀምሮ ትምህርት ላይ እንዲያተኩር አደረጉ።ኅሩይም በተወለደበትና በሌሎች ቦታዎችም በመዘዋወር የንባብ፣ የዜማና የድጓ ትምህርቶችን ከዘመኑ ሊቃውንት ተምሯል።

ኅሩይ በእንጦጦ ራጉኤል ደብር የመጽሐፍ ትርጓሜን በሚገባ ተምሮ አጠናቋል። በቀሰመው ትምህርትም በአስተርጓሚነት አገልግሏል።በባሕላዊው ትምህርት የተሟላ እርካታ ማግኘት ያልቻለው ኅሩይ፣ አዲስ አበባ ስዊድን ሚሽን ትምህርት ቤት ገብቶ እንግሊዝኛ ቋንቋ ተምሯል። ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ አረብኛ ቋንቋ ለመማር ጥረት ቢያደርግም ‹‹ኅሩይ ሰለመ›› የሚል አሉባልታ ስለሰማ ለጊዜው ትምህርቱን ለማቆም ተገዷል። በኋላም ከፈረንሳያውያን ሐኪሞች ፈረንሳይኛ ቋንቋን መማር ችሏል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰነድ ላይ ሰፍሮ እንደሚገኘው፤ ብላቴን ጌታ ኅሩ ከ1910 እስከ 1914 ዓ.ም ድረስ የአዲስ አበባ ከንቲባ ሆነው አገልግለዋል። ከንቲባ ከመሆናቸው አስቀድሞ የከተማዋ ሥራ አስኪያጅ ሆነው ሰርተዋል።በከንቲባነት የአገልግሎት ዘመናቸውም ቀደም ሲል በተለያዩ የአስተዳደር ስያሜዎች ይጠራ የነበረውን የከተማውን አስተዳደር ‹‹ማዘጋጃ ቤት›› ብለው በመሰየም እስካሁን ድረስ የዘለቀ ቋሚ ስያሜ ሰጥተውታል። ብላቴን ጌታ ኅሩይ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደራዊ መዋቅር መልክ እንዲይዝ እንዲሁም በከተማዋ የመሠረተ ልማት ተግባራት እንዲከናወኑ በርካታ ተግባራትን አከናውነዋል።

በዓለም መንግሥታት ማኅበር የመጀመሪያው የኢትዮጵያ መልዕክተኛ ቡድን አባል ነበሩ፤ አልጋወራሽ ተፈሪ መኮንን የልዑክ ቡድናቸውን እየመሩ በአውሮፓ ጉብኝት ሲያደርጉ ብላቴን ጌታ ኅሩይም የቡድኑ አባል ሆነው የአውሮፓን ከተሞች ጎብኝተዋል።ይህም የአውሮፓውያንን ባሕል እንዲመለከቱና የወቅቱን የአውሮፓን ሥልጣኔና አጠቃላይ ሁኔታም እንዲታዘቡ እድል ፈጥሮላቸዋል።

የፋሺስት ኢጣሊያ ጦር ኢትዮጵያን በወረረበት ወቅት ብላቴን ጌታ ኅሩይ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ነበሩ።ለአጭር ጊዜ ቢሆንም ብላቴን ጌታ ኅሩይ በጃፓን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት አምባሳደር ሆነው ሠርተዋል። በጃፓን የነበራቸው ቆይታ ኢትዮጵያም በቴክኖሎጂ ታግዛ እንደጃፓን ጠንካራና ዘመናዊ እንድትሆን የሚያነሳሳ ምኞት ፈጥሮባቸው ነበር።

ብላቴን ጌታ ኅሩይ ‹‹ኢትዮጵያንና ጃፓንን ብዙ የሚያመሳስሏቸው ነገሮች አሉ፤ ስለሆነም ኢትዮጵያ ለዘመናዊነት የጃፓንን አርዓያ ብትከተል ጥሩ ውጤት ታገኝበታለች›› ብለው ከሚያምኑትና ‹‹ጃፓናይዘርስ/Japanisers›› ተብለው ከሚታወቁት የ20ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ኢትዮጵያውያን ተፅዕኖ ፈጣሪ ምሁራን መካከል አንዱ ነበሩ።ብላቴን ጌታ ኅሩይ ኢትዮጵያና ጃፓን ለበርካታ ዓመታት የዘለቀ ዘውዳዊ የአስተዳደር ሥርዓት ባለቤት እንዲሁም የምዕራባውያንን ተፅዕኖ ተቋቁመው የኖሩ በመሆናቸው አንዳቸው ለሌላቸው አርዓያ የሚሆኑባቸው ብዙ ነገሮች እንዳሉ በጽኑ ያምኑ ነበር።ይህን እሳቤያቸውንም ‹‹ማኅደረ ብርሃን ሐገረ ጃፓን›› በተሰኘው ስራቸው በዝርዝር አብራርተውታል።

ከማይጨው ጦርነት በኋላ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ የዲፕሎማሲ ትግል ለማድረግ ወደ ውጭ በተሰደዱበት ወቅት ብላቴን ጌታ ኅሩይም ከኢትዮጵያ ወጡ።ቀዳማዊ አፄ ኃይለስላሴ ፋሺስት ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ላይ ስለፈጸመችው የግፍ ወረራ ጀኔቫ ላይ ለዓለም መንግሥታት ማኅበር ሤስረዱ ኅሩይ ከጎናቸው ነበሩ።

ብላቴን ጌታ ኅሩይ ከመንግሥታዊ ኃላፊነቶቻቸው ባሻገር በደራሲነታቸውም ይታወቃሉ።በርካታ የታሪክ፣ የጉዞ ማስታወሻ፣ የሃይማኖት፣ የልብወለድ፣ የግጥምና የጠቅላላ ዕውቀትን ጨምሮ ከ16 በላይ መጽሐፍትን አበርክተዋል። ከሥራዎቻቸው መካከል ‹‹ወዳጄ ልቤ›› የሚባለው መጽሐፍ በብዙዎች ዘንድ ታዋቂነትንና ተወዳጅነትን አትርፎላቸዋል።

ብላቴን ጌታ ኅሩይ እንግሊዝን፣ አሜሪካን፣ ቻይናን፣ ፈረንሳይን፣ ኢጣሊያን፣ ግብጽንና ሌሎች ሀገራትን ጎብኝተዋል።የሀገራቸውን ወደኋላ መቅረት ከአውሮፓውያኑ ዘመናዊነት አንፃር ባስተዋሉ ቁጥር ቁጭታቸውን ባገኙት አጋጣሚ ይገልጹ ነበር። በአንድ አጋጣሚ ኢጣሊያን ሲጎበኙ በኢንዱስትሪው አማካኝነት የሚከናወነውን ድንቅ ሥራ ተመልክተው በመደነቅ ተከታዩን ሃሳብ አስፍረው ነበር።

‹‹ ለሀገራችን ለኢትዮጵያ የልብስና የእርሻ መኪና የግድ ያስፈልጋል። ኑሯችን ሁሉ ሸማ ለብሰን ነው እንጂ እንደ አውሮፓዎች የበግ ጠጉርና ሐር ዘወትር አንለብስምና ሀገራችን ጥጥ ለማብቀል የተመቸ ነውና ስለዚህ የሸማ መኪና ያስፈልገናል። ምግባችንም እህል ነው እንጂ እንደ አውሮፓዎች ሥጋና ዓሣ አትክልት ሁልጊዜ አናገኝምና ሀገራችንም አሳምሮ እህል ያበቅላልና ስለዚህ የእርሻ መኪና ያስፈልገናል። ይህንንም አስቀድሞ መንግሥት ገዝቶ ፋብሪካውን ቢያቆም መኳንንቱና ያገር ባለፀጎች ሁሉ እንደ ኩባንያ ገንዘብ እያዋጡ አንድ አንድ መኪና እየገዙ ፋብሪካ ያቆሙ ነበር። ከዚህም በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም ያገኙበት ነበር ።››

በሌላ በኩል ብላቴን ጌታ ኅሩይ ዓለማዊ ችግርን ለመፍታት ዕጣፋንታ ላይ ተስፋ ማድረግ እንደማይገባና ፈጣሪም የሰጠንን ጸጋ የገጠሙንን ችግሮች ለመፍታት ማዋል ሲሳነን እንደሆነ በሚከተለው መልኩ ገልጸዋል።

‹‹እግዚአብሔር ይጠብቀኛል ብሎ ቤት ሳይሠሩ፣ አጥር ሳያጥሩ፣ እህል ሳይዘሩ መንደር ለመንደር ሲዞሩ ቢሞቱ እግዚአብሔርን መፈታተን ነው። ንጉሥም እግዚአብሔር ይጠብቀኛል ብሎ ጋሻ ጦሩን፣ ሰይፉን፣ መድፉንና ጠመንጃውን ሳያዘጋጅ ቢቀመጥ ድንገት ጠላት መጥቶ እርሱን ገድሎ መንግሥቱን ቢወስድበት እግዚአብሔርን መፈታተን ነው። ጉልበታችሁን ተማም ናችሁ እግዚአብሔርን አትርሱ።››

ለንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ የቅርብ አማካሪ በመሆን የሃይማኖትና የአስተዳደር ሕግጋትን እየተረጎሙና የአርትኦት ሥራዎቻቸውን እያጠናቀቁ እንዲወጡ ያደረጉት ታላቁ ዲፕሎማትና ደራሲ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴ እንግሊዝ ውስጥ በስደት ላይ ሳሉ፣ መስከረም ዘጠኝ ቀን 1931 ዓ.ም አርፈው ሥርዓተ ቀብራቸው በዚያው እንዲፈፀም ተደረገ።የፋሺስት ኢጣሊያ ጦር በኢትዮጵያውያን ተሸንፎ ከኢትዮጵያ ምድር ከተባረረ በኋላም በ1940 ዓ.ም አስከሬናቸው ካረፈበት ቦታ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ በመንበረ ፀባኦት ቅድሥት ሥላሴ ካቴድራል እንዲያርፍ በክብር ተድርጓል።በስደት ላይ የነበሩት ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ እንግሊዝ በነበረው የብላቴን ጌታ ኅሩይ ሥርዓተ ቀብር ላይ የሚከተለውን ንግግር አድርገው ነበር።

‹‹አሁን የአዳምን ልጆች ወግ ሲቀበል የምታዩት ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴ በሀገራችን ሥርዓት በመልካም አያያዝ ያደገ ከኢትዮጵያም ከፍ ካሉት ሊቃውንት የሚቆጠር ነው። ብልሃቱንና ትጋቱንም ለመልካም ሥራ የሚያገለግሉ መሣሪያዎች ስላደረ ጋቸው በመንግሥታችን ሥራ ለመመረጥና ወደ ታላቁ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነት ለመድረስ በቃ። በየጊዜው የጻፋቸው ከፍተኛ ባህሪውን የሚገልጹ መጻሕፍት፤ ይልቁንም በቤተ-ክህነትና በታሪክ እውቀት በዓለም ሊቃውንት ዘንድ የታወቀና የተከበረ አደረጉት። ለምታውቁት ሰው ከታሪኩ ከዚህ የበለጠ ልነግራችሁ የሚያስፈልግ አልመሰለኝም። በአጭሩ ከጠባዩ ትልቅነት የሚሰማኝን ለመናገር ሳስብ ጊዜውን ሁሉ ቁም ነገር በመሥራት ማሳለፉ፤ ከራሱ ይልቅ የተቸገሩትን ለመርዳት መጣሩ፤ እውነትን፣ ፍርድንም ማክበሩና በአገር ፍቅር መቃጠሉ ትዝ ይሉኛል።

አገልጋዩና ወዳጄ ኅሩይ! በተቻለህ ስለአገርህ ሥራህን በሚገባ ፈጽመህ በምትሰናበትበት ጊዜ ታላቅ ነህ ሳልልህ ብቀር ሥራዎችህ ቀድመውኝ ይናገራሉ። በክፉ አድራጊዎች የሚገፉ የዓለምን ፀጥታ የሚያናውጥ ነፋስ ምንም ቢያንገላታህና በታላቅ ፈተና ላይ ቢጥልህም ሊያሸንፍ አልቻለም። ታላቅና ቸር በሆነው ጌታ በተመደበው ሕግ ግን መታዘዝ ግድ ሆነብህ። ይህም ለያንዳንዳችን የሚደርሰን ዕድል ነው። አንተም እስከ መጨረሻ ከታገልክ በኋላ ዛሬ ደከመህ፣ አንቀላፋህም። በሥጋ ብትለየንም ስምህና ሥራህ በመካከላችን ይኖራሉ።

ኅሩይ፣ እግዚአብሔር ሲያስበን አጥንቶችህና መንፈስህ የሚሰፍሩበትን ቦታ እስኪያዩና ከአባቶችህ እስኪቀላቀሉ ድረስ በእንግድነት በመጣህበት በዚህ ሥፍራ በሰላም ዕረፍ።»

ብላቴን ጌታ ኅሩይ ከወይዘሮ ሐመረ እሸቴ ጋር ጋብቻ መስርተው ስድስት ልጆችን አፍርተዋል፤ ብዙ የልጅ ልጆችንም ለማየት በቅተዋል። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበር ከኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት ጋር በመተባበር ጳጉሜን ሁለት ቀን 2004 ዓ.ም በአዲስ አበባ ቴአትርና ባህል አዳራሽ የአራት ቀደምት ደራሲያንን ምስል የያዙ ቴምብሮች አስመርቆ ገበያ ላይ ሲያውል ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ምስላቸው በቴምብር ላይ ከታተሙላቸው ደራሲያን መካከል አንዱ ነበሩ። ጉለሌ የሚገኘው የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚም ያስገነባውን የሥነ ጥበባት ማዕከል በስማቸው እንዲጠራ አድርጓል። የሕይወት ታሪካቸው ‹‹የብላቴን ጌታ ህሩይ ወልደ ሥላሴ ታሪክ ፡ 1871 - 1931 ዓ.ም›› በሚል ርዕስ በኤመሪተስ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ ተዘጋጅቶ ታትሟል።

ስፖርት እና መዝናኛ

# የዝነኞች ገጽ

## የቤተሰብ ጫና ከሙዚቃ ያራቃቸው ድምጸ መረዋ

ቤዛ እሸቱ

ሕይወት ፈርጇ ብዙ ነው።አንዳንዶች ከጅምሩ በአንድ የሙያ ዘርፍ ተክነው በዛው ታውቀው ወደሌላ ሳያማትሩ ሰጥመው ይቀራሉ።አንዳንዶች ሕይወትን ለማሸነፍ በተለያዩ ምክንያቶች በየጊዜው የሙያ መስካቸውን ለመቀያየር ይገደዳሉ።በዛሬው የዝነኞች ገፅ አምዳችን ልንመለከታቸው የወደድነው የዝናው ዓለም ሰው ምንም እንኳን ከሁሉ የላቀውን ስምና ዝና በድምጻዊነቱ ቢቀዳጁም ጋዜጠኝነት፣ የሽያጭ ባለሙያነት እንዲሁም ሹፍርና ከተሰማሩባቸው የሥራ መስኮች ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

«ከጣትም ጣት ይበልጣል» እንዲሉ ከሳቸው የሙዚቃ ሥራዎች የኔ ሃሳብ የተሰኘው ዘመን ተሻጋሪ ሥራ ደግሞ የ 62 ዓመት የእድሜ ባለጸጋ ቢሆንም ዛሬም እንደጥንቱ ከልጅ እስከአዋቂው እንዲታወሱና እንዲወደዱ ያደረጋቸው አንኳር ሥራቸው ነው።ድምጻዊ እንዲሁም ጋዜጠኛ ግርማ ነጋሽ 80 ዓመትን ቢሻገሩም ድምጻቸው አሁንም አልተለያቸውም።በሙያም በእድሜም አንጋፋ ናቸውና ከስማቸው ፊት ጋሼን ማስቀደም መርጠናል።

የተወለዱት አዲስ አበባ ፊት በር ነው።የአሁኑ ሸራተን ሆቴል ያረፈበት አካባቢ የሳቸው የልጅነትና የወጣትነት እድሜ የተቀለሰበት ሰፈር ነው።ታዲያ ሰፈሩ በሕብረት የታወቀ ነውና ከእኩዮቻቸው ጋር ሰብሰብ ብለው ማውጋትና ዘፈን መሞከር መለያቸው ነበር።በተለይ በበዓል ወቅት ዋነኛ የሰፈሩ አድማቂዎች ናቸው።የጥምቀት ሰሞን ከእኩዮቻቸው ጋር ጃንሜዳ ከትመው ታዳሚ ሲያዝናኑ ይሰነብታሉ። ይሄ ስብስብ ማርኳቸው ከተቀላቀሉ ሰዎች መካከል እውቁ ድምጻዊ ጥላሁን ገሰሰ ይገኝበታል፡፡

ያኔ እሱ በሬዲዮ የሚሰማ ስሙ የታወቀና የተወደደ ድምጻዊ ቢሆንም በመልክ አያውቁትም።ወደእነሱ ሰፈር አመጣጡ አያቱ እዛ አካባቢ መኖር በመጀመራቸው ስለሆነ ስለማንነቱም ጠለቅ ያለ እውቀት አልነበራቸውም።እሱን የሚያውቁት በዘፋኝነቱ ሳይሆን ሰፈራቸው በገባ ዘናጭ ሰውነቱ ነበር።ስለዚህም እሱ ባለበት የሰፈር ልጆች በሙሉ ያለመሳቀቅ ያዜማሉ።ያኔ ቀረብ ብሎ አስተያየት ሲሰጣቸው ከሰፈር ልጅነት በዘለለም ማንነቱ ስለተገለጸላቸው የእሱን አስተያየት ከቁምነገር ይወስዱት ጀመር፡፡

ፊት በር በሰፈር ጓደኝነት የተመሠረተ ወዳጅነት ዳብሮ የያኔ ተማሪና ወጣቱ ጋሽ ግርማ ጥላሁንን ፍለጋ ጃንሜዳ የክብር ዘበኛ የኪነት ቡድን ጋር ሲሄዱ ከትዝታው ንጉሥ መሀሙድ አሕመድን፣ ከድምጻዊ እሳቱ ተሰማ፣ ከድምጻዊ ተፈራ ካሳና ባጠቃላይ የክብር ዘበኛ ኦርኬስትራ አባላትን መተዋወቃቸውን ያወሳሉ።ድምጻዊ ወዳጃቸው ጥላሁንን ብለው ሲሄዱ ካገኙት ድምጻዊ መሀሙድ አሕመድ ጋር የተመሠረተው ወዳጅነት ሰምሮ ብዙ ክፉ ደጎችን አብረው አሳልፈዋል።ከጥላሁን ጋር የተጀመረው ወዳጅነትም በ1964 ዓ.ም ትዳር ሲመሰርቱ አንደኛ ሚዜያቸው በመሆን ታጅቧል።በሰርጋቸው ምኒልክ ወስናቸው ከሌሎች ሁለት የሰፈር አብሮ አደጎቻቸው ጋር ሚዜዎቻቸው ነበሩ፡፡

ሙዚቃና ጋሽ ግርማ ቁርኝታቸው ለመንፈስ ምግብነት ነበር።ያለምንም ትርፍ ፍላጎት ይዘፍናሉ በምትኩ ከሷ ምንም አይጠብቁም።የሰፈር ድግሱን እነሱ አሉለት፤ ደግሞም የመስቀል ደመራም ሆነ ጥምቀት ሲደርስ ከዘፈኑም ከመዝሙሩም እያጣቀሱ ያስነኩታል። ሰፈራቸው ለጃንሜዳ ቅርብ በመሆኑ በየዓመቱ ለጥምቀት የጃንሜዳ ድምቀቶች ነበሩ።ሆኖም ለሙዚቃ መስመራቸው ፈር መያዝ ከጥላሁን ገሰሰ ጋር መወዳጀታቸውን ዋና ምክንያት ያደርጉታል።እሱ ያኔ የሰፈር ወዳጃቸው ሲሆን በቃኘው ሬዲዮ ጣቢያ ዘፈኖቹን የሚሰሙ ብሎም የሚያደንቁት ድምጻዊ ቢሆንም በአካል ስለማያውቁት በነጻነት ወዳጅነት መስርተዋል።ያለመሳቀቅ ከሰፈር ልጆች ጋር አብረው ያዜማሉ፤ በሂደት ማንነቱን ሲያውቁ ፈር የሚያሲዝ ምክር ለግሷቸዋል፤ ከዛም አልፎ በርካታ የሙዚቃ ሰዎችን እንዲያውቁ ምክንያት ሆኗቸዋል።

የጥላሁን ምክር ለሙዚቃ ቢያቀርባቸውም የሰፈር አብሮአደጎቻቸው የፖሊስ ኦርኬስትራን መቀላቀል ጋሽ ግርማንም ሥራቸው ሙዚቃ እንዲሆን አነሳስቷቸዋል።ነገሩ እንዲህ ነው፤ ከዕለታት አንድ



ቀን አባይ በለጠ እና አረጋይ ተስፋዬ የተሰኙ የሰፈር ልጆች የፖሊስ ኦርኬስትራን ተቀላቅለዋል የሚል ወሬ በሰፈራቸው ፊትበር ናኘ።እነሱ ገብተው እኔ እንዴት እቀራለሁ ሲሉ የተቆጩት ጋሽ ግርማ ኦርኬስትራው ወደሚገኝበት ኮልፌ የሚወስዳቸውን መኪና መፈለግ ጀመሩ።በዚህ ፍለጋ ላይ እያሉ አሸዋ የጫነ የጓጋደኛቸው አባት ይመጣል።ቀረብ ብለው "እባኮት ወደኮልፌ ከሆኑ ይሸኙኝ" ይላሉ።"ና ውጣ" የሚል ፈቃድ እንደተቸራቸው አሸዋው ላይ ወጥተው ጉዞ ወደ ኮልፌ።

በቦታው ያረጋገጡት እውነትም ጓደኞቻቸው ኦርኬስትራውን ተቀላቅለዋል።ጋሽ ግርማም ሰፈር ውስጥ አብሮአቸው የሚያደምቅ ድምጸ መረዋ ነበርና ለአለቃቸው ሻለቃ ደመቀ ስለብቃቱ ይመሰክራሉ።ሻለቃውም ቆፍጠን ባለ የወታደር ትእዛዝ "አንተ ና እስቲ ዘፈን ታውቃለህ አሉ እስቲ ዝፈን" የሚል ቀጭን ትዕዛዝ ቢያሰሙም ከሰፈሩ በአሸዋ መኪና ተጭነው እንዳልሄዱ ተግደረደሩ።ከአፍታ ማፈር በኋላ ሰፈር ውስጥ ከሚዘፍኗቸው ዘፈኖች አንዱን ቢዘፍኑ ወዲያው ተቀጠሩ።

ከሰፈር ጓደኞቻቸው እኩል የ50 ብር ደሞዝተኛ ሆኑ።መጀመሪያ ከዛ ሃምሳ ብር ደሞዝ ላይ እየተቆረጠ እዛው ለፖሊስ አባላት የሚዘጋጅ ምግብ እየበሉ በልምምድ ይውላሉ።በሂደት ለሙዚቀኛ ወሳኙ ነገር ምግብ ነው ተብሎ በመታመኑ ከክፍያ ነጻ የጣመ የላመ ምግብ የሚበሉበት ሁኔታ ተመቻቸ።ማደሪያውም እዛው ተመቻችቶላቸው ሰፊ ጊዜ ወስደው መለማመድ ቀጠሉ።በተለይ ለመጀመሪያ ጊዜ ለአዲስ ዓመት መድረክ ላይ የሚቀርብ አፍሪካ የዓለም ዘውድ የሚሰኝ በተስፋዬ አበበ የተደረሰ ግጥምና ዜማ ተሰጥቷቸው ጥናቱን ተያያዙት፡፡

የፖሊስ ቤት ሁሉ ነገር ተመችቷቸዋል።ምግቡ ማረፊያ መገኘቱ ደሞዝተኛ መሆናቸው እንዲሁም የሚወዱትን ሙዚቃ የመሥራት እድሉ አስደስቷቸዋል።ግን እሳቸው ጋር ባይደርስም ያጠፉ የፖሊስ አባሎች ሲቀጡ በጭቃ ላይ ተንከባለሉ ተብለው ሲንከባለሉ እንዲሁም ጭቃ ሲያቦኩ ሲያዩ ሆዳቸው ባር ባር እያለው ይሄ ቅጣት እሳቸው ጋር እንዳይደርስ በጸሎት ፈጣሪያቸውን ይማፀኑታል።

ከዕለታት አንድ ቀን የልምምድ ቀን ቢሆንም ከሳቸው ከፍ ያለ ሰው የእረፍት ቀን ነው ስላላቸው በማረፊያቸው ከጓደኞቻቸው ጋር እያወጉ ተኝቶ ማርፈድን ምርጫ አድርገዋል።እሳቸው ደግሞ ከሃምሳ ብር ደሞዛቸው ቀንሰው በገዟት ቄንጠኛ ነጭ ሱሪ አልጋቸው ላይ ጋደም ብለው ያወጋሉ።ሆኖም ትልቅ ዱላ ይዞ የፖሊስ ዩኒፎርሙን ለብሶ በቁጣ ማረፊያቸው የደረሰው መኮንን ጓደኞቻቸውን በያዘው በትር መቶ ነጭ እንደለበሱ በሥራ ቀን ተኝታችሁ አረፈዳችሁ ብሎ የፈሩት ጭቃ ላይ እንዲንከባለሉ ፈረደባቸው።

እንደፈሩት አልቀረም በሰው የፈሩትና አታጋጥመኝ ብለው ለፈጣሪያቸው የነገሩት ጭቃ ላይ ተንከባለሉ። በእሱም አልበቃም ቅጣቱ ግጫ ሲነቅሉ አመሹ።ያኔውኑ ሙዚቃ እንዲህ ካመጣ ብለው ልባቸው ዋለለ።ግን የተሰጣቸውን ሙዚቃ

**የአፍሪካ የዓለም ዘውድ መሆንሽን አውቃለሁ**
**እኔን መስክር ቢሉኝ ከልቤ እምላለሁ**

መለማመዱ ላይ በረቱ።ሙዚቃውን ለአዲስ ዓመት ብሔራዊ ትያትር በነበረው ዝግጅት ላይ በተገቢው መልኩ አቀረቡ።በቀጣይ በክፍለ ሀገር የመዞር ፕሮግራም ተይዞ የነበረ ቢሆንም ከካምፕ እግሬ አውጭኝ ሲሉ ወደ ሰፈራቸው ገሰገሱ።የነጭ ሱሪያቸው መበላሸት ይበልጥ ልባቸውን አጨክኖት ሳይሆን አይቀርም ከካምፑ እንደወጡ ሳይመለሱ ቀሩ፡፡

ከቆይታ በኋላ የቀድሞው የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ትያትር ቤት የአሁኑ ብሔራዊ ትያትር ሙዚቀኞችን ለመቅጠር ማስታወቂያ ማውጣቱን ይሰማሉ።ውድድሩ ላይ የጥላሁን ገሰሰን ለወሬም አይመች ዜማን በግሩም ሁኔታ በማቀንቀናቸው ትያትር ቤቱን ሊቀላቀሉ ችለዋል።

**ምነው ተለየሽኝ መስከረም ሳይጠባ**
**እንቁጣጣሽ እያልን ሳናጌጥ በአበባ**

በትያትር ቤቱ በነበራቸው አጭር ቆይታ ከሠሯቸው ግሩም ሥራዎች መካከል ይገኝበታል።ዘፈኑ ከግጥም፣ ከዜማው እና ከቅንብሩ የተሳካ መሆን እኩል መሀል ላይ የተካተተው ፉጨት የተለየ ውበት ሰጥቶታል።በወቅቱ ፉጨቱ ከመድረክ ተለቆ እንጂ እሳቸው የሚያፏጩ የማይመስላቸው በርካታ ታዳሚዎች እንደነበሩና ለማረጋገጥ መድረክ ላይ ፊት ለፊት የሚቀመጡ ታዳሚዎች እንደነበሩ ያስታውሳሉ።በወቅቱ እንኳን የዘፈኑ አካል ሆኖ ቀርቶ እንዲሁም ማፏጨት ይወዱ ነበርና በግሩም ሁኔታ ያፏጩ ነበር።በግሩም ሁኔታ የማፏጨታቸውን ሚስጥር "የጉርምስና ትንፋሽ" ይሉታል።

ትያትር ቤቱ በ1954 ዓ.ም የእንቁጣጣሽ በዓልን አስመልክቶ ባደረገው የአዳዲስ ዜማዎች ውድድር ጋሽ ግርማ ያቀረቡት የኔ ሃሳብ አሸናፊ ነበር።በወቅቱ ከ70 በላይ አዳዲስ ዜማዎች ለውድድር ቢቀርቡም በአዘጋጆቹ ታምኖባቸው ለውድድሩ የቀረቡት 21 ነበሩ።በወቅቱ ከቀረቡት 21 አዳዲስ ዜማዎች መካከል በአሁኑ አንጋፋ በያኔው ወጣት ድምጻዊ ግርማ ነጋሽ የተቀነቀነው ግጥሙ በደራሲ ጌታቸው ደባልቄ ዜማው በካሳ ወልዴ የተደረሰውና በነርሲስ ናልባንዲያን የሙዚቃ አቀናባሪነት በትያትር ቤቱ የኦርኬስትራ አባላት የታጀበው የኔ ሃሳብ ለአሸናፊነቱ የ300 መቶ ብር ሽልማት ተበርክቶለታል፡፡

ጋሽ ግርማ ከ300 ብር ውስጥ ድርሻዬ ብለው ያሰቡትን 50 ብር ወስደው ከተቀረው 250 ብር የራሱን ድርሻ እንዲወስድና ለሌሎች ባለድርሻዎች እንዲያከፋፍል ለዜማ ደራሲው ካሳ ወልዴ አስረክበው ጉዞ ወደ ፊት በር።መለስ ብለው ሲያስቡት ከሽልማት ድርሻቸው 50 ብር ላይ ያልተጋበዘ የሰፈር ጓደኛ አልነበረም፡፡

**የኔ ሃሳብ ባንተ ፍቅር ተመርዞ**
**ቢያስቸግረኝ እጅግ ልቤን አስተክዞ**
**ተረታሁኝ ባንቺ ፍቅር ተይዤ**
**አሀሀሀ ሀሀሀሀሀ**

**ቁጭ ብዬ ቀረሁልሽ ተክዤ**

የተሰኘችው ድንቅ ዜማ የጋሽ ግርማ መታወቂያ የተለየች ምልክት ነች።በአጭር ጊዜ የትያትር ቤት ቆይታቸው ከየኔ ሃሳብ በተጨማሪ ምነው ተለየሽኝ፣ አልበቃኝም ገና ጨርሶ፣ የሸማኔ ፍቅር፣ አዝናለሁ ስላንቺ የተሰኙ ሙዚቃዎችን አቀንቅነዋል።በድምጹ ውበት በርካቶችን መማረክ ቢችልም ቤተሰቦቹ ግን የሱን ድምጻዊነት አምነው መቀበል አልቻሉም።በወቅቱ በአብዛኛው ማሕበረሰብ ዘንድ ዘፋኝነት አዝማሪ ተብሎ የተናቀ ሙያ ነበርና ቤተሰቦቹ በሱ ዘፋኝ መሆን አልተደሰቱም።በዚህ የተነሳም ጋሽ ግርማ በዘፈን ያገኘው ብር ከቤተሰብ ብር ጋር እንዳይቀላቀል ሁሉ ይባል ነበር።በተለይም የታላቅ ወንድማቸው የቀድሞ የኢትዮጵያ ሦስተኛ አብዮታዊ ሠራዊት አዛዥ ጀነራል ሙላቱ ነጋሽ ዛቻ ቢበረታባቸው ጋሽ ግርማ በ1955 ዓ.ም ከሚወዷት ሙዚቃ ተሰናበቱ።

በመቀጠልም የኮካ ኮላ የለስላሳ መጠጦች ድርጅትን በሽያጭ ሠራተኝነት ማገልገል።በ1959 ዓ.ም በኢትዮጵያ ማስታወቂያ ሚኒስቴር የትራንስፖርት ኃላፊ በመሆን ሥራ ጀመሩ።በወቅቱ የማስታወቂያ ሚኒስቴርና የኢትዮጵያ ሬዲዮ አንድ ተቋም በመሆኑ የቢሮው ኃላፊዎች ጋዜጠኛ ሆነው መሥራት እንደሚችሉ በማመናቸው የኢትዮጵያ ሬዲዮ የስፖርት ክፍል ባልደረባ በመሆን ጋዜጠኝነትን ሀ ብለው ጀመሩ።በዚህ ጉዟቸውም በጣቢያው ከሳቸው ቀድመው የስፖርት ክፍል ጋዜጠኞች የነበሩት ይንበርበሩ ምትኬ፣ ደምሴ ዳምጤና፣ ጎርፍነህ ይመር ሙያውን በማስለመድ እንደረዷቸው ያስታውሳሉ።ለዚህም በዘፈን የተገራው ድምጹ የአድማጮችን ትኩረት ሰቅዞ በመያዝ አስተዋጽኦው የጎላ ነበር፡፡

ከሙዚቃ ጋር ካለው ቅርበት የተነሳም በጣቢያው አርብ ምሽት ይቀርብ የነበረው የባህል ሙዚቃ አዘጋጅና አቅራቢ በመሆን ሰርቷል።ድምጹ በተፈጥሮ የታደለ መረዋ ነበርና በሬዲዮ የጋዜጠኝነት ዘመኑ አድማጭን ሰቅዞ የሚይዝ ግሩም ጋዜጠኛ ነበር።ጡረታ እስኪወጣ ድረስ ከ30 ዓመት በላይ በማስታወቂያ ሚኒስቴር አገልግሏል፡፡

በ1985 ዓ.ም ዘመን ተሻጋሪ ሥራዎቹን በካሴቴት አሳትሞ ለአድማጭ አቅርቧል።የእሱ ሥራዎች የታዳሚውን ቀልብ ብቻ ሳይሆን የድምጻውያንንም ልብ ያሸፍታሉ። ለዚህም ይመስላል በርካታ ሥራዎቹ በሌሎች ድምጻውያን በድጋሚ ተዚመዋል።62 ዓመት የሞላት የኔ ሃሳብ አብነት አጎናፍር፣ እንደሻው ተስፋዬና ሞገስ መብራቱ በተለያየ ጊዜ በድጋሚ ዘፍነውታል።

**እንገናኛለን አልቆረጥኩም ተስፋ**
**ብደነዝዝ እንኳን ቆሜ ባንቀላፋ**

በ1955 ዓ.ም የወጣውን እንገናኛለን የተሰኘ ተወዳጅ ሥራቸውን ወደ አምስት የሚጠጉ ድምጻውያን ተጫውተውታል።ከእነዚህ ውስጥ ሰላማዊት ነጋ፣ ብጽአት ስዩም፣ እያዩ በሌና ማርታ አሻጋሪ ይገኙበታል።በአንድ ወቅት ዘፈኑን በርካታ ሰው በድጋሚ መጫወቱን ተጠይቀው ሲመልሱ "እንገናኛለንን ያልሞከረው የለም፤ መለኩሴ ወይም ቄስ ካልሆነ በቀር ብዙ ሰው ሰርቶታል" ብለዋል።አልበቃኝም ገና ጨርሶ የተሰኘው ዘፈናቸውን ድምጻዊ ጌታቸው ካሳ ደግሞ ተጫውቶታል፡፡

ጡረታ ከወጡ በኋላ የጋሽ ግርማ የሙዚቃ ብቃት አብሮአቸው ስለቆየ በአድናቂዎቻቸው አማካኝነት የተለያዩ መድረኮች ላይ በሦስት ዓመት የሙዚቃ ቆታቸው የሰሯቸውን ሥራዎች እያቀረቡ ቆይተዋል።ከዚህ በተጨማሪም በራሳቸው መኪና ለተማሪዎች የሰርቪስ አገልግሎት በመስጠት ሕይወታቸውን ሲመሩ የቆዩ ቢሆንም ያለፉትን ሁለት ዓመታት ይሄን ሥራቸውን አቋርጠዋል።እድሜያቸው ሰማንያን ቢሻገርም አሁንም የድሮ ሥራቸውን የሚያዳምጥ እሳቸውን መድረክ ላይ ሲያይ የሚደሰት በርካታ ታዳሚ አላቸው፡፡

የኢትዮጵያውያን በቁም የማመስገን ባህል አነስተኛ ነው በማለት በርካቶች ሲወቅሱ ቢታይም፤ ነሀሴ 16 ቀን 2015 ዓ.ም በአሜሪካ የሚኖሩ የኪነጥበብ ባለሙያዎች በአሜሪካ ቨርጂንያ ጋሽ ግርማን «ስለአገልግሎትህ እናመሰግናለን» ያሉበትን የምስጋና መረሀ ግብር አሰናድተዋል።በፕሮግራሙ ላይ የጋሽ ግርማ የልብ ወዳጅ ድምጻዊ መሀሙድ አሕመድን ጨምሮ በርካታ ባለሙያዎች ተገኝተው ድምጸ መረዋውን አመስግነዋል።

# ዓለም አቀፍ



## ኢራን ሂጃብ የማይለብሱ ሴቶችን በ10 ዓመት እሥራት ልትቀጣ ነው

በጋዜጣው ሪፖርተር

ኢራናውያን ሴቶች “አግባብ ያልሆነ አልባሳት” ለብሰው ከተገኙ የ10 ዓመት እሥራት ከፊታቸው ይጠብቃቸዋል ተብሏል።

የሀገሪቱ ምክር ቤት የአልባሳት ደንብን የማይከተሉ ልጃገረዶችንና ሴቶችን የእስራት ጊዜና ቅጣትን ከፍ የሚያደርግ አወዛጋቢ አዋጅ አጽድቋል።

በአዋጁ ያላግባብ የለበሱ የተባሉ ሴቶች እስከ 10 ዓመት በሚደርስ እሥራት ይቀጣሉ። የፍርድ ቤት ሂደቱም እስከ ሦስት ዓመት ሊወስድ ይችላል ተብሏል። ረቡዕ የጸደቀው አዋጅ በህዝብ መሰብሰቢያ ቦታዎች ያለአግባብ የሚለብሱ ሴቶች በሀገሪቱ ወንጀል ሕግ መሠረት አራተኛ ደረጃ ቅጣት ይጠብቃቸዋል። በዚህም እስከ 10 ዓመት የሚደርስ እሥራትና ከሦስት ሺህ እስከ ሰባት ሺህ ዶላር የሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ይጠብቃቸዋል።

ሆኖም አዋጁ ሕግ እንዲሆን በጠባቂዎች ምክር ቤት መጽደቅ ይጠበቅበታል። ርምጃው ማሻ አሚኒ የተባለች ሴት በፖሊስ ጥበቃ እያለች ሕይወቷ ማለፉን ተከትሎ በሀገሪቱ ከባድ ተቃውሞ በተቀሰቀሰ ከዓመት በኋላ የተወሰደ ነው።

በተቃውሞው ሴቶች ሂጃባቸውን በማቃጠልና በመወርወር መንግሥትን አሻፈረኝ ብለዋል ሲል የዘገበው አል ዓይን ኒውስ ነው።

## የሱዳኑ መሪ ጦርነቱ ወደ ጎረቤት ሀገራት ሲስፋፋ ይችላል ሲሉ በተመድ ስብሰባ ላይ ተናገሩ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የሱዳኑ መሪ በሀገራቸው የተከሰተው ጦርነት ወደ ጎረቤት ሀገራት ሊስፋፋ ይችላል ሲሉ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባዔ ላይ ተናገሩ።

የሱዳን ጦር መሪ ጀነራል አብድል ፋታህ አል-ቡርሃን ዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ በጀነራል ሐምዳን ዳጋሎ የሚመራውን ፈጥኖ ደራሽ ኃይል ሽብርተኛ ቡድን ብሎ እንዲፈርጀውም ጥያቄ አቅርበዋል። በሌላ በኩል የፈጥኖ ደራሹ ኃይል መሪ ጀነራል ሃምዳን ደጋሎ የተኩስ አቁም ለማድረግ ዝግጁ መሆናቸውን ተናግረዋል።

ሱዳን ከባለፈው ሚያዚያ ጀምሮ በእርስ በርስ ጦርነት የተዘፈቀች ሲሆን በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ተገድለዋል፤ በሚሊዮን የሚቆጠሩት ደግሞ ሀገር ጥለው ተሰደዋል። በአውሮፓውያኑ 2021 ሁለቱ መሪዎች ተባብረው መፈንቅለ መንግሥት ማወጃቸው ይታወሳል። ነገር ግን በሁለቱ መካከል ያለው የሥልጣን ሽኩቻ ጦር እንዲማዘዙ አድርጓቸዋል።

ሐሙስ ዕለት ለተባበሩት መንግሥታት ንግግር ያደረጉት ጀነራል አል ቡርሃን የሳቸው ፓርቲ የሰላም ስምምነት ለማድረግ ዝግጁ መሆኑን ገልጠዋል።

“ጦርነቱን ለማቆምና እና የሕዝባችንን ስቃይ ለመግታት ዝግጁ ነን” ነገር ግን ፈጥኖ ደራሽ ኃይሉ ፈቃደኛ አይደለም ብለዋል። ነገር ግን በቅፅል ስማቸው ሄሜቲ ተብለው የሚታወቁት ተቀናቃኛቸው ጀነራል ደጋሎ ለተመድ በላኩት ተንቀሳቃሽ ምስል ግጭቱን በንግግር ለመፍታት ዝግጁ መሆናቸውን ተናግረዋል።

ሁለቱ የጦር ጀነራሎችን ልዩነቶቻቸውን በንግግር እንዲፈቱ አሜሪካ፣ ሳዑዲ አረቢያ እና ግብጽ ያደረጉት ጥረት ሳይሳካ ቀርቷል። የፈጥኖ ደራሹ ኃይል አባላት በመላው ሱዳን መሰማራታቸውንና ጀነራል አል ቡርሃን እንደ ስጋት ማየታቸውን ተከትሎ ነው የሱዳን የእርስ በርስ ጦርነት ባለፈው ሚያዚያ የፈነዳው።

የመጀመሪያዋን ጥይት ማነው የተኮሰው የሚለው አከራካሪ ቢሆንም ግጭቱ በፍጥነት አይሎ በመላ ሀገሪቱ ተስፋፍቷል። በጦርነቱ ምክንያት ቢያስን 7500 ሰዎች መገደላቸውን አክሌድ የተሰኘው መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ያወጣው መረጃ ያሳያል፤ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ደግሞ ተፈናቅለዋል።



ከፍተኛ ውጊያ ከሚያስተናግዱ የሱዳን ከተሞች መካከል መዲናዋ ካርቱም አንደኛዋ ናት፤

በአውሮፓውያኑ 2021 የተፈፀመውን መፈንቅለ መንግሥት ተከትሎ ጀነራል አል ቡርሃን የሱዳን መሪ ሆነው ሲያገለግሉ ቆይተዋል። ዓለም አቀፍ ዕውቅና ለማግኘት በመላው ዓለም ሲዘዋወሩም ከርመዋል። ለተባበሩት መንግሥታት ባደረጉት ንግግራቸው ፈጥኖ ደራሽ ኃይሉ ከሩሲያ ቫግነር ቡድን ጋር ያለውን ግንኙነትም አንስተዋል።

ቅጠረኛው ቫግነር ቡድን በሱዳን ጨምሮ በማዕከላዊ አፍሪካ ሪፐብሊክ፣ ሊቢያ፣ ሞዛምቢክ እና ማሊ እንደሚንቀሳቀስ ይታመናል።

“የጦርነቱ አደጋ አሁን ለጎረቤት ሀገራትም እና ለመላው ዓለም ሰላምና ፀጥታ ስጋት እየሆነ ነው። አማፂያኑ ሕጋዊ ያልሆኑ እና ሽብርተኛ ከተባሉ ሀገራትና ድርጅቶች ድጋፍ እያገኙ ነው” ብለዋል ሲል የዘገበው ቢቢሲ አማርኛ ነው።


## የጨረታ ማስታወቂያ
## የጨረታ ማስታወቂያ ቁጥር ኦ/ፖ/ኮ ግ/ጨ/02/ 2016

የኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽን ለ2016 በጀት ዓመት ለክልሉ ፖሊስ አባሎች አገልግሎት የሚውል የተለያዩ የፖሊስ ደንብ ልብሶች የክብረ በዓል ልብስ(ግራውንድ ዩኒፎርም የፖሊስ ረጅም እና አጭር ጫማዎች እና የፖሊስ ካልሲዎችን ለመግዛት በዘርፉ ከተሰማሩ ህጋዊ ተጫራቾች በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡

በዚሁ መሰረት ፖሊስ ኮሚሽኑ የሚገዛቸው እቃዎች ከዚህ በታች በሎት ተዘርዝረው ቀርበዋል።

1.ሎት አንድ፡-የተለያዩ የፖሊስ ደንብ ልብሶች
2.ሎት ሁለት፡-የክብረ በዓል ልብስ (ግራውንድ ዩኒፎርም)
3.ሎት ሶስት፡-የተለያዩ የፖሊስ ረጅም እና አጭር ጫማዎች
4. ሎት አራት፡-የፖሊስ ረጅም እና አጭር ካልሲዎች

በመሆኑም በዘርፉ የተሰማሩ ብቃት ያላቸው ተወዳዳሪዎችን ለውድድር ይጋብዛል፡፡

1. ተጫራቾች ህጋዊ የታደሰ ንግድ ፍቃድ ያላቸው፡፡
2. የዘመኑን ግብር የከፈሉ፡፡
3. በአቅራቢዎች ዝርዝር የተመዘገቡ መሆናቸውን የሚገልጽ ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው፡፡
4. ማንኛውም ተጫራች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና 2% በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ ማቅረብ አለባቸው፡፡
5. የጨረታ ሰነዱን የጨረታው ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በተከታታይ 15 (አስራ አምስት) የስራ ቀናት ከፋይናንስ መምሪያ በመቅረብ የማይመለስ 200(ሁለት መቶ) ብር በመክፈል መግዛት ይችላሉ፡፡
6. አሸናፊ ድርጅት ያሸነፈባቸውን ዕቃዎች በራሱ ወጪ የማጓጓዣ መጫኛ እና ማውረጃ ወጪዎችን ሸፍነው የኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽን መጋዘን ቢሾፍቱ በሚገኘው ማስረከብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
7. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዳቸውን የሚያስገቡበት የመጨረሻ ቀነ ገደብ 08/02/2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ይሆናል፡፡
8. ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎ ቻቸው በተገኙበት 08/02/2016 ዓ.ም በኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽን የመሰብሰቢያ አዳራሽ 4፡30 ሰዓት ይከፈታል፡፡
9. ማንኛውም ተጫራች ዋጋ ሲሞላ ቫትንና ሌሎችን ታክስ፤ትራንስፖርት የመጫኛ እና ማውረጃ ዋጋ ጨምሮ በትክክል መሙላት አለበት ይህ ካልሆነ ግን የቀረበ ዋጋ ሁሉንም ወጪ አካቶ እንደተሞላ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡
10. ኮሚሽኑ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

አድራሻ ኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚን አ/አባባ ክ/ከተማ ጉለሌ ወረዳ 02 ስድስት ኪሎ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከፍ ብሎስልክ ቁጥር 0118787093

### የኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽን



## ግልጽ የጨረታ ማስታወቂያ የጨረታ ቁጥር፡- አ.አ. 01/2016

የአማራ ሕንጻ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ውል ይዞ ለሚገነባቸው የአሚኮ ደሴ ቅር/ጽ/ቤት፣ ለቆቦ እና ግዳን ከተማ ሆስ/ግን/ፕሮጀክቶች አገልግሎት የሚውል የተለያዩ ዲያሜትር ያላቸውን የአርማታ ብረቶች ደ/ዘይት ከተማ ከሚገኘው የአቢሲንያ ኮልድ ሮሊንግ የብረት ማም/ፋብሪካ በመጫን ወደ ደሴ ከተማ አጓጉዘው ለማድረስ የሚችሉ በትራንስፖርት ዘርፉ የተሰማሩና ህጋዊ ፈቃድ ያላቸውን የደረቅ ጭነት አገልግሎት ሰጪ ትራንስፖርተሮችን በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ የአገልግሎት ግዥ ለመፈጸም ይፈልጋል። ስለዚህ በጨረታው ለመወዳደር የሚፈልጉ ተጫራቾች መሳተፍ የሚችሉ መሆኑን እየገለጽን የግልጽ ጨረታው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ተከታታይ ቀናት ውስጥ የማይመለስ ብር 300.00/ሶስት መቶ ብር/ በመክፈል የጨረታ ሰነዱን መውሰድ የምትችሉ መሆኑን እያሳወቅን፡፡ የጨረታ ውድድሩ በድምር ውጤት የሚታይ ሲሆን እንዲጓጓዙ ለተገለጹ የአርማታ ብረት ዓይነቶች በሙሉ የማጓጓዣ ዋጋው መሙላት እንዳለበት እያሳሰብን፡፡

1. ተጫራቾች የመጫረቻ ሰነዶቻቸውን በዋና እና በቅጅ በመለየት በ2 በተለያዩ ፖስታዎች በጥንቃቄ በማሸግ ጨረታው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 15ኛው ቀን (15 ተከታታይ ቀናትን በመቁጠር) ከቀኑ 8፡00 ሠዓት ድረስ ብቻ አዲስ አበባ ለገሃር በሚገኘው አመልድ-ኢትዮጵያ ሕንጻ 7ኛ ፎቅ በማስ/ጽ/ቤቱ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል። 15ኛው ቀን የሥራ ቀን ካልሆነ በሚቀጥለው የሥራ ቀን እስከ ቀኑ 8:00 ሠዓት ድረስ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
2. ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ጨረታው በተዘጋበት እለት ከቀኑ 8:30 ሠዓት በድርጅቱ የአዲስ አበባ ማስ/ጽ/ቤት ቢሮ ቁጥር 02 የሚከፈት ይሆናል።
3. በሚቀርበው የጨረታ ሰነድ መሟላት ያለበት
3.1. በዘርፉ ስለመሰማራታቸው የንግድ ስራ ፈቃድና ለዘመኑ ስለመታደሱ ማረጋገጫ ኮፒ፣
3.2.ማንኛውም የወቅቱን የመንግስት ገቢ ግብርና ሌሎች ግዴታዎችን ስለመወጣት ማረጋገጫ ኮፒ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
3.3. የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር/TIN/ ኮፒ፣
3.4. የጨረታ ማስከበሪያ የጠቅላላ ዋጋውን 2% ከታወቀ ባንክ በተረጋገጠ ሲ.ፒ.ኦ. ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና Amhara Building Works Construction Enterprise በሚል ስም ተዘጋጅቶ መቅረብ ይኖርበታል፣
3.5. በውድድሩ አሸናፊው የሚሆነው የትራንስፖርት ሰጪው ድርጅት በጉዞ ላይ በሚፈጠረው ብልሽት ወይም ጉድለት ተጠያቂ ይሆናል። በጭነት ወቅት የተረከበው ዝርዝር የብረት ዓይነት መሰረት ትክክለኛ መሆኑ ታይቶ እየተረጋገጠ ሲራገፍ ብቻ ርክክቡ የሚፈጸም ይሆናል፡፡
3.6. በጨረታው ቅር የተሰኘ ተጫራች የጨረታ ውጤቱ ከተገለፀለት ቀን ጀምሮ በሶስት የስራ ቀናት ብቻ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡
4. ተወዳዳሪ ትራንስፖርት አቅራቢ ድርጅቶች ከትራንስፖርት ፈቃድ ሰጪው ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ፣ የተሽከርካሪ ዝርዝር የሰሌዳ ቁጥርና ሊብሬ ሰርተፍኬት ኮፒ አያይዞ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።
5. የጨረታ አሸናፊው ለአሸነፈበት የማጓጓዣ ዋጋ ጠቅላላ ድምር ውጤት 10% የውል ማስከበሪያ የሚሆን የመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና በባንክ በተረጋገጠ ሲ.ፒ.ኦ. ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና ያስይዛል፡፡
6. በጨረታ ሰነዱ የተሞላው ዋጋ ጨረታው ከተከፈተበት ቀን ጀምሮ ለአርባ አምስት ቀናት ፀንቶ ይቆያል፡
7. የጨረታ ተወዳዳሪዎች በሌሎች ተወዳዳሪዎች ዋጋ ላይ ተንተርሶ ማቅረብ አይችሉም፡፡
8. የትራንስፖርት አገልግሎት ገዥ ድርጅቱ በጨረታው አሸናፊ ከሆነው አገልግሎት ሰጪ ድርጅት የጨረታውን ይዘት ሳይቀይር ከሚገዛው አገልግሎት ጠቅላላ መጠን ላይ ለገዥ ጠቃሚ ነው ብሎ ከታመነ ውል ሲይዝ 50% ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል፡፡ ከውል በኋላም አቅርቦቱ ሲፈጸም 50% ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል፡፡
9. ተጫራቾች ለሚወዳደሩባቸው የትራንስፖርት አገልግሎት ማቅረቢያ ፕሮጀክቶች ብረቱን በጥንቃቄ በማጓጓዝ ግንባታው ከሚከናወንበት ፕሮጀክት ድረስ በራሳቸው ወጪ አጓጉዘውና ቆጥረው ያስረክባሉ፡፡
10. ከጨረታ ሳጥን መዝጊያ ቀንና ሰዓት ዘግይቶ የቀረበ ተጫራች ተቀባይነት አይኖረውም፡፡
11. ገዥ ድርጅቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው፡፡ ይህም ሲባል ጨረታው በመሰረዙ ተጫራቾች በጨረታው ለመወዳደር ላወጡት ወጪ ድርጅቱ ኃላፊነት አይወስድም፡፡
12. ለማንኛውም ተጨማሪ ማብራሪያ በአካል በመገኘት ወይም ከዚህ በታች በተጠቀሱት ስልክና ፋክስ መጠየቅ ይችላሉ

ስልክ ቁጥር፡ 0111265652/0913158074/0930352410 ፋክስ ቁጥር፡ 0111265338

### በአማራ ህንፃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት የአዲስ አበባ ማስ/ጽ/ቤት

# ስፖርት

# ከጎደፉ የስፖርት ታሪኮች ማህደር

ብርሃን ፈይሳ

ኢንስ ጌፔል እአአ ከ1980ዎቹ ስኬታማ ከሚባሉ የአጭር ርቀት ሴት አትሌቶች መካከል አንዷ ነበረች፡፡ ጀርመናዊቷ አትሌት ከምትታወቅበት ከ100 ሜትር እስከ 4በ 100 ሜትር የዱላ ቅብብል ውድድር ባለፈ በዝላይ ስፖርቶችም ስኬታማ ነበረች፡፡ ባስመዘገበቻቸው ሰዓቶች ምክንያትም ስሟ በክብረወሰን መዛግብት ላይ ሰፍሮ ቆይቷል፤ አሁን ግን ድምቀታቸው ወይቦ እንዲሰረዝ ተደርጓል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ «በስፖርት አበረታች ንጥረ ነገሮች የተመረዙ ውጤቶች በመሆናቸው ነው» ስትል ራሷ ምስክርነቷን ትሰጣለች፡፡

እአአ በ1980ው የሞስኮ ኦሊምፒክ በውሃ ዋና ውድድር የወርቅ እና ብር ሜዳሊያዎችን ያጠለቀችው ጀርመናዊት ዋናተኛ ፔትራ ቼንደርም «በክብር መዛግብቱ ላይ የሰፈሩት ተፍቀው መዝገቡ እንዲጸዳ እፈልጋለሁ» ስትል ይህንኑ ሃሳብ ትደግማለች፡፡ እነዚህን አትሌቶች ጨምሮ 10ሺ የሚሆኑ ወንድ እና ሴት ስፖርተኞች በወቅቱ ሁለገብ የስፖርት የበላይነቱን ለመያዝ ሲባል በሚስጥር አበረታች መድሃኒቱን እንዲወስዱ ተደርገዋል፡፡ አትሌቶቹ ምንም በማያውቁት የአበረታች ንጥረ ነገር ተጠቂ ከመሆናቸው ባለፈ የልፋታቸውን ተነጥቀው ባዶ እጃቸውን ሊቀሩ የግድ ሆኗል፡፡ አሁንም ድረስ በሕይወት ያሉትም የደረሰባቸውን የጤና እክል በማስታመም ላይ ናቸው፡፡

ምስራቃዊቷ ጀርመን ግን ዜጎቿ ላይ በደል ትፈጽም እንጂ ተሳክቶላት እአአ በ1976ቱ የሞንትሪያል ኦሊምፒክ 40 የወርቅ ሜዳሊያዎችን በማስመዝገብ ሩሲያን ተከትላ ሁለተኛ ደረጃ ላይ መቀመጥ ችላለች፡፡ ከአራት ዓመት በኋላም በተመሳሳይ የሞስኮ ኦሊምፒክ ላይ በሰበሰበቻቸው ሜዳሊያዎች ብዛት ሁለተኛውን ደረጃ ልትይዝ ችላለች፡፡ ከስፖርቱ ዓለም ጥቁር ነጥቦች መካከል አንዱ የሆነው ይህ ታሪክ ምስራቅ ጀርመንን ከሁሉ በላይ የማድረግ ዓላማን ባነገቡ አላዋቂዎች የተፈጸመ ሲሆን፤ የስፖርትን ታሪክ ካጎደፉ ጉዳዮች መካከል ይጠቀሳል፡፡



ነገሩ እንዲህ ነው፤ ጀርመን ለሁለት ከተከፈለች በኋላ ምዕራብ ጀርመን እአአ በ1960ዎቹ በስፖርት ተጽዕኖ ፈጣሪ ሀገር ነበረች፡፡ እአአ ከ1970 በኋላ ባሉት ዓመታት ግን ምስራቅ ጀርመን ድራማዊ የሆነ ለውጥ በማምጣት የውድድሮች ቁንጮ ሆና ብቅ አለች፡፡ በእርግጥ ነገሩ ሀገሪቷ በስፖርቱ ዓለም ብልጫ እንድታገኝ ከማድረግ ያለፈ ዓላማ የነበረው ሲሆን፤ ሁኔታውን ተጠቅሞ የበላይነትን የመገንባት ፖለቲካዊ ፍላጎትም ነበረበት፡፡ እአአ ከ1972ቱ ሙኒክ ኦሊምፒክ አንስቶም በምታስመዘግበው ውጤት ከእነ አሜሪካ እና ሩሲያ ጋር ለመሰለፍ በቃች፡፡ በወቅቱ 16 ሚሊዮን ህዝብ የሚወክለው ብሄራዊ ቡድኗ ኦሊምፒክን በመሰሉ ዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ ያለምንም ተቀናቃኝ በውጤታማነታቸው ቁንጮ የሆኑትን አሜሪካንና ሩሲያን በመብለጥ ምስራቅ ጀርመንን ከድል ማማ ላይ ለማስቀመጥ ሲባል የስፖርቱ አመራሮች በስፖርቱ ዓለም እጅግ አስነዋሪውን ጉዳይ ፈጸሙ፡፡

በዚህ ሁኔታ ምስራቅ ጀርመን በስኬታማነቷ ዓመታን ካስቆጠረች በኋላ ለሁለት የተከፈለችው ሀገረ ጀርመን ተዋህዳ በመካከላቸው የተገነባው ግንብም ፈረሰ፡፡ ነገር ግን ጀርመን የሚለው ስም ከኦሊምፒክ የደረጃ ሰንጠረዥ አናት ላይ ለመታየት የወሰደበት 35 ዓመታት እንደሆነ ከዩኔስኮ ዲጂታል ላይብረሪ የተገኘው መረጃ ያብራራል፡፡ በ1970ዎቹና 80ዎቹ የሆነው ታውቆ በምርመራ ሊለይ የቻለውም ከዓመታት በኋላ ሲሆን፤ ተጠቂዎች የገንዘብ ካሳ ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት እንደነበራቸው የተረጋገጠባቸው ጥፋተኞች ደግሞ ለእስር ሊዳረጉ ችለዋል፡፡

የወቅቱ ምርጥ አትሌት የነበረችው ጌፔል «ሕይወታችንን ሰረቁ፤ አካላቶቻችንንም እንደ ተራ ዕቃ ቆጠሩት» ትላለች ስለነገሩ ስታብራ፡፡ አትሌቶቹ አበረታች ንጥረ ነገሮቹን በሃኪሞች ትዕዛዝ «የቫይታሚን እንክብሎች ናቸው» በሚል ነበር እንዲወስዱ የተደረገው፡፡ በጊዜ ሂደትም በዚህ አደገኛ ነገር ተጠቂ የሆኑ አትሌቶች የተለያዩ ለውጦችን በጡንቻዎቻቸው፣ በድምጻቸው፣ በጸጉራቸው እንዲሁም በተለያዩ የአካል ክፍሎቻቸው ላይ ማስተዋል ችለዋል፡፡

ለአብነት ያህል ሄዲ ክሪገር(አሁን ላይ አንድሬስ ክሪገር) የተሰኘችው በሴቶች የአሎሎ ውርወራ ተወዳዳሪ አትሌት በተሰጣት አበረታች ንጥረ ነገር በአካሏ ውስጥ በርካታ የወንድ ሆርሞን እንዲመነጭና በጡንቻዎቿም ላይ በርካታ ለውጦች እንዲታዩባት ምክንያት ሆኗል፡፡ ይኸው ሁኔታ ቀጥሎም በወቅቱ የአትሌቷ የቴስቴስትሮን የተባለ ሆርሞን በእጅጉ ጨምሮ በመገኘቱ ከተፈጥሮ ሕግ በተቃራኒ የወንድ ጡንቻና የተክለ ሰውነት ልትላበስ ችላለች፡፡ ሌሎች ሴት አትሌቶችም ወልደው መሳም እንዳይችሉና የተቀሩት ደግሞ በአፈጣጠራቸው ላይ እንከን ያለባቸውን ልጆች እንዲወልዱ ምክንያት ሆኗል፡፡

በዓለም ታሪክ ከታዩና በሀገር ደረጃ ከተከወኑ ስፖርታዊ ወንጀሎች መካከል በቀዳሚነት የሚቀመጥ ነው፡፡ ነገሩ አሁንም ድረስ ከስፖርታዊ የጸረ አበረታች ንቅናቄዎችና የግንዛቤ ማስጨበጫዎች ላይ እንደ ማሳያ የሚነሳ ሲሆን፤ በሰው ሕይወት ላይ ያደረሰው ጉዳት ግን በቃላት ሊገለጽ ከሚችለው በላይ ነው፡፡




# የመጀመሪያው የትምህርት ሳምንት እንዴት አለፈ?

**እየሩስ ተስፋዬ**

ሠላም ልጆች እንዴት ናችሁ? ሳምንቱ እንዴት አለፈ? በጥሩ እንዳሳለፋችሁት ምንም ጥርጥር የለኝም።ትምህርት ቤቶች ማድረግ ያለባቸውን ዝግጅት ጨርሰው እናተን መቀበል ጀምረዋል።በዚህም ምክንያት አብዛኞቻችሁ ያለፈውን ሳምንት በትምህርት እንዳሳለፋችሁ ተስፋ አደርጋለሁ። ከዚህ ጎን ለጎንም የናፈቃችኋቸውን ጓደኞቻችሁን፣ መምህራን እና በትምህርት ቤት ውስጥ የሚሠሩትን ሌሎች ሰዎች ዳግም በመገናኘታችሁ ደስ እንዳላችሁ ምንም አልጠራጠርም።

ልጆችዬ ከረዥም ጊዜ ረፍት በኋላ ትምህርት ስትጀምሩ ምን ተሰማችሁ? በርግጥ እናንተ ጎበዞች ስለሆናችሁ አልከበዳችሁም አይደል?።የክረምቱን ወቅት በንባብ እንዲሁም ትምህርታችሁን ላለመርሳት ደብተሮቻችሁን በማንበብ ጥረት ስታደርጉ እንደነበር እተማመናለሁ። ከዚህ በኋላም በክፍል ውስጥ በንቃት በመከታተል፣ በማጥናት እና መምህራኖቻችሁን በመጠየቅ በትምህርታችሁ መጠንከር ይኖርባችኋል፡፡

አንዳንዶቻችሁ ደግሞ ከዚህ ቀደም ከነበራችሁበት ትምህርት ቤት በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ሌላ ትምህርት ቤት የገባችሁ ተማሪዎች ትኖራላችሁ። በተለይም ለእናንተ እንደ አዲስ ተማሪዎችን እና መምህራንን መተዋወቅ ግድ ይላችኋል።ነገሮች ለጊዜው አዲስ ሊሆንባችሁ እንደሚችል በመገመት፤ ከተማሪዎች፣ ከመምህራን ጋር በመላመድ፤ ትምህርታችሁን እየተከታተላችሁ ፣ እያጠናችሁ እና እየተጫወታችሁ የትምህርት ጊዜያችሁን በጥሩ መንገድ ማስኬድ



ትችላላችሁ፡፡

ያለፈው ሳምንት ትምህርቱ አሰጣጥ ከሌላው ጊዜ ቀለል ያለ ሊሆን እንደሚችል ይጠበቃል።ከዚህ በኋላ ግን ወደ መደበኛው የመማር ማስተማሩ ሂደት በስፋት ስለሚገባ የክፍል እና የቤት ሥራዎችን በመሥራት፣ ያልገባችሁን በመጠየቅ፣ በማጥናት በክፍል ውስጥ ባለመረበሽ ትምህርታችሁን በንቃት ከተከታተላችሁ ጎበዝ ተማሪ እንድትሆኑ ይረዳችኋል።

ወደ ወላጆች ደግሞ እንለፍ። ወላጆች ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ልጆቻቸውን ለሀገር፣ ለወገን እና ለራሳቸው እንዲጠቅሙ በማሰብ ስማችሁ መርቃችሁ ትሸኛላችሁ። በይበልጥ ደግሞ ለመጀመሪያ ጊዜ ልጆቻችሁን ወደ ትምህርት ቤት የላካችሁ ወላጆች ስሜታችሁ ድብልቅልቅ (የደስታና የኀዘን) ያለ እንደሚሆን ይጠበቃል።ከዚህ ቀደም ልጆቹ አብረዋችሁ የሚውሉ ከሆነ እና ከነሱ ተይቶ ለመዋል ከባድ ሆኖባቸው ልጅም ወላጅም በጋራ ሲያልቅሱ ይታያሉ።ይሁን እንጂ ለልጆቻችሁ ለወደፊት ሕይወት እንደ አንድ ወሳኝ ምዕራፍ የሚታይ መሆኑን መዘንጋት የለባችሁም።እንዲህ አይነቱ ነገር በጊዜ ሒደት የሚለመድ ሲሆን፤ ልጆቻችሁ እናንተን አይተው እንዳይረበሹ ይህንን ወቅት በጥንካሬ ማሳለፍ ይኖርባችኋል።

በተጨማሪም ልጆቻችሁ ትምህርት እንዲወዱ ስለ ትምህርት ጥሩ ነገር በመንገር እና በትምህርት ቤት ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ ምን እንደሚመስል በዝርዝር በመንገር የጀመሩትን ትምህርት በተሻለ መንገድ እንዲቀጥሉ በሥነ ልቦና ዝግጁ ማድረግ ከወላጅ ወይም አሳዳጊ የሚጠበቅ ኃላፊነት ነው።

ከትምህርት ቤት ሲመለሱም ትምህርታቸውን እንዲያጠኑ ምቹ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ለምሳሌ የማጥኛ ሥፍራ በማዘጋጀት፣ እንደ ቴሌቪዥን፣ ታብሌት፣ የእጅ ስልክ (ሞባይል) ያሉ እና መሰል የልጆችን ትኩረት በቀላሉ ሊስቡ የሚችሉ ነገሮችን ማራቅ ይገባል።እንዲሁም ወደ የመኝታ (እንቅልፍ የሚተኙበትን እና የሚነሱበትን) ሰዓት እና የጥናት ሰዓታቸውን በማውጣት፣ የትምህርት ቤት ውሏቸው ምን እንደሚመስል በመጠየቅ፤ ልጆች የትምህርት ቤት ውሏቸውን እንዲወዱት ማለማመድ ይገባል።

ታዲያ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ትምህርት ቤት የገቡ ልጆችን ተጨንቀው እንዲያጠኑ ከማድረግ ይልቅ በማጫወት እና ዘና እንዲሉ በማድረግ ትምህርት ቤት ገብቶ መማር ቀላል እንጂ ከባድ አይደለም የሚለውን ነገር እንዲስቡ ያደርጋቸዋል።ሁኔታዎች የተመቻቸላችሁ ከሆነም እነርሱን ለማበረታታት ከልጆቻችሁ ጋር በጋራ በማንበብ እና በመጻፍ ብታለማምዱ የትምህርት ፍላጎታቸውን በከፍተኛ ሁኔታ ለማነሳሳት ያግዛቸዋል።ገና ማንበብ ያልጀመሩ ወይም የማይችሉ ልጆቻችሁን ደግሞ ተረት በማንበብ፤ የማንበብ ልምድ እንዲኖራቸው ከወዲሁ ከማለማመድ ባሻገር ከልጆቻችሁ ጋር ደስተኛ ጊዜ እንድታሳልፉ ይረዳችኋል።

ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ማሰብ ያለባችሁ ነገር ቢኖር፤ አንዳንድ ተማሪዎች ደፋር፣ ተግባቢ... ሲሆኑ፤ አንዳዶቹ ደግሞ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ለመላመድ ጊዜ የሚፈጅባቸው፣ ቁጡ፣ አኩራፊ ወይም የሚፈሩ እና መሰል ጸባይ ያላቸው መሆኑን በማጤን፤ ልጆቻችሁን የምክር እና የሥነ ልቦና ድጋፍ ልታደርጉላቸው ይገባል፡፡

ለመጀመሪያ ጊዜ ይሁን ከዚህ ቀደም ወደ ትምህርት ቤት የገቡ ልጆች ትምህርታቸውን ያለ አንዳች እንከን እና ለቀጣዩ ቀን ደስ ብሏቸው እንዲሄዱ በማድረጉ በኩል የመምህራን ድርሻ ላቅ ያለ ነው።የነገ ሀገር ተረካቢውን ዜጋ በሥነ ምግባር የታነጸ እንዲሆን በማድረግ መምህራኑ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ።ስለሆነም ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ትምህርት ቤት የሚመጡ ልጆች እንግዳ ነገር ሊያሳዩ የሚችሉ መሆኑን በማሰብ ሂደቱን እስኪለማመዱት ድረስ በትዕግስት መወጣት ይኖርባችኋል፡፡